
# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## 6ኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ





*የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ*



# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
# 6ኛ ክፍል
# የተማሪ መጽሐፍ



በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# 6ኛ ክፍል

አዘጋጆች፡-ዳንኤል ኃይለኢየሱስ (MA)

ህይወት ታምሩ (MA)

ሰለሞን ሰርካ (BA)

ኤዲተር፡-ሃብታሙ መስፍን (MA)

ጥራት ተቆጣጣሪ፡-እንግዳ ዘውዴ (PHD)

አወቀ ፀጋዬ (MA)

ጥቅምት 2014

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና የ__________ዞን ትምህርት መምሪያ/ ልዩ ወረዳ የቴክኒክ ድጋፍ በ___________ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

## ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ልጆቻችን የቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይገነዘቡዘንድ የመምህራን እና የእርሶ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት በቤትዎ ውስጥ ልጅዎን ያግዙ፡፡

1. ለልጆችዎ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን. . .ይንገሯቸው/ያንብቡላቸው (እንዲያነቡ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩላቸው)፡፡

2. ለልጆችዎ የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ልጆችዎ መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

3. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው(ያስረዷቸው)፡፡

4. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

5. ልጆችዎ መምህራቸው በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የሚሰጣቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎትን ይወጡ፡፡

መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡ ከዚህ መጽሐፍ የሚጠበቁ ውጤቶችም ፡- ማዳመጥና መናገር መቻል ፣ማንበብና መጻፍ መቻልና የስዋስውና ሥነ ጽሑፍ እውቀትና ችሎታ ናቸው፡፡

መጽሐፉ ለ6ኛ ክፍል የተዘጋጀው አገር በቀል እውቀትን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ተማሪዎችም በደረጃቸው ባህላዊ ነገሮችን፣ ሳይንሳዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊ ፣አከባቢያዊ፣ ዓለም አቀፍዊ ፣ ወዘተ. ይዘቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ መጽሐፉም ለይዘታዊ ጉዳዮች ቀዳሚ ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ በይዘቱ አማካይነት ተማሪዎች የመናገርና የማዳመጥ፤የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲሁም የሰዋሰውና የስነ ጽሁፍ እውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ ስለሚያስችል ነው፡፡

በዚህ መሰረት መጽሐፉ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን አንደኛው መረዳዳትን ፤ሁለተኛው ባህላዊ የግጭት አፈታትን ፣ሦስተኛው የሴቶች ሚና ፣አራተኛው ስለ አካባቢ መናገርን ፣ አምስተኛው የታዋቂ ሰዎችን ህይወት ታሪክ ፣ስድስተኛው ሀገር ወዳድነትን ፣ሰባተኛው ባህልን ፣ስምንተኛው መቻቻልን፣ዘጠነኛው ተላላፊ በሽታዎችን ፣አስረኛው የፈጠራ ስራን የሚመለከቱ ይዘቶች አሏቸው፡፡ለነዚህም ተገቢነት ያላቸው ማራኪና ተገቢ ምንባቦች ተመርጠው ተካተዋል፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፍ አስቀድሞ የሚጠበቁ ውጤቶች ተቀምጠዋል፡፡ ሁሉም ምዕራፎች በመርሐ ትምህርቱ መሰረት እንደ የስፋታቸው በክፍለ ጊዜያት የተደራጁ ሲሆኑ በዚህም የማዳመጥና የመናገር ክፍሎች ቀድመው ፣የማንበብና የመፃፍ ክፍሎች ተከትለው በመጨረሻው የሰዋሰውና የስነ - ጽሁፍ እውቀቶች ተደራጅተዋል፡፡

ይህ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የሥርአተ - ትምህርቱ ቅደም ተከተል፣ ተደራሽነት ፣የማስተማር ዘዴ ፣ወደ ጎንና ወደ ላይ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ግኑኝነት ፣አነባበቡና ግልጽነቱ፣ የአገላለጽ ዘዴው ፤በአግባቡ እንዲጠበቅ

ተደርጓል፡፡ መጽሐፉ ወቅታዊነት ፣ሳይንሳዊነትና ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰቦችን የሚያንፀባርቁ ይዘቶች ያሉበት ነው፡፡

ተማሪዎች አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በመጽሐፉ ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትንና መልመጃዎችን በየምዕራፉ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ ተግባራቱ ተማሪዎች ቋንቋቸውን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙበት ብሎም የመናገርና የማዳመጥ የንባብና የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ሰፊ አማራጮች የሚሰጡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የሰዋሰውና የስነ - ጽሁፍ ሥራዎችን እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል፡፡

በመጽሐፉ በሁሉም ምዕራፎች መጨረሻ የምዕራፉ ክለሳና የመልመጃ ጥያቄዎች ተቀምጠዋል፡፡ መልመጃዎቹም ሆኑ ተግባሮቹ ከላይ ርዕስ አድርገው የተነሱትን ክፍልም ይሁን ስዋስው መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህም የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ያስችላሉ የሚል ግምት አለ፡፡

በአጠቃላይ መጽሐፉ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከደረጃቸው አንፃር የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጡ በትክክል ያስችላቸዋል፡፡ የሚል እምነት አለ፡፡

መልካም ትምህርት

# የይዘት ማውጫ

ምዕራፍ 1

መረዳዳት ----------------------------------------------------------1

ምዕራፍ 2

ባህላዊ የግጭት አፈታት ------------------------------------------20

ምዕራፍ 3

የሴቶች ሚና ------------------------------------------------------------38

ምዕራፍ 4

ስለ አካባቢ መናገር ---------------------------------------------------54

ምዕራፍ 5

የታዋቂ ሰዎች ታሪክ ---------------------------------------- 67

ምዕራፍ 6

ሀገር ወዳድነት ----------------------------------------------------81

ምዕራፍ 7

ባህል ---------------------------------------------------------------93

ምዕራፍ 8

መቻቻል --------------------------------------------------------------103

ምዕራፍ 9

ተላላፊ በሽታዎች -------------------------------------------------115

ምዕራፍ 10

የፈጠራ ስራ ---------------------------------------------------------126

# ምዕራፍ አንድ

# መረዳዳት

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- በመጣመራቸው ምክንያት ተጨማሪ ፍች የሚያመጡ ቃላትን አዳምጣችሁ ፍቻቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- በሚና ጨዋታዎች አማካኝነት ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ ፡፡
- ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን አውቃችሁ ቃላትን በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- ሥርአተ ነጥቦችን በአረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፡
- ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ መሣሪያዎችን ሥም ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን በመነጠል ታወጣላችሁ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ቃላት ሲጣመሩና በተናጠል ሲሆኑ የሚኖራቸውን የፍች ልዩነት በማዳመጥ ትናገራላችሁ፡፡
- ቃላትን በማጣመር ጥምር ቃል ትመሰርታላችሁ፡፡

### ጥምር ቃላትን ማዳመጥ

**ማስታወሻ**

ጥምር ቃላት የምንላቸው በሁለት የተለያዩ ቃላት ተመስርተው እንደ አንድ ቃል የሚነበቡ ሲሆኑ ፍችያቸውም መጀመሪያ በተናጠል ከነበራቸው ፍች የተለየ ነው፡፡

**ተግባር 1. ቀጥለው የቀረቡትን ምሳሌዎች በደንብ በመመልከት ያሳዩትን የፍች ለውጥ ተረዱ።**

ምሳሌ 1. **እንጀራ** - የዚህ ቃል ቀጥተኛ ፍች ከጤፍ ዱቄት የሚሰራ ምግብ ሲሆን፤

**እናት** - የዚህ ቃል ቀጥተኛ ፍች ደግሞ ወላጅ ይሆናል ።

ምሳሌ 2. **እንጀራ እናት** - ሲል ግን ቀጥተኛ ፍችው ፡ ወላጅ ያልሆነች የእናትነትን ሚና የምትጫወት የአባት ሁለተኛ ሚስት ማለት ነው።

**ተግባር2. ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ (ሲጠሩላችሁ) በማዳመጥ ፍችያቸውን ተናገሩ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሜዳ | ብረት | ድስት | ትምህርት |
| ጣቢያ | ኳስ | ቤት | ጤና |

**ተግባር 3 . በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር የሚኖራቸውን ቀጥተኛ ፍች በጽሑፍ አሳዩ።**

| ቃል | ቃል | ጥምር ቃል | ቀጥተኛ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1. ሐኪም | ቤት | ሐኪም ቤት | የህክምና ማዕከል |
| 2. አልጋ | ልብስ | | |
| 3. ነጠላ | ጫማ | | |
| 4. ምግብ | ቤት | | |
| 5. ፓሊስ | ጣቢያ | | |

## *አንደኛ ሳምንት ፡ ክፍለ ትምህርት ሁለት*

### *ቃላት*

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-**

- የተለያዩ የአካል ጉዳተኞች መገልገያ መሳሪያዎችን ስም ትዘረዝራላችሁ።

**ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ መሣሪያዎች**

**ተግባር 1.** ከላይ በርዕሱ የተመለከታችኋቸውን ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ መሣሪያዎች ስም በቡድን በመሆን ለማወቅ ሞክሩ፡፡

**ተግባር 2.** የቀረበውን ስዕል መሰረት በማድረግ መሣሪያዎቹ ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ተናገሩ፡፡

**ተግባር 3.** በአካባቢያችሁ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች በባህላዊ መንገድ እራሳቸውን ለመደገፍ የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች በቡድን በመሆን ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## አንደኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ሶስት

### መናገር

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤-**

- የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ፡፡
- ስለምትወዷቸው ጨዋታዎች ትናገራላችሁ
- አጫጭር ጭውውት ታቀርባላችሁ፡፡

**ተግባር፡- ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ**

1. በአካባቢያችሁ በስፋት የተለመደ ጨዋታ ምንድነው ?
2. እነዚህን ጨዋታዎች ተጫውታችኋል?
3. በቡድን በመሆን ከምታውቋቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱን በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጭውውት መልክ አቅርቡ ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፡ክፍለ ትምህርት አራት

### ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን ለቅማችሁ በማውጣት ታሳያላችሁ፡፡
- ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን ጠብቃችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ከአነባበባችሁት ምንባብ መረጃ ታወጣላችሁ፡፡

***ሳልስና ሳድስ ፊደላትን ማንበብ***

**ተግባር 1. ቀጥለው ከቀረቡት ቃላት ውስጥ በሳልስ ፊደል የሚጀምሩትን ቃላት በአንድ በኩል በሳድስ ፊደል የሚጀምሩትን በሌላ በኩል በመፃፍ አስቀምጡ፡፡**

ምሳሌ ባእድ /እ/ ክፍል /ክ/ /ፍ/ /ል/ ሚጥሚጣ /ሚ/

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቢሮ | ትዳር | ቅጠል | ብር |
| ምግብ | -ሚዛን | ሊቅ | ቢላዋ |
| ሲሆን | ስሆን | ቢሆን | ብሆን |

**ተግባር 2 .** በሳልስና በሳድስ ፊደል ቅድም ተከተል የለያችኋቸውን ቃላት ድምፃችሁን ጮክ በማድረግ ተራ በተራ አንብቡ ፡፡

**ተግባር 3 . ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሳልስና ሳድስ ፊደላት በትክክል ጠብቃችሁ አንብቡ፡፡**

ዘወትር ጧት ከመኝታህ እንደተነሳህ ፊትህን መታጠብ አለብህ፡፡ ቁርስህን ከበላህ በኋላ ጥርስህን መፋቅ አትርሳ፤ ይህም ለንጽህናህ ብቻ ሳይሆን የጥርስህንም ጤንነት ይጠብቅልሃል፡፡ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሁል ጊዜ ንፁህ ሆነህ መታየት አለብህ፡፡ በእረፍት ጊዜህ ደግሞ ልብስ ማጠብና ሌላም ስራ መስራት እንዳለብህ እወቅ፡፡ ጤንነትህ የተጠበቀ እንዲሆን ሁል ጊዜ ንፁህ ልብስ መልበስና ገላህን መታጠብ አለብህ፡፡ በዚህ አይነት ንፁህ ሆነህ የሚያዩህ ሰዎች ሁሉ ጥሩና ጎበዝ ልጅ ነህ ይሉሀል፡፡

## ሁለተኛሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አምስት

### አንብቦ መረዳት

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- የቀረበላችሁን ምንባብ የንባብ ሂደት ስርአትን ጠብቃችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ትናገራላችሁ ፡፡

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ሀ. የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት መልካም ነው ትላላችሁ?

ለ. አካል ጉዳተኛ ብለን የምንጠራቸው ምን አይነት ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ነው?

ሐ. አካል ጉዳተኞችን መርዳት የምንችለው እንዴት ነው?

## መስማት የተሳናቸው

አብዛኛውን ጊዜ የመስማት ችግር ያለባቸው ህፃናት የመናገር ችግር አለባቸው፡፡ የንግግር ድምፃቸውንም ሰዎች ሲሰሙት ያልተለመደ አይነት ይመስላል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት መስማት የተሳናቸው ሰዎች የንግግር ድምጽ ምን አይነት ድምጽ ሊኖረው እንደሚችል ስለማያውቁ ነው፡፡ ለእነዚህ ህፃናት በትክክለኛው ቋንቋ መናገር በጣም ይከብዳቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት መስማት የተሳናቸው ህፃናት አለመናገርን ይመርጣሉ፡፡ እናም በአካላዊ እንቅስቃሴዎች (gestures) ወይም በምልክቶች ብቻ ይግባባሉ፡፡የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች ለመናገር ስለሚፈሩና ስለሚያፍሩ ፣ ለመናገር የሚደፍሩት በደንብ ከሚያወቋቸውና ከሚግባቧቸው ሰዎች ጋር ብቻ ነው፡፡ እነዚህ መናገር የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ልዩ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ድጋፉ ደግሞ በማህበራዊ ህይወታቸው ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ትልቅ እገዛ ያደረግላቸዋልና በምናደርግላቸው ድጋፍና እርዳታ ከእለት ተእለት ህይወታቸው ጀምሮ እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን፣ ችሎታቸውን ፣እንዲያዳብሩ ከፍተኛ እገዛ ያደረግላቸዋል፡፡ መስማት የተሳናቸው ህፃናት በማህበረሰቡ ውስጥ መሳተፍ፣ የሚባለውን መስማት፣ የሚደረገውን ነገር መስማት ይፈልጋሉ፡፡ በነዚህ ሂደቶች ውስጥ ይህንን ለማድረግ ድጋፍና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በትምህርት ቤት ለመማር ሲመጡ ልንረዳቸው ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ህፃናት

መስማት የተሳናቸው መሆናቸውን እንዳወቅን ወደ ትምህርት ቤት ሄደው የምልክት ቋንቋ እንዲማሩ በማድረግ ድጋፍ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡ በተመሳሳይም ወላጆቻቸውም ሆኑ ተመሳሳይ ሰዎች በምልክት ቋንቋ በመማር የሚነገሩ ነገሮችን በመተርጎምና በምልክት ቋንቋ ለነሱ በማስረዳት ሊተረጉሙላቸው ይገባል፡፡

ባጠቃላይ መስማት የተሳናቸው ህፃናት እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሊያውቁ ፣ሊማሩ ትልቅ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው የእኛ ድጋፍና እርዳታ ሲታከልበት መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ መስማት የተሳናቸው ህፃናት በቃ፣ አለቀላቸው ተብለው የሚተዉ አለመሆናቸውን አውቀን አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ሁሉ በቅንነትና በታማኝነት ልናደርግላቸው ይገባል፡፡

(መስማት የተሳናቸውና ችሎታቸው ገጽ 147 ተሻሽሎ የተወሰደ )

**ተግባር 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የመስማት ችግር ያለባቸው ህፃናት የመናገር ችግር የሚገጥማቸው ለምንድነው ?
2. መናገርና መስማት የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ምን አይነት ድጋፍ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል?
3. መስማት የተሳናቸውና መናገር የማይችሉ ህፃናት መስማት ፣መናገር ከሚችሉ ህፃናት ጋር ባንድ ላይ እንደ ጓደኛ እንዲሆኑ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

**ተግባር 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

ሀ/ መስማት የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ድጋፍ አይፈልጉም፡፡

ለ/ መስማት የተሳናቸው ህፃናትን መርዳት ተገቢ ነው ፡፡

ሐ/ ብዙውን ጊዜ የመስማት ችግር ያለባቸው ሕጻናት የመናገር ችግር የለባቸውም፡፡

መ/ መስማትና መናገር የማይችሉ ህፃናትን ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ አያስፈልግም፡

ሠ/ መስማትና መናገር የማይችሉ ህፃናት ተምረው ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ተግባር 3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተስማሚውንመልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. መስማትና መናገር የተሳናቸውን ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት የምንልከው ለምንድነው?

   ሀ/ ተምረው በምልክት ቋንቋ መግባባት እንዲችሉ፡፡

   ለ/ በተማሩት ልክ እራሳቸውንና አገራቸውን መርዳት እንዲችሉ፡፡

   ሐ/ በራስ የመተማመን ስሜት እዲኖራቸው ለማድረግ ፡፡

   መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

2. መስማት የተሳናቸውና መናገር የማይችሉ ህፃናት ባለ መማራቸው ሊያጡት የሚችሉት ነገር ምንድነው?

   ሀ/ እንደማንኛውም ማህረሰብ ሊያውቁ የሚገባቸውን ነገር ሳያውቁ ይቀራሉ፡፡

   ለ/ እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሊረዱ የሚገባቸውን ነገር ሳይራዱ ይቀራሉ፡፡

   ሐ/ እራሳቸውን ከማህበረሰቡ ዝቅ አድርገው ያያሉ፡፡

   መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

3. መስማት የተሳናቸው ህፃናት አለመናገርን የሚመርጡት ለምንድነው?

   ሀ/ የንግግር ድምጾችን ለይተው ስለማያውቁ ነው፡፡

   ለ/ በትክክለኛው ቋንቋ መናገር ስለሚችሉ ነው፡፡

   ሐ/ በቀላሉ ከጓደኞቻቸው ጋር መግባባት ስለሚችሉ ነው፡፡

   መ/ መልሱ አልተሰጠም፡፡

4. መስማት ለተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ልዩ ድጋፍ ሲደረግላቸው

   ሀ/ በማህበራዊ ህይወታቸው ደስተኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ፡፡

ለ/ ህይወታቸውን ደስተኛ በሆነ መንገድ መምራት ይችላሉ።

ሐ/ ተስፋቸውን ያሳድግላቸዋል።

መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል።

## ሁለተኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ስድስት

### መፃፍ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- በአረፍተ ነገር ውስጥ ስርአተ ነጥቦችን በትክክል ትጠቀማላችሁ።
- የተጓደሉ ሥርአተ ነጥቦችን ታሟላላችሁ።

**ማስታወሻ**

- ስርአተ ነጥቦች ፦ በቃላት ፣ በሀረጋት ፣ በአረፍተ ነገሮች መሀከልና መጨረሻ በመግባት ጽሁፍን ለመረዳት እንዳያስቸግርና መልእክቱ ግልጽ እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው።
- ነጠላ ሰረዝ (፣) የሚዘረዘሩ ቃላትንና ሀረጋትን ለመለየት ያገለግላል።
- ጥያቄ ምልክት (?) ጥያቄያዊ በሆኑ አረፍተ ነገሮች መጨረሻ በመግባት አረፍተ ነገሩን ጥያቄያዊ ያደርጋል።

**ተግባር 1. ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመመልከት ሥርዓተ ነጥቦቹ የገቡበትን ቦታ ተረድታችሁ ግንዛቤ ጨብጡ።**

<u>ምሳሌ</u>፡- 1. ድርጅቱ ለተጠቃሚዎች ጨው ፣ስኳር፣ዘይትና ሳሙና ያቀርባል።

2. ትናንት ወደቤት የመጣው ማነው?

3. ከወንድሜ ጋር በሳምንታችን ዛሬ ተገናኘን።

4. አካሬሰ፣ ዋኖና ሎዘንቦ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ።

5. ምን ትፈልጋለህ?

**ተግባር 2. የጎደሉትን ስርዓተ ነጥቦች አሟሉ።**

- ዘይሴ ሙዝ ብርቱካን ማንጎና ሎሚ ከገበያ ገዛች
- ትምህርት ቤት መቼ ነው የሚዘጋው

- ደያሶ ለልጁ መማሪያ ደብተር ብዕር እርሳስና ላጲስ ገዛለት
- መማር እውቀትንና ችሎታን ለማዳበር ይረዳል

## ሶስተኛ ሳምንት፡ክፍለ ትምህርት ሰባት

## አንብቦ መረዳት

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- ምንባቡን በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፤

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄ

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

ሀ/ ማየት የተሳናቸው ልጆች እንደማንኛውም ሰው ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር የሚያስችላቸው ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ/ ከኛ ጋር አብረውን ሲማሩ ማየት የተሳናቸውን ተማሪዎች እንዴት ነው መርዳት የምንችለው?

## ትንሿ ዛይሴ

ዛይሴ የምትኖረው በደቡብ ክልል ውስጥ በምትገኘው ትንሽ ከተማ ዘምሳ ሲሆን ከተወለደች ጀምሮ ማየት አትችልም ነበር፡፡በዚህ ምክንያት ቤተሰቦቿም ስለሷ ይጨነቁ ነበር፡፡ዛይሴ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ እድሜዋ 12 ዓመት ደርሷል፡፡ ምክንያቱም የአካባቢው ማህበረሰብ ማየት የተሳናቸው ልጆች ትምህርት ቤት ገብተው መማር እንደሚችሉ አያወቁም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በዘምሳ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች የአንድ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆነው **ዶቢር** ወደነ ዛይሴ ቤት በመምጣት ከወላጆቿ ጋር ተገናኝና ዛይሴ ወደ ትምህርት ቤት መግባትና መማር እንደምትችልና ተምራም ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደምትችል እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ለዛይሴ መማሪያና መፃፊያ የሚሆን የትምህርት መሳሪያ እንደሚያዘጋጅላትም በመግለጽ በሳምንቱ መጀመሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዘዋት እንዲመጡ ነገራቸው፡፡

ወላጆቿም በጣም ተደስተው ዛይሴን በሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ ወደ ትምህርት ቤት ይዘዋት ሄዱ፡፡ርዕሰ መምህሩም ተማሪዋን ተቀብሎ ወደ አንደኛ ክፍል በመውሰድ ከአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር አስተዋውቋት ተማሪዎቹንም እንዲንከባከቧትና እንዲደግፏት ነገሯቸው ቦታ ካሲያዛት በኋላ ለክፍሉ አለቃ አደራ ብሎት ሄደ፡፡ ዛይሴ በዚያ ቀን በህይወቷ የማትረሳው ከፍተኛ ደስታ ተሰማት፡፡ያገኘቻቸው ተማሪዎች ጓደኛ በመሆን ተራ በተራ ይዘዋት ሲሄዱ ግቢውን ሲያስጎበኟት ፣ከልጆች ጋር ሲያስተዋውቋት ሂሊናዋ በደስታ ተውጦ ጓደኞቿን በጣም አመሰገነቻቸው፡፡እነሱም ሁል ጊዜ ከሷ እንደማይለይዋት፤ እንደሚረዷት፤ አብረዋትም ሁሉን እንደሚያደረጉ ነግረዋት ሲደወል ወደ ቤት አድርሰዋት ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

(ለማስተማሪያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ )

**ተግባር2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ዛይሴ የምትኖረው ምን በምትባል ከተማ ውስጥ ነው?
2. ትምህርት መማር እንዳለባት ለወላጆቿ የነገረው ማነው?
3. ዛይሴ ጓደኞቿን ያመሰገነችው ለምንድነው?

**ተግባር3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ዛይሴ ከመጀመሪያውም ትምህርት ቤት ያልገባችው መማር ስለማትፈልግ ነበር፡፡
2. ዛይሴን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ይዟት የመጣው የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ነው፡፡
3. ዛይሴ ማየት ስለማትችል ወላጆቿ ስለሷ ሁሌም ይጨነቁ ነበር፡፡
4. ማየት የተሳናቸው ልጆች ከሌሎች ልጆች ጋር እኩል የመማር መብት አላቸው፡፡
5. ዛይሴ የተዋወቀቻቸው ልጆች ተራ በተራ ጊቢውን ያስጎበኟት ነበር፡፡

**ተግባር4. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ አገባብ መሰረት በማድረግ ፍች ስጧቸው።**

ሀ/ ተደሰተች　　　　መ/ ተራ በተራ

ለ/ በህይወቷ　　　　ሠ/ መማሪያ

## ሦስተኛ ሳምንት፦ክፍለ ትምህርት ስምንት

### ቅጥያዎች

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- ስለ ቅጥያ ምንነት አውቃችሁ ታብራራላችሁ።
- ቅድመና ድህረቅጥያን ነጥላችሁ ታወጣላችሁ፡

**ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን በመነጠል ማውጣት**

**ማስታወሻ**

ቅጥያ - የምንለው በዋናው ቃል ላይ የሚጨምር ሲሆን የሚጨመረውም ከዋናው ቃል ቀድሞ ወይም ተከትሎ ሊሆን ይችላል

ቅድመ ቅጥያ፡- - ከዋናው ቃል ቀድሞ የሚቀጠል ቅጥያ ነው።

ድህረ ቅጥያ፡- - ከዋናው ቃል መጨረሻ የሚቀጠል ቅጥያ ነው።

**ተግባር1.** የቀረበውን ምሳሌ በደንብ በመመልከትና በመረዳት ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን ለይታችሁ በማውጣት አሳዩ።

| ምሳሌ፡- | ቃል | ዋናቃል | ቅድመ ቅጥያ | ድህረ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መጣችሁ | መጣ | ---------- | - ኣችሁ |
| 2. | አልመጣም | መጣ | አል - | -ም |
| 3. | ቤቶች | | | |
| 4. | ከፊታችን | | | |
| 5. | ተራመደች | | | |
| 6. | አሰለጠነ | | | |

## ሦስተኛ ሳምንት፡ክፍል ትምህርት ዘጠኝ

### ስነ ጽሁፍ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- ስለ እንቆቅልሽ ምንነት አውቃችሁ ትናገራላችሁ፡
- እንቆቅልሽ ታቀርባላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

እንቆቅልሽ፡- አብዛኛውን ጊዜ ህፃናት የሚጫወቱት የጥያቄና የመልስ ጨዋታ ሲሆን አንዱ ጠያቂ ሌላው መላሽ ሆኖ ይካሄዳል፡፡ እንቆቅልሽ አመራማሪ ሲሆን የማሰላሰል ችሎታን ያሳድጋል፡፡

**ተግባር 1. የሚከተለውን ምሳሌ በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን እንቆቅልሾች መልሱ፡፡**

ጠያቂ = እንቆቅልሽ / ህ

መላሽ = ምን አውቅልህ /ሽ

ጠያቂ = ላዩ በድን ታቹ በድን መሀሉ ነብስ አድን

መላሽ = እንጀራ

ጠያቂ = በትክክል አግኝተሃል፡

በዚህ ጊዜ መላሹ መልሱን ካገኘ ወደ ጠያቂነት ሲሻገር ጠያቂው ደግሞ ወደ መላሽነት ይዞራል፡፡

ጠያቂ = እንቆቅልሽ / ህ

መላሽ = ምን አውቅልህ /ሽ

ጠያቂ = ትንሽ ምላጭ አገር ትላጭ

መላሽ = ምላጭ

ጠያቂ = አላገኘህም (አገር ስጠኝ ብሎ ይጠይቃል)

በዚህ ጊዜ መላሹ መልሱን ስላላገኘ ወደ ጠያቂነት አይዞርም፡፡

እራሱ ተጠያቂ ሆኖ ይቀጥላል፡፡መልሱን አግኝቶ ጠያቂ ለመሆን በሚያደርገው ጥረት የውድድር መንፈስ ይፈጠራል፡፡

- ባለአራት እግር ወንዝ አያሻግር
- ሁለት ጎሮቤቶች የማይተያዩ
- ቀይ ሙሽራ በነጭ አጥር ታጥራ
- ትልቅ ጫካ ገብቼ አንድ ዱላ አጥቼ

**ተግባር 2. በአካባቢያችሁ በስፋት የሚነገሩትን እንቆቅልሾች ሰብስባችሁ በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በመጀመሪያ ቃላት በተናጠል ሲሆኑና ሲጣመሩ የፍች ልዩነት እንደሚያመጡ ተመልክታችኋል፡፡የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጠቀም ሀሳባችሁን ገልፃችኃል ፤እንዲሁም አካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙባቸውን መገልገያ መሳሪያዎች ተመልክታችኋል ፡፡ሳድስና ሳልስ ፊደሎችን አስተካክላችሁ እንዴት ማንበብ እንዳለባችሁ ተምራችኋል፡፡በተጨማሪም መስማት የተሳናቸውን መርዳት በሚልና ትንሿ ዛይሴ በሚል የተዘጋጀውን ምንባብ አንብባችሁ መልመጃዎችን ሰርታችኋል፡፡በመጨረሻም ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን ማውጣትን የሰራችሁ ሲሆን ፤ እንቆቅልሾችንም ከዚሁ ጋር አያይዛችሁ ተምራችኋል፡፡

**ቀጥለው ለቀረቡት ጥምር ቃላት ቀጥተኛ ፍች ስጡ፡፡**

- ሰውሰራሽ
- ራሰበራ
- ቤተመጻሕፍት

**ከዚህ በታች ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያና ድህረ ቅጥያን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

1. ስለሸለመው
2. እንደችሎታችሁ
3. አስደበደበው

**ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም ዐረፍተ ነገሩን አሟሉ።**

1. ምግብ ውሃ ልብስና መጠለያ ለኑሮ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ዋንኞቹ ናቸው
2. ነገ በዚህ ሰአት ወዴት ትሄጃለሽ
3. ጥሬ ስጋን መብላት አልወድም

## ምዕራፍ ሁለት

## ባህላዊ የግጭት

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፦**

- የጓደኞቻችሁን ሃሳብ አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- በሚሰጣችሁ ርዕስ ላይ የቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡
- መመሪያዎችን አንብባችሁ ተግባራትን ትፈጽማላችሁ፡፡
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅማችሁ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- በየባህሉ ያሉ ባህላዊ እሴቶች የሚጠሩበትን ስያሜ መዝግባችሁ ታቀርባላችሁ፡፡
- ባለቤት ፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽን በቀላል ዐረፍተ ነገር ውስጥ ታዋቅራላችሁ፡፡
- ታሪኮችን አንብባችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| ግጭት | ማሰሪያ አንቀጽ | ባለቤት |
| አፈታሪክ | መመሪያ | ማዋቀር |
| አያያዥ | ትዕዛዝ | ተሳቢ |

## አንደኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አንድ

## ቃላት

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- የቃላትን ፍች ትናገራላችሁ፡፡
- ባህል ነክ ቃላትን በዐውዳቸው ትጠቀማላችሁ፡፡
- ለቃላት ከአውዳቸው አንፃር ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡት ቃላት ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት በየትኛው ባህላዊ ክንዋኔ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ አብራሩ፡፡**

**<u>ባሕላዊ በዓላት</u>**

ሀ/ እንቁጣጣሽ

ለ/ እሬቻ

ሐ/ ደራሮ

መ/ ጊፋታ

ሠ/ ፍቼ

ረ/ ዮ ማስቀላ

ሰ/ ያ ሆዬ ማስቀላ

ሸ/ ጋዜ ማስቀላ

ቀ/ ዮኦ ማስቀላ

በ/ ዮ ዮ ማስቀላ

**ተግባር2 .ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ስጡ፡፡**

1. ብልሃት
2. ያልተሰራ
3. ትኩረት
4. ብዙ
5. ለጋ

**ተግባር 3. ከላይ የቀረበውን መልመጃ (ተግባር) ሰርታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረበውን ባዶ ቦታ በተስማሚ ቃላት አሟሉ፡፡**

ሀ/ ዳንቾ በመልኳ --------------------------ስለሆነች ሰውን ሁሉ ትማርካለች ፡፡

ለ/ ሉዘንቦ ሌብነት ----------------------ባህሪ እንደሆነ ያውቃል ፡፡

ሐ/ ላምሬ በትምህርቱ አንደኛ ስለወጣ በጣም ----------------------------፡፡

መ/ ላዌ የምትኖርበት ጎጆ -------------------ስለሆነ አልጋ ለማስገባት አልቻለችም፡፡

## አንደኛ ሣምንት ፡-ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ሥዕልን ተመልክቶ ገለፃ ማድረግ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ስዕሎችን ተመልክታችሁ ገለፃ ታደርጋላችሁ፡፡
- ስዕሎችን ታወዳድራላችሁ፡፡



ሥዕል ሀ/




ሥዕል ለ/

**ተግባር1. ከላይ የቀረቡትን ስዕሎች በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. በስዕል "ሀ" ና በስዕል “ለ” ላይ የምትመለከቱት የሥራ ክፍፍል ምን አይነት ነው?
2. በራሳችሁ አመለካከት ከስዕል “ሀ” እና ከስዕል “ለ ” የትኛው ጥሩ ነው ትላላችሁ፡፡
3. ያነፃፀራችሁበት ወይም ያወዳደራችሁበት ሀሳብ ምን ነበር ?
4. ሴት የወንድን ስራ ብትሰራ ወንድም የሴትን ስራ ቢሰራ ችግር አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

**ተግባር2 ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ምንባብ በማንበብ ከየትኛው ስዕል ጋር ግንኙነት እንዳለው አብራሩ፡፡**

**ኡፋይሴና ሉፓክ**

ኡፋይሴና ሉፓክ በአንድ ላይ የሚኖሩ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ሁለቱም በቤታቸው ውስጥ ተሳስበውና ተጋግዘው በፍቅር ይኖራሉ፡፡ በሁለቱም መካከል ያለው የሥራ ሁኔታ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ምክንያቱም ማንኛውንም ስራ ሁለቱም ይሰራሉ፡፡ ኡፋይሴ እህል ስትፈጭ ወይም በቆሎ ስትወቅጥ ሉፓክ ወጥ ይሰራል፡፡ ወይም ሉፓክ እንጀራ ሲጋግር ኡፋይሴ ላሞችን ታልባለች፡፡አስፈላጊ ከሆነም ከብቶችን ወደ ወንዝ ይዛ በመሄድ ውሃ ታጠጣለች፡፡ በሉፓክ እና በኡፋይሴ መካከል ይሄ የሴት ነው ፣ ይሄ የወንድ ነው የሚል ምንም አይነት የሥራ ክፍፍልና የሥራ ንቀት የለም፡፡ ሁለቱም የደረሱበትን ሥራ ሁሉ ይሰራሉ፣ ይተጋገዛሉ፣ ይረዳዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ደስተኞች ናቸው፡፡

1. ከላይ የቀረበው አጭር ታሪክ ከየትኛው ስዕል ጋር ይመሳሰላል ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ኡፋይሴና ሉፓክን ደስተኛ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው ?
3. ኡፋይሴና ሉፓክ ሁሉንም ስራ በመስራታቸው ባህላዊ ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ ?
4. ባህላዊውን ተጽእኖ ለማለፍና ሌላውን ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**ተግባር3 ከላይ በተማራችሁት መሠረት በቡድን በመሆን ስለ አንድ ቤተሰብ የሥራ ሁኔታ ጽፋችሁ በማምጣት ለክፍል አቅርቡ፡፡**

**አንደኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ሶስት**

***ማዳመጥ***

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የጓደኞቻችሁን ሃሳብ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፡፡
- ጥንድ በመሆን ንግግርን በማዳመጥ መልሳችሁ ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር1 ቀጥሎ የቀረበውን የአቻ ንግግር ጥንድ ጥንድ በመሆን እየተቀባበላችሁ እንደ ንግግር አንብቡት፡፡የክፍል ተማሪዎችም እንዲያዳምጡ አድርጉ፡፡**

**የተማሪዎች ቃል ምልልስ**

አርሳሌ - እንተዋወቅ ማነው ስምህ ?

ቦርድሎ - ቦርድሎ እባላለሁ አንቺስ ?

አርሳሌ - እኔ አርሳሌ እባላለሁ ፡፡

ቦርድሎ - ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል፡፡

አርሳሌ - እኔም ደስ ብሎኛል፡፡

ቦርድሎ - ወዴት እየሄድሽ ነው ?

አርሳሌ - ወደ ትምህርት ቤት

ቦርድሎ - ስንተኛ ክፍል ነሽ ?

አርሳሌ - ስድስተኛ ክፍል ነኝ ፡፡

ቦርድሎ - በጣም ይገርማል ! እኔም የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ በትምህርቴ ደግሞ ጎበዝ ስለሆንኩ የደረጃ ተሸላሚ ነኝ፡፡

አርሳሌ - በጣም ደስ ይላል፡፡

ቦርድሎ - አንቺስ በትምህርትህሽ እንዴት ነሽ?

አርሳሌ - በጣም ጎበዝ ተማሪ ባልባልም መሀከለኛ ተማሪ ነኝ፡፡

ቦርድሎ - ጥሩ! ጎበዝ ለመሆን በርትተሽ ማጥናት ይጠበቅብሻል፡፡

አርሳሌ - ከዚህ በኋላ እኔም ጊዜ በመስጠት በሚገባ ለማጥናት ወደ ፊት ለመሆን የምፈልገውን ለማሳካት እጥራለሁ፡፡

ቦርድሎ - በጣም ጥሩ ውሳኔ ነው የወሰንሽው፤ ሁለታችንም በዚህ ዓመት ተሸላሚ እንደምንሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

አርሳሌ - እኔም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ቦርድሎ - በድጋሚ ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል መልካም የትምህርት ጊዜ ይሁንልሽ፡፡

አርሳሌ - ላንተም፣ ቸር ያገናኘን፡፡

**ተግባር2. ከላይ የቀረበውን የተማሪዎች ቃለ ምልልስ ባዳመጣችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ/ ሁለቱ ተማሪዎች ማና ማን ነበሩ ?

ለ/ ተማሪዎቹ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?

ሐ/ በትምህርት ጎበዝና ተሽላሚ የነበረው የትኛው ተማሪ ነው?

መ/ ተማሪዎቹ ከምን ጀምረው እስከ ምን ድረስ እንደተነጋገሩ በቅደም ተከተል እየተነሳችሁ ለክፍል ተናገሩ፡፡

ማስታወሻ

እራሳችሁን ለክፍል ተማሪዎች በምታስተዋውቁበት ጊዜ የሚከተለውን ሂደት መጠበቅ ይኖርባችኋል፡፡

- ስማችሁን ከነ አባታችሁ መናገር
- እድሜያችሁን
- የመጣችሁበትን አካባቢ
- የክፍል ደረጃችሁን
- የምትወዱትን የትምህርት ዓይነት
- ወደ ፊት መሆን የምትፈልጉትን
- ወዘተ ….

**ተግባር 3. ከላይ የቀረበውን እራስን የማስተዋወቅ ቅድም ተከተል በመከተል መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ተግባር መሠረት እራሳችሁን ለክፍል አስተዋውቁ፡፡ በመቀጠልም ቀጥለው በቀረቡት ጥያቄዎች እራሳችሁን ገምግሙ፡፡**

ሀ/ በተማሪዎች ፊት ስቆም ፍርሃት ተሰምቶኝ ነበር?

ለ/ እራሴን ያስተዋወኩት ምንም ሳልጨነቅ ነበር ?

ሐ/ ሳልናገር ያለፍኩት ነገር ነበር?

መ/ በአጠቃላይ አቀራረቤን ስመለከተው መልካም ነበር?

## ሁለተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አራት

### ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡**

- የሚሰጣችሁን ምንባብ በትክክል ታነባላችሁ ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በትክክል ትሰራላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጭት ማለት ምን ማለት ነው ?
2. ግጭት የሚፈጠረው በምን ምክንያት ነው ?
3. ግጭትን እንዴት መፍታት ይቻላል?



## የጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት

የጋሞ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የግጭት አፈታት ስልት እንዳለው መረጃዎች ያሳያሉ።በግለሰቦች ይሁን በቡድኖች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በውይይት መፍታትና በሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖር ጋሞዎች ካሏቸው እሴቶች አንዱና ዋናው ነው። የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እንኳን በትናንሽ ችግሮች ላይ እና በከፍተኛ ሁኔታ በአገር ደረጃ የሚከሰት ችግር እንኳን ቢኖር የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ትልቁ ሚናቸው መሆኑን የውጪ ፀሐፊዎችም ጽፈውላቸዋል።Boeg (2006) እና Freeman (2002) እንደሚገልጹት በጋሞ አካባቢ ያሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ብዙ ጊዜ በሀገሪቱ የመንግስት ለውጥ በተደረገበት ወቅት የተፈጠረውን ክፍተት

በመሙላት የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ሂደት ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳደረጉ ይገልፃሉ፡፡

በጋሞ ብሔረሰብ ዘንድ አብዛኞቹ ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱ ሲሆን ፣ብዙውን ጊዜ በአፈታት ሂደት ላይ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ በጋሞ ብሔረሰብ ሽማግሌዎች ስለሚከበሩ እነሱ የሚናገሯቸው ቃላቶች ይጠበቃሉ፣ የሚያዟቸው ትዕዛዞች ይፈጽማሉ ፣የሚወሰኑአቸውም ውሳኔዎች ይፀናሉ፡፡

በጋሞዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ችግር ቢከሰት ለምሳሌ ህይወት የሚያጠፋ ፣ንብረት የሚያወድም ፣ህብረተሰቡን የሚያፈናቅል ፣ወዘተ ግጭት ቢከሰት ሽማግሌዎች ምንም ለህይወታቸው ሳይፈሩ እርጥብ ሣር በእጃቸው ጨብጠው ፈጥነው ከግጭቱ መሀል ይገባሉ፡፡በመሀከልም ሆነው ተው እኛ ሽማግሌዎች በመኃል ገብተናል ይላሉ፡፡ማንም ቃላቸውን የሚጥስ የለም ፣ሁሉም ግጭቱን ወዲያው ያቆማል፡፡ሽማግሌዎች ሲናገሩ አንበሳ እንኳን ቢመጣ ሽማግሌዎች እርጥብ ሣር ይዘው ከለመኑት ይቆማል ፣ ወይም ይመለሳል እንጂ አንዳች ጉዳት አያደርስም ይላሉ፡፡በዚሁ መሰረት ነገሩ በሰላማዊ መንገድ በሽምግልና ተይዞ እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ በቅርብ ጊዜ በአርባ ምንጭ ከተማ ላይ የታየው የዚሁ ባህል አንድ መገለጫ ነው፡፡

(የጋሞ፣ የጎፋ ፣የአይዳ፣ የዘይሴ እና የጊዴቾ ብሔረሰቦች የግልና የጋራ እሴቶች 2008 ተሻሽሎ የቀረበ)

**ተግባር1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ በቃል መልሱ፡፡**

1. ግጭትን በባህላዊ መንገድ ለሽማግሌዎች ሰጥቶ መፍታት ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?
2. በጋሞ ብሔረሰብ የሽማግሌዎችን ቃል ማክበርና የወሰኑትን ውሳኔ መቀበል ለአሁኑ ትውልድ ምንን ያስተምራል ትላላችሁ?

3. ግጭቶችን ሁሉ ወደ ፖሊስ ጣቢያና ወደፍርድ ቤት ይዞ ከመሮጥ ያለምንም ድካምና ልፋት በአካባቢው ሽማግሌዎች ነገሩን እዚያው መፍታት ጥሩ ነው ትላላችሁ?
4. ግጭት እንዳይከሰት ቀድሞ መሰራት ያለበት ነገር ምንድነው ትላላችሁ?
5. የጋሞ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ስርአት እንዴት ተወዳጅ ሊሆን ቻለ?
6. ብዙ ብሔረሰቦች የግጭት አፈታት ስርአት ቢኖራቸውም የሽማግሌዎቹን ቃል ተተኪው ትውልድ ስለማይሰማና የወሰኑትን ውሳኔ ስለማያከብር እነዚህ ባህላዊ ዕሴቶች እየቀሩ ሄደዋል፡፡እነዚህን ዕሴቶች ወደ ቦታቸው ለመመለስ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**ተግባር 2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጠው አማራጭ ትክክለኛውን መልሰ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት

ሀ/ በሰላም ለመኖር ይረዳል፡፡

ለ/ አብሮ ተቻችሎ ለመኖር ይረዳል፡፡

ሐ/ያስተዳደር ችግር ክፍተቶችን ይሞላል፡፡

መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

2. በጋሞ ብሔረሰብ ውስጥ ግጭትን በባህላዊ መንገድ በመፍታት ዙሪያ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት-------------- ናቸው፡፡

ሀ/ ወጣቶች ለ/ ሴቶች ሐ/ ወንዶች መ/ ያገር ሽማግሌዎች

3. የጋሞ ያገር ሽማግሌዎች ግጭትን ለማብረድ በግጭት መሀከል ሲገቡ የሚይዙት ነገር ----------- ይባላል፡፡

ሀ/ መሣሪያ ለ/ እርጥብ ሣር ሐ/ጦርና ቀስት መ/ሁሉም

4. ሽማግሌዎች የት ሆነው ነው ግጭትን የሚያበርዱት?

ሀ/ በቤታቸው በመሆን ለ/ በሽምግልና ቦታ ተቀምጠው

ሐ/ በግጭቱ መሀል ገብተው

መ/ ግጭቱን በመሣሪያ አስቁመው

5. ከጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት ምን እንማራለን?

   ሀ. መከባበርን        ለ/ የራስ ችግርን በራስ መፍታትን

   ሐ/ ችግሮችን ሳይባባሱ በአጭር ማስቀረትን  መ/ ሁሉምመልስ ነው

**ከላይ የቀረበውን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ አንብባችኋል፣ እናንተ ደግሞ ከዚሁ ባህላዊ የግጭት አፈታት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት አፈላልጋችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አምጥታቸሁ አንብቡላቸው።**

**ተግባር3 ቀጥለው የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው። ስለዚህ በምንባቡ መሰረት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ፃፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ ችግር | ሐ/ ስልት | ሠ/ ደህንነት |
| ለ/ እርጥብ ሳር | መ/ ግጭት | ረ/ ሽማግሌዎች |

## ሁለተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አምስት

## አንብቦ መረዳት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የሚቀርብላችሁን መመሪያ አንብባችሁ ተግባራዊ ታደርጋላችሁ ።
- ትእዛዞችን አንብባችሁ ትፈጽማላችሁ።

### መመሪያዎችና ትዕዛዞችን  አንብቦ መተግበር




ስዕል 1




ስዕል 2

ሀ. ከላይ የቀረበውን ስዕላዊ መግለጫ በጥንድ በመሆን ተመልክታችሁ ምን አይነት መልዕክት ወይም መመሪያ እንደሚያስተላልፍ ተናገሩ።

ለ..በስዕሉ ላይ የተገለጹት መመሪያዎችና ትዕዛዞች ጠቀሜታ አላቸው ብላችሁ ታሳባላችሁ?

ሐ. በአሁኑ ሰአት ከፍተኛ ትኩረት የሳበውና በብዙ ሰው ዘንድ ተግባራዊ የሚደረገው የትኛው ትዕዛዝ ነው? ለምን ይመስላችኃል?

መ. አንድን መድሃኒት የሚጠቀም ሰው የተነገረውን ትዕዛዝ ወይም ከመደሃኒቱ ጋር የተሰጠውን መመሪያ ወረቀት ባይመለከትና በራሱ አስተሳሰብ መድሃኒቱን ቢጠቀም ጉዳት ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

**ተግባር1 ከዚህ በታች የቀረቡትን መመሪያዎችንና ትዕዛዞች አንብባችሁ በቡድን በመሆን ትዕዛዝ የሆነውን በትዕዛዝ ቦታ፣መመሪያ የሆነውን በመመሪያ ቦታ ፃፉ፡፡**

1. እጃችሁን አውጡ፡፡
2. መጥረጊያ ለመስራት፣ መጀመሪያ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል፡፡
3. ተማሪዎች ክፍላችሁን ስታፀዱ አቧራ በአፍንጫችሁ እንዳይገባ አፍና አፍንጫችሁን መሸፈን ያስፈልጋችኋል፡!
4. ቶሎ ወደ ቢሮ በመሄድ፣ ጥቁር ሰሌዳ ማጥፊያ ይዘህልኝ ና !

5. እጃችሁን አውጡ!
6. ተማሪዎች ክፍላችሁን ስታፀዱ አቧራ በአፍንጫችሁ እንዳይገባ አፍና አፍንጫችሁን መሸፈን ያስፈልጋችኋል፡፡
7. ቶሎ ወደ ቢሮ በመሄድ፣ ጥቁር ሰሌዳ ማጥፊያ ይዘህልኝ ና !
8. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኂላ እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ ፡፡
9. አሁን ወደ ሱቅ ሂደህ አንድ ኪሎ ቡናና አንድ ኪሎ ስኳር ይዘህ ቶሎ ና !
10. ወንድምህን ቶሎ ወደዚህ እንዲመጣ ንገረው !

11.እነዚህን መድሃኒቶች ስትጠቀም መጀመሪያ ምግብ መብላትህን አረጋግጥና ከበላህ በኃላ በውሃ ዋጣቸው፤በለስላሳ ብትውጣቸው ግን ጥሩ አይደለም።

**ተግባር 2. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ትዕዛዛዊ ዐረፍተ ነገር መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

| | |
|---|---|
| ሀ አመጣ | ሰ/አስረዳ |
| ለ/ ተናገረ | ሸ/ አስተላለፈ |
| ሐ/ አሳየ | ቀ/ አካፈለ |
| መ/ አዳምጥ | በ/ ብላ |

**ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**መፃፍ**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ

- አያያዥ ቃላትን በትክክል ትጠቀማላችሁ።
- ነጠላ ዐረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት ታጣምራላችሁ፡፤
- ስለ አንቀጽ ምንነት ታብራራላችሁ፡፤

**ማስታወሻ**

አያያዥ ቃላት የምንላቸው ቃልን ከቃል፣ሀረግን ን ከሀረግ እንዲሁም ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር የሚያያይዙ ወይም የሚያጣምሩ ናቸው።

**ምሳሌ፡-** እና፣ ወይም፣ ነገር ግን፣ ምክንያቱም ወዘተ...

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት እና ሐረጋት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አጣምሯቸው።**

ምሳሌ ከገበያ ሎሚ <u>ወይም</u> ሙዝ እገዛለሁ።

ማርቆስ <u>ና</u> አለሙ መጡ ።

1. በረኃ -------------------አባቱ

2. ቁጭ አለ-------------------ስለደከመው፡፡
3. በላ ------------------------ሄደ፡፡
4. ብር -------------------------ምግብ
5. በላሁ ----------------------አልጠገብኩም፡፡
6. ሣቅ ------------------------ ለቅሶ
7. ብርትኳን ---------------------ሙዝ
8. ተኝቷል -------------------ደከሞታል፡፡
9. ወፍ ጮኂል --------------------- አልነጋም ፡፡
10. ቀልቷል ---------------------------በስሏል፡፡

**ተግባር 2. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ወደ አንድ ዐረፍተ ነገር ቀይሩ፡፡**

1. አበበ ቁርሱን በላ፡፡
2. ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡
1. ሁለቱም ልጆች አይነጋገሩም፡፡
2. ትላንት ተጣልተዋል፡፡
1.ከገበያ ልግዛልህ፡፡
2. ከሱቅ ልግዛልህ፡፡
1. ከትምህር ቤት መጥተሀል፡፡
2. እኔና አንተ አልተገናኘንም፡፡

**ተግባር 3.ከላይ በሰራችሁት ተግባር መሰረት አምስት ዐረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት አጣምራችሁ በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡፡**

## ሶስተኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ሰባት

## ስዋስው

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች**

- ባለቤትና ተሳቢን ከዐረፍተነገር ውስጥ ታወጣላችሁ ፡፡
- በዐረፍተነገር ውስጥ ማሰሪያ አንቀጽን ትጠቀማላችሁ፡፡

- ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ታዋቅርላችሁ፡፡

**ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ**

**ማስታወሻ**

ባለቤት፡- በዐረፍተ ነገሩ የተጠቀሰውን ድርጊት የሚፈጽመው ወይም እንዲፈፀም የሚያደርገው ቃል ወይም ሐረግ ነው፡፡

ተሳቢ፡- በዐረፍተ ነገሩ የተጠቀሰው ድርጊት የሚያርፍበት ወይም የሚፈፀምበት ነው፡፡

ማሠሪያ አንቀጽ ፡- ዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ የሚገባ ድርጊት አመልካች ነው፡፡

**ተግባር1. ከስር የቀረበውን ምሳሌ በደንብ በመመልከት ቀጥሎ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ ባለቤት ፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ከፋፍላችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ/ አርጊቴ ውሻውን መታችው፡፡

ባለቤት - አርጊቴ = ድርጊት ፈፃሚ ናት፡፡

ተሳቢ - ውሻውን = ድርጊቱ ያረፈበት

ማሰሪያ አንቀጽ - መታችው= የድርጊቱ ዓይነት ና የዐረፍተ ነገሩ መዝጊያ ነው፡፡

ለ/ ሾይጫ ምሳውን በላ፡፡

ባለቤት - ሾይጫ

ተሳቢ - ምሳውን

ማሰሪያ አንቀጽ - በላ

1. ቡሴራ ከብቶቹን ነዳ፡፡
2. አመርጋ በሬ ገዛ ፡፡
3. ሲልቱ እንጀራ ጋገረች፡፡
4. አይካ አንበሳ ገደለ ፡፡
5. ላምቤቦ ድንች ተከለ ፡፡

**ተግባር 2. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በማገናኘት ዐረፍተ ነገር አዋቅሩ፡፡**

አየለ ያዘ ምሳሌውን

| | | |
|---|---|---|
| መሐመድ | በላ | ሚዳቋ |
| ባርጂን | ቀቀለ | ውሃ |
| ካንሶ | ቀዳ | ንፍሮ |

## ሶስተኛ ሳምንት፡ ክፍለ ትምህርት ስምንት

### መናገር

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- የቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡
- ውይታችሁን በንግግር ታቀርባላችሁ፡፡
- ንግግር ታቀርባላችሁ፡፡





**ተግባር1.** ከላይ የቀረበውን ስዕል ተመልክታችሁ ቀጥሎ የቀረቡትንጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ/ ከሁለቱ ቡድን በሥርዓት ውይይት እያካሄደ ያለው የትኛው ቡድን ነው?

ለ/ ከስዕሉ እንደምትረዱት ውይይት ትኩረት የሚፈልግ ተግባር ነው?

ሐ/ ለውይይት የሚሆን ርዕስ ማዘጋጀት የመጀመሪያ ሥራ መሆኑን ታውቃላችሁ ?

መ/ ውይይት ማድረግ ምን ጠቀሜታ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

**ተግባር 2. እራሳችሁን በቡድን በማደራጀት የኮረና ቫይረስ በሽታ በሰዎችና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ ተወያይታችሁ ለክፍሉ አቅርቡ፡፡**

**ተግባር 3** በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ተሰብሳቢዎቹ እንዴት ውይይት እንደሚያካሂዱ መረጃ ሰብስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፦ ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ**

***ሥነ - ጽሁፍ***

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- አፈታሪኮችን ፈልጋችሁ አደራጅታችሁ መናገር ትችላላችሁ፡፡
- ታሪኮችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታቀርባላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

አፈታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንዱን ገጽታ በመውሰድ ስነ ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡

**ተግባር1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸውና ምላሻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ/ አፈታሪክ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?

ለ/ አፈታሪኮችን ማን እንደተናገራቸው ፣መቼ እንደተነገሩ ማወቅ ይቻላል?

ሐ/ በአካባቢያችሁ የሚነገሩ አፈታሪኮች ካሉ ጥቀሱ፡፡

**ተግባር2 . የሚከተለውን አፈታሪክ አንብቡና ከታሪኩ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ስሩ ፡፡**

**ሰጎን**

ሰጎን በአገራችን በስፋት የምትገኝ ትልቋ የወፍ ዝርያ ነች፡፡በአብዛኛው የምትገኘው በሞቃታማ ስፍራ ሲሆን ምግብ በደንብ ለማግኘት የሚመቻትን ሥፍራ ትመርጣለች፡፡ስጎን ከማንኛውም እንስሳ በተለየ አንገቷ ረጅም ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከእለታት በአንድ ቀን ሰጎን ውሃ ልትጠጣ ወደ

ወንዝ ሄዳ አዞን ወንዝ ዳር ታገኘዋለች፡፡ ከዚያም አዞው ሞትኩ እያለ ያለቅሳል፡፡ ሰጎንም ምን ሆነህ ነው ትለዋለች፡፡ አዞውም እባክሽ ጥረሴን አሞኝ እየተሰቃየሁ ነው ይላታል፡፡ ሰጎኗም በጣም ታዝንለታለች፣ ከዚያም አዞ እባክሽ አንድ ነገር ብቻ እርጂኝ ይላታል፡፡ እሷም በጣም እቸኩላለሁ ትለዋለች፡፡ ግድየለሽም እኔም ብዙ አላስቸግርሽም፤ አፌ ውስጥ ገብተሽ የትኛው ጥርሴ ብቻ እንደታመመ አይተሽ ንገሪኝ ይላታል፡፡ እሷም የታመመውን ጥርስ ብቻ ለማየት ከሆነ ምንም ችግር የለውም ብላ አፉን ከፈተላትና ለማየት አንገቷን ወደ ውስጥ አስገብታ ለመመልከት ስትጀምር አዞ አፉን ዝግት አደረገና ጭንቅላቷን ይዞ ወደ ወንዝ ይጎትታት ጀመረ፡፡ እሷም ወደ ወንዙ እንዳይጎትታትና እንዳይበላት ያለ የሌለ ሀይሏን አጠራቅማ ወደ ኋላ ትታገል ጀመረች፡፡ በዚህ ጊዜ አዞው ሲስባት እሷ ወደኋላ ስትስብ አንገቷ እየረዘመ እየረዘመ መሄድ ጀመረ፡፡ ከዚያም ከብዙ ትግል በኋላ አንገቷን ስታስለቅቅና ሸሽታ ስታመልጥ አንገቷ በጣም ረዝሞ ነበረ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሰጎን አንገት ረጅም ሆኖ ቀረ፡፡

ሀ/ የሰጎን አንገት ረጅም ነው ወይስ አይደለም ?

ለ/ አንገቷ የረዘመበት ምክንያት ትክክለኛ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?

ሐ/ በውስጡ ግን አስተማሪ የሆነ ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ ?

መ/ ከታሪኩ ውስጥ እስቲ ሁለት ጠቃሚ ና አስተማሪ ናቸው የምትሏቸውን ሀሳቦች አውጡ ?

ሠ/ ጥንድ ጥንድ በመሆን አዞ ታመምኩ ያለበትን ምክንያትና ይህንን ዘዴ ለምን እንደተጠቀመበት ተወያዩበት ፡፡

**ተግባር 3.** ከላይ በቀረበው አፈታሪክ ብዙ ነገሮችን ተምራችኋል፡፡ ምንም እንኳን አፈታሪክ ሙሉ በሙሉ እውነት ባይሆንም ብዙ አስተማሪ ነገሮች እንዳሉት ለማየት ችላችኋል፡፡ በዚሁ መሰረት በአከባቢያችሁ ከሚነገሩ አፈታሪኮች አንዱን በመውሰድ የታሪኩን ሂደትና በውስጡ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚሁ ምዕራፍ እራስን እንዴት ማስተዋወቅ እንደሚቻል ተምራችኋል። በመቀጠልም እንዴት ውይይት እንደምታደርጉ ስለ ውይይት ተምራችኋል። የተለያዩ መመሪያዎችንና ትእዛዞችን አንብባችሁ እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርጉና መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን መለየትን አውቃችኋል። አያያዥ ቃላት የምንላቸው ቃላትን፣ ሀረጋትን ፣ ዐረፍተ ነገሮችን ፣የሚያይዙ እንደሆኑና ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑ አንደ ፦ እና ፣ወይም ፣ነገርግን፣ ምክንያቱም ፣የሚሉትን ምሳሌዎች ተመልክታችኋል። ስለ ጋሞ ቤሔረሰብ ግጭት አፈታት በምንባቡ ላይ ተምራችኃል። ከሱ ጋር ተያይዞ የባህላዊ እሴቶችን መጠሪያ አውቃችኋል። በስዋስው ክፍል ደግሞ ባለቤት ፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ በአረፍተ ነገር ውስጥ እንዴት እንደሚዋቀር የተማራችሁ ሲሆን በመጨረሻም ስለ አፈታሪክ ምንነት አውቃችኋል።

**ቀጥሎ የቀረቡትን የማጠቃለያ ጥያቄዎች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

1. መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን ማንበብና መረዳት ያለውን ጠቀሜታ ሰፋ አድርጋችሁ በጽሁፍ ግለፁ።
2. ከተማራችኋቸው አያያዥ ቃላት ውስጥ ከመጽሐፍ ፈልጋችሁ ተጨማሪ አምስት አያያዥ ቃላት ፃፉ።
3. ባለቤት ፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አምስት ነጠላ ዐረፍተ ነገሮች ጽፋችሁ አቅርቡ ።

ምዕራፍ ሶስት

የሴቶች ሚና

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የክርክሮችንና የውይይቶችን ሀሳብ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ውስብስብ (ጠንካራ ) ቃላትን በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- የእለት ተእለት እንቅስቃሴ መረጃችሁን ትጽፋላችሁ፡፡
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ታዛምዳላችሁ ፡፡
- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ ፡፡
- በአያያዥ ቃላት ዐረፍተ ነገር ታጣምራላችሁ ፡፡
- ሥነ-ጽሑፋዊ ምንባቦችን አንብባችሁ ትረዳላችሁ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| አመለካከት | በራስ መተማመን |
| አዳሪ | ፍላጎት |
| መብት | ማዕከል |

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የክርክር ሂደትን ተከትላችሁ ክርክር ታቀርባላችሁ ፡፡
- ጭውውትን በማዳመጥ ጭውውት ታቀርባላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ክርክር አንድን ሀሳብ በመያዝ ያንን ሀሳብ ደግፈንም ይሁን ተቃውመን በአንድ በኩል በመቆም ሀሳባችንን ለማስረዳትና አድማጭን ለማሳመን የምናደርገው ጥረት ነው ።

**ተግባር1.** ከታች የቀረቡትን አማራጭ ርዕሶች በመመልከት ለክርክር ይመቸኛል፤ መረጃ አገኝበታለሁ፤ የምትሉትን አንዱን ርዕስ በመምረጥ ክርክር አቅርቡ።

1. ሴቶች ዕድል እንጂ ችሎታ አላጡም ።
2. ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል ።
3. ፖለቲካና ኤሌትሪክ በሩቁ ነው ።
4. አገር ወይስ ህዝብ ይቀድማል ?
5. አስተሳሰብና አመለካከት አንድ ናቸው ?

**ተግባር2.** ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ክርክሩን የሚዳኙና የሚመሩ አካላትን ምረጡ። የምትመርጡትም ዳኛ፣ ፀሐፊና ሰዓት ተቆጣጣሪ ነው።

**አንድኛ ሳምንት ፦ ክፍለ ትምህርት ሁለት**

**ስዕልን ተመልክቶ ማብራራት**

ስዕል 1 ስዕል 2





**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ስዕል አንድንና ስዕል ሁለትን እያነፃፀራችሁና እያወዳደራችሁ በስዕሉ ላይ ያለውን ሀሳብ ግለፁ፡፡**

ሀ. ስዕል አንድ ስለምንድነው የሚገልፀው ?

ለ. ስዕል ሁለት ስለምንድነው የሚገልፀው ?

ሐ. በስዕል አንድና በስዕል ሁለት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው ?

መ. ከፍተኛ ሚናና ኃላፊነት ያለው በየትኛው ስዕል ላይ ነው ?

ሠ. በሁለቱ ስዕሎች መካከል መስተካከል አለበት የምትሉት ነገር አለ ?





ስዕል 1 ስዕል 2

**ተግባር 2. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ ፡፡**

ሀ. ስዕል አንድ ምንን ያሳያል ?

ለ. ስዕል ሁለት ምንን ያሳያል ?

ሐ. በስዕል አንድና በስዕል ሁለት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው ?

መ. ከሁለቱ ስዕሎች የትኛው ስዕል ነው ጥሩ መልዕክት የሚያስተላልፈው?

## አንደኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ሶስት

### ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ምንባቦችን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ከምንባብ የሚወጡ ጥያቄዎችን ትሠራላችሁ፡፡
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ትናገራላችሁ ፡፡

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ሴቶች በትላልቅ ኃላፊነቶች ላይ መቀመጥ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. ሴቶች በስራቸውም ሆነ በኃላፊነታቸው ከወንዶች እኩል ስራቸውን የመፈፀም አቅም አላቸው ?

ሐ. አካል ጉዳተኛ ሴቶች እንደማንኛውም ሰው ተምረው ትልቅ ደረጃ መድረስ ይችላሉ ?



### የትነበርሽ

የትነበርሽ የተወለደችው በ1975 ዓ.ም በአማራ ሳይንት አከባቢ ሲሆን በተወለደች በአምስት ዓመቷ የዓይን ብርሃኗን አጣች፡፡ እናቷ ለአይን ህክምና

ወደ አዲስ አበባ ቢያመጧትም ምንም ለውጥ ማምጣት አልተቻለም። ሆኖም ስድስት ዓመት ሲሞላት እናቷ ወደ ሻሸመኔ የዓይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት ላኳት። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷንም የተማረችው በዚሁ ትምህርት ቤት ነበር ። ስድስተኛ ክፍልን እንደጨረሰች በራስ መተማመኗን እንደያዘች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመማር ወደ አዲስ አበባ ሄደች።

የትነበርሽ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ 12ኛ ክፍል ማየት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር ተምራለች። በዚያ ጊዜ ውስጥ የክበባት መሪ በመሆንና የተማሪዎች መማክርት ፕረዘዳንት በመሆንም ሠርታለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትጨርስ ዲግሪ ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባች ። ለሰዎች መብት መከበር በነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የህግ ትምህርት ለማጥናት ወሰነች። የህግ ትምህርቷን በማጥናት ሰዎች እኩል መብቶች እንዳሏቸው ተረዳች ። በዚህም የአካል ጉዳተኛና የችግረኛ ሰዎችን መብቶች ለማስከበር ወሰነች ። በዚሁ መሠረት በ1998 ዓ.ም በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪዋን እንደጨረሰች የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኝነትና ልማት ማዕከልን በማቋቋም ሂደት በንቃት ተሳተፈች። ምኞቷን እውን ለማድረግ ጥረቷን ቀጠለች። በማዕከሉም ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ሆና እየሠራች ነው።

ልበ ብርሃኗ የትነበርሽ ባበረከተችው ከፍተኛ አስተዋፅኦ በሀገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሽልማቶችን አግኝታለች ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ አገልግሎት የትምህርት መስክ ሁለተኛ ድግሪዋን ይዛለች ። ባለትዳርና የሁለት ሴት ልጆች እናት የሆነችው ይቺ ወጣት አሁንም የተዘነጉ ወገኖች መብት እንዲከበር በመታገል ላይ ትገኛለች ። አካል ጉዳተኞች ጠንካሮችና ራዕያቸውን ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን እያሳየች ነው ።

(ሲዳ ፡፡ 2010 ኢዱኬሽን ጀንደር ኢኳሊቲ ገጽ 1-7 ተሻሽሎ የተወሰደ )

**ተግባር1. ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ ።**

ሀ. የትነበርሽ የዓይን ብርሃኗን ያጣችው ገና ስትወለድ ነበር ።

ለ. ወደ ዓይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት የመጣችው ስድስት ዓመት ሲሞላት ነበር።

ሐ. እሷ ባበረከተችው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምክንያት በርካታ ሽልማቶችን ማግኘት ችላለች።

መ. የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞችና ለተዘነጉ ወገኖች ምሳሌ ልትሆን ትችላለች ።

**ተግባር 2. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን አማራጭ በመምረጥ መልሱ ።**

1. የትነበርሽ የህግ ትምህርቷን ለመማር የወሰነችው ለምን ነበር ?

   ሀ. ለሰዎች መብት መከበር ከነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ፣

   ለ. በጓደኞቿና በቤተሰቦቿ ከፍተኛ ጫና ስለነበረባት፣

   ሐ. ከልጅነቷ ጀምሮ በሚደርስባት ተጽዕኖ ምክንያት፣

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

2. የትነበርሽ በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘችው መች ነበር?

   ሀ. በ1998 ሐ. 1999

   ለ. በ2004 መ. 2006

3. የትነበርሽ ሁለተኛ ዲግሪዋን የያዘችው በየትኛው መስክ ነበር ?

   ሀ. በአከባቢ ሳይንስ ሐ. በአከባቢ ጥበቃ

   ለ. በማህበራዊ አገልግሎት መ. መልሱ አልተሰጠም

4. የአካል ጉዳተኝነትና ልማት ማዕከል በመቋቋሙ ምክንያት

   ሀ. ምኞቷን እውን አድርጋለች ።

   ለ. ጥረቷን አሳክታለች ።

   ሐ. የሌሎችን መብት ማስከበር ችላለች ።

   መ. ሁሉም መልስ ነው።

## ሁለተኛ ሳምንት ፦ ክፍለ ትምህርት አራት

### መናገር

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ስለ ራሳችሁ ታሪክ ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር 1. ቀጥሎ በቀረበው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ስራችን እንጀራችን መሆኑን ማወቅ አለብን ፡፡
2. ገና ሲያየኝ ውሃ ሆነ ፡፡
3. ውሃ መጠጣት ለሕይወታችን አስፈላጊ ነው፡፡
4. ትናንትና ሴትዮዋ እንስራ ሙሉ ውሃ ደፋች ፡፡
5. አገራችን እንድታድግ ጠንክረን እንስራ አሉ ተሳታፊዎች ፡፡
6. ቀና አመለካከት ያለው ሰው ጠቃሚ ነው፡፡
7. አለሙ በሚስቱ ቀና ፡፡
8. የተጣመመው እንጨት በሰዎች ብርታት ቀና እንዲል ተደረገ፡፡
9. ጠማማው ቀና ሰባራው ተጠገነ ፡፡
10. ህፃኑ ምሳውን እንጀራ በወጥ በላ፡፡

**ተግባር 2. ቀጥሎ የቀረቡትን ሀሳቦች በመመልከት ከቀረቡት ሀሳቦች አንፃር ስለራሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ ፡፡**

- የምትኖሩበት አከባቢ ገጽታ ምን ይመስላል?
- በህይወታችሁ ደስ የተሰኛችሁበት ነገር ምንድነው ?
- በቂ ገንዘብ ብታገኙ ማድረግ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- እንዲህ ማድረግ ያስደስተኛል የምትሉት ነገር ካለ ግለጹ፡፡

**ተግባር 3. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከአንድ በላይ ቀጥተኛ ፍች አላቸው ፍቺያቸውን አስባችሁ ፃፉ ።**

| ቃል | ቀጥተኛ ፍች |
|---|---|
| 1. ሄደ | |
| 2. ሰረቀ | |
| 3. በላ | |
| 4. አስተማረ | |
| 5. ልብ | |

## ሁለተኛ ሳምንት፥ ክፍለ ትምህርት አምስት

**መፃፍ**

**የእለት ተእለት ማስታወሻ መፃፍ**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

*ዕለታዊ ማስታወሻ ምን እንደሆነ ታብራራላችሁ።*

*ዕለታዊ ማስታወሻችሁን ትፅፋላችሁ ።*

*ማስታወሻ*

*የእለት ተእለት ማስታወሻ ማለት አንድ ሰው በየቀኑ በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚሠራቸውን፣ የሚፈፅማቸውን ተግባራት ያጋጠሙትን ነገሮች ( መልካምም ይሁን መጥፎ ) ወዘተ በማስታወሻ የሚፅፍበት ሂደት ነው ።*

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን የአንድ ተማሪ የእለት ተእለት ማስታወሻ አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኋላ አንድ የራሳችሁን የእለት ተእለት ማስታወሻ ፃፉ ።**

ቀን 04/01/2014

ዛሬ ከቤት የወጣሁት በጧት ነው ። ቤተሰቦቼም ከመኝታቸው ገና ስላልተነሱ ቁርሴን የመብላት አጋጣሚ አላገኘሁም። ቀጥታ ደብተሬን ይዤ ወደትምህርት

ቤት ሄድኩኝ ፡፡ አንድ ክፍል ውስጥ ገብቼ የቤት ስራዬን መስራት ጀመርኩኝ ፡፡ የቤት ስራዬን ሰርቼ ስጨርስ ተደወለና ተማሪዎች ገቡ፡፡ እኔም ወደ ክፍሌ በመግባት ትምህርቴን ቀጠልኩ ፡፡ ልክ 6፡15 ሲሆን ተደወለና ወደ ቤቴ ሄጄ ምሳዬን በላሁ፡፡ ከብቶችን እንድጠብቅ ተነገረኝና እስከ 12 ሰዓት ስጠብቅ ቆይቼ ወደቤት ተመለስኩ ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ያጋጠመኝ ክፉ ነገር አልነበረም፡፡

**ተግባር 2. ቀጥሎየቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ ፡፡**

ሀ. የእለት ተእለት ማስታወሻ ማለት ምንድነው ?

ለ. የእለት ተእለት ማስታወሻን ማንም ሰው ሊጽፈው ይችላል ?

ሐ. የእለት ተእለት ማስታወሻ ለምን ይጠቅማል ?

መ. ወደፊት የእለት ተእለት ማስታወሻ እያደገ ሲሄድ ወደ መጽሐፍነት ሊቀየር ይችላል ትላላችሁ? የራሳችሁን አስተያየት ስጡ፡፡

**ተግባር 3 . ከላይ በቀረበላችሁ ጽሑፍ መሠረት የእለት ተእለት ማስታወሻችሁን በመፃፍ ወደ ክፍል አምጥታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው ፡፡**

## ውስብስብ ቃላት

**ተግባር 4. ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት በምዕላድ ከፋፍላችሁ አስቀምጡ፡፡**

1. ኢትዮጵያዊነት
2. ትክክለኝነት
3. ብልፅግናችን
4. አካሄዳቸው
5. ጠባብነት
6. ማወቃችሁ
7. ሰብአዊነት

## ሁለተኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፦**

- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ታዛምዳላችሁ፡፡
- ቃላትን ተመሳሳያቸውንና ተቃራኒያቸውን ታወጣላችሁ፡፡

**ተግባር 1. በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳያቸውን ፈልጋችሁ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሀቅ | ሀ. ፈፀመ |
| 2. ልፋት | ለ. ገንዘብ |
| 3. መናቅ | ሐ. ምሳሌ |
| 4. ስልት | መ. ቀማ |
| 5. ቃኘ | ሠ. ተመለከተ |
| 6. ባለጋራ | ረ. እውነት |
| 7. አርአያ | ሰ. ድካም |
| 8. ነጠቀ | ሸ. ብልሀት |
| 9. አከናወነ | ቀ. ጠላት |
| 10 ሀብት | በ. መጸየፍ |

**ተግባር 2. ከ "ሀ" በታች ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተቃራኒያቸውን ፈልጋችሁ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መነሻ | ሀ. ለስላሳ |
| 2. በለፀገ | ለ. ቋሚ |
| 3. ችኩላ | ሐ. ዘመናዊ |
| 4. አያሌ | መ. ሽንፈት |
| 5. ድልብ | ሠ. መድረሻ |
| 6. ቆጣቢ | ረ. እርጋታ |
| 7. ከርዳዳ | ሰ. ደኸየ |
| 8. ጊዜያዊ | ቸ. ጥቂት |
| 9. ድል | ቀ. ከሲታ |

10.ጥንታዊ                    በ. አባካኝ

**ተግባር3. ቀጥሎ ላሉት ቃላት ተመሳሳያቸውና ተቃራኒያቸው ተቀምጦላቸዋል ፡፡ በነዚህ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት ዐረፍተነገር መስርቱ ፡፡**

| ቃል | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|
| 1. ሀቅ | እውነት | ሐሰት |
| 2. ባለጋራ | ጠላት | ወዳጅ |
| 3. መጨረሻ | መድረሻ | መነሻ |
| 4. ወደደ | አፈቀረ | ጠላ |
| 5. ብዙ | አያሌ | ትንሽ |

**ሶስተኛ ሳምንት ፦ ክፍለ ትምህርት ሰባት**

**ነጠላና ድርብ ዐ.ነገር**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

ነጠላ ዐ.ነገሮችን አውቃችሁ ትመሰርታላችሁ፡፡

ድርብ ዐረፍተነገሮችን ታወጣላችሁ፡፡

ነጠላና ድርብ ዐረፍተነገርን ትመሰርታላችሁ፡፡

ማስታወሻ

- ነጠላ ዐረፍተነገር - አንድ ግስ ብቻ ያለው ሆኖ ሙሉ ሀሳብን መግለፅ የሚችል ሲሆን በውስጡ ባለቤትና ማሠሪያ አንቀፅን በወጥነት ይዞ ይመሠረታል ፡፡

ድርብ ዐረፍተነገር- ሁለት ግስ ያለው ሆኖ ሁለት ነጠላ ዐረፍተ ነገሮችን አጣምሮ የያዘ ነው ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ በመመልከት ከዚያ በታች የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም ነጠላ ዐረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

ምሳሌ ፡- 1 ባለቤት - ጡሜቦ

ግስ - መጣ

ነጠላ ዐረፍተ ነገር -ጡሜቦ መጣ ፡፡

2.ባለቤት ደራሮ

ተሳቢ ምሳዋን

ግስ - በላች

ነጠላ ዐረፍተ ነገር -ደራሮ ምሳዋን በላች ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በረሶ | ይሽለማል | ላሚ | ጎበዝ | ጥጃ |
| ወለደች እሱ | እሷ | አጠበ | ቁቱ | ዘነበ |
| በትምህርቷ | | ሄደ | | ወደ ቤት |
| ጎበዞች | ተማሪ | | ዝናብ | ልብሴ |

1. ቁቱ በትምህርቷ ጎበዞች
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________
5. ______________________
6. ______________________

**ተግባር 2.ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ በመመልክት ከታች የቀረቡትን ነጠላ ዐረፍተ ነገሮች በማጣመር ድርብ ዐረፍተ ነገር መስርቱ፡-**

ምስሌ 1. ሀ. ማቱሳላ ጎበዝ ነው ፡፡

ለ. ጨዋታ ያበዛል፡፡

ማቱሳላ ጎበዝ ነው ነገር ግን ጨዋታ ያበዛል፡፡

2. አበበ ምሳውን በላ ፡፡

ወደ ትምህርት ቤት ሄደ ፡፡

አበበ ምሳውን በላና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ ፡፡

1. ሀ. አይካ ልብሱን ለበሰ፡፡

    ለ. ጫማውን አደረገ ፡፡

2. ሀ. ፈተናው ቀላል ነበር ፡፡

    ለ. እኔ አልሰራሁትም ፡፡

3. ሀ. አንበሳ ስጋ ይወዳል፡፡

    ለ. በሬ ሳር ይበላል ፡፡

4. ሀ. ሰለሞን ጎበዝ ተማሪ ነው ፡፡

    ለ. ሰናይትን ያስጠናታል፡፡

5. ሀ. ሲቲና ገበያ ተላከች

    ለ. ሙዝና ብርቱካን ተወዷ.ል

6. ሀ.ሁሴን ከትምህርት ቤት ወጣ ፡፡

    ለ. ወደ ቤቱ ሄደ

**ተግባር 3 . ከላይ በሰራችሁት መሠረት በቡድን በመሆን አምስት ነጠላና አምስት ድርብ ዐረፍተነገሮችን አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

**ሶስተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ስምንት**

**ሥነፅሑፍ**

**ቀለል ያሉ ሥነፅሑፋዊ ምንባቦች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የቀረበላችሁን ምንባብ አንብባችሁ ትረዳላችሁ
- የሚቀርቡላችሁን ተረቶች መልዕክት ትናገራላችሁ
- አጫጭር ግጥሞችን ታነባላችሁ

**ተረት**

አንበሳ በፈጣሪው እንዲህ ሲል አማረረ፡፡ የአራዊት ሁሉ አለቃ አድርገህ ፈጥረህኝ እንዴት አውራ ዶሮን እንድፈራ ታደርገኛለህ፡፡ ጅብን ዝሆንን፣ ጎሽን የሚያካክሉ እንስሳት የማርበደብድ ጀግና እዚህ ግባ የማይባል አውራ ዶሮ ላይ መበርገጌን ቢሰማ ፍጥረት ሁሉ ጉድ አይልም ? አያ አንበሳ በዚህ ዓይነት ዘውትር ሲቆዝም ኖሮ አንድ ቀን ወደ ወንዝ ሲወርድ ዝሆንን ያገኘዋል፡፡

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ዝሆንን ልብ ብሎ ሲመለከተው ያለማቋረጥ ጆሮውን ያርገበግባል፡ ታድያ አንበሳ በጣም ተገርሞ አያ ዝሆን ፣ ለመሆኑ ካየሁህ ጀምሮ ጆሮህን ያለማቋረጥ የምታርገበግበው ለምንድነው ሲል ይጠይቀዋል። ዝሆንም ፣ አየህ ፣ይቺ ትንኝ ወደ ጆሮዬ ድንገት ብትገባብኝ ስለምትገለኝ እሷን ለመከላከል ነው ይለዋል።

አንበሳም ከዚያ ሰዓት ጀምሮ እንዲህ ሲል አምላኩን ይቅርታ ጠየቀ። ጌታዬ ይቅር በለኝ ይህን የሚያህል ግዙፍ እንስሳ ትንኝን የፈራ ፣ እኔ አውራ ዶሮ ብፈራ ምንም የሚያስደንቅ አይደልም። ለካስ ማማረሬ ያለ አግባብ ነው አለ።

**ተግባር 1. ከላይ የቀረበውን ተረት አንብባችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ ።**

ሀ. ተረቱን እየተናገረ ያለው ማነው?

ለ. አውራ ዶሮን የሚፈራው ማነው?

ሐ. ዝሆንን የሚያስፈራው ነገር ምንድነው?

መ. ዝሆን ችግር እንዳይደርስበት የሚያደርገው መከላከል ምንድነው ?

ሠ. አጠቃላይ የተረቱ መልዕክት ምን ነበር?

**ተግባር 2. ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

ሀ. አንበሳ ንግግሩን የጀመረው በምስጋናና የተሰጠውን ትልቅነት በመጥቀስ ነበር።

ለ. ትንኝ በጆሮው ከገባች ስለሚሞት አንበሳ ሁልጊዜ ይፀልያል ።

ሐ. አውራ ዶሮ አንበሳን የሚያስበረግገው በጉልበት ስለሚበልጠው ነው ።

መ. መጨረሻ ላይ አንበሳ የተፀፀተው ከሱ የበለጡ እንስሳትን ትንሽ ነገር እንደሚያስፈራቸው ስላወቀ ነው።

ሠ. ተረቱ የሚያወራው "በአንተ አትማረር ካንተ የበለጠ ችግር ያለበት አለና" ስለሚል ነገር ነው።

**ተግባር3 በአከባቢያችሁ ከሚነገሩ ተረቶች አንዱን በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና በሚያስተላልፈው መልዕክት ላይ ተወያዩበት ።**

## ሶስተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

### አረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት ማጣመር

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- አያያዥ ቃላትን ከነተግባራቸው ትዘረዝራላችሁ ፡፡
- ቃላትን በአያያዥ ቃላት ታያይዛላችሁ ፡፡
- ዐረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት ታጣምራላችሁ ፡፡

**ተግበር 1. ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በቡድን በመሆን አጥኗቸውና እንዴት ቃላትን ፣ ሀረጋትንና ዐረፍተ ነገርን እንደሚያያይዙ ተወያዩበት ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ስለሆነ | ሆኖም | ስለዚህ |
| እንጂ | ይሁንና | ይሁን እንጂ |
| በመሆኑ | ቢሆንም | |

**ተግበር 2. ከላይ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት በመምረጥ ቀጥለው የቀርቡትን ቃላት፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮችን አጣምሩ፡፡**

ምሳሌ- ምሳ አልበላሁም <u>ነገር ግን</u> አልራበኝም፡፡

1. ዝናብ የለም ________________ ሊመጣ ይችላል፡፡
2. ገንዘብ የለኝም ________________ ቢኖረኝ ሸሚዙን እገዛው ነበር፡፡
3. ምንም እንኳ በትምህርቱ ጎበዝ ________________ ማጥናቱን ግን አላቋረጠም ፡፡
4. ጥሩ አስተማሪ ያለን ________________ ጥናታችንን ማቋረጥ የለብንም ፡፡
5. በጣም የስራ ጫና አለብኝ ________________ ቤተሰቤን መርዳት አላቋርጥም፡፡

**ተግባር 3. ቀጥለው በቀረቡት አያያዥ ቃላት በመጠቀም ሁለት ሁለት ዐረፍተ ነገር መስርቱ ፡፡**

1. ስለሆነ ሀ. ________________________

    ለ. ________________________

2. ይሁንና ሀ. ______________________

ለ.

3. በመሆኑ ሀ. ______________________

ለ. ______________________

4. ስለዚህ ሀ. ______________________

ለ. ______________________

5. ይሁን እንጂ ሀ. ______________________

ለ. ______________________

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለክርክር ምንነትና ክርክር እንዴት እንደሚቀርብ ተምራችኋል፡፡ በመቀጠልም ስዕሎችን በመመልከት በስዕሉ ላይ የተገለፀውን ሀሳብ መግለፅ ችላችኋል ፡፡ ሌላው ምንባብ በማንበብ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል ፤በንግግር ክፍል ላይ የቃላት ዐውዳዊ ፍችንና የራሳችሁን ታሪክ ተናግራችኋል ፡፡ በተጨማሪም የእለት ተእለት ማስታወሻ አፃፃፍን ተምራችኋል፣ ስለውስብስብ ቃላት፣ ስለቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ፤ ፍች ፣ስለነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገር በዚህ ክፍል ትኩረት ሰጥታችሁ የተማራችሁት ነው፡፡

### የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በግል በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. ለክርክር የሚሆን ሀሳብ በምንመርጥበትና ለከርክሩ ቡድን በምናደራጅበት ጊዜ ቀድመን የምናስባቸው ነገሮች ምንድናቸው ?
2. የቃላት አውዳዊ ፍች የምንለው የትኛውን ነው ? አውዳዊ ፍች ከቀጥተኛው (መዝቀበ ቃላዊ) ፍች የሚለይበት አጋጣሚ አለው?
3. የእለት ተእለት ማስታወሻ መያዝ ጠቀሜታ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገር ልዩነታቸው ምንድነው ?
5. አያያዥ ቃላት ቃልን ከቃል ፣ሀረግን ከሀረግ ፣ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር የሚያጣምሩ መሆናቸው ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?

ምዕራፍ
አራት

አካባቢያችን

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ጭውውቶችን  አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፤
- ስለ አንድ አካባቢ በዝርዝር ትናገራላችሁ ፡፡
- የገረፍታ የንባብ ስልትን ተጠቅማችሁ መረጃ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለምን  እንዴት የሚሉትን ቃላት በጽሁፍ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ለሚጠብቁና ለሚላሉ ቃላት ፍቾ ትሰጣላችሁ፡፡
- ጸታን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን አምጥታችሁ ክፍል ውስጥ ታቀርባላችሁ፡፡
- ቃላትን  በቅድመ ቅጥያና በድህረ ቅጥያ ነጥላችሁ ታወጣላችሁ፡-
- ስርአተ ነጥቦችን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

| | |
|---|---|
| ንቅናቄ | ኘላስቲክ |
| ግንዛቤ | አካባቢ |
| ብክለት | ጥንቃቄ |

**አንደኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አንድ**

**ማዳመጥ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የጭውውቱን ሀሳብ አዳምጣችሁ ትረዳላችሁ፡፡
- ስላዳመጣችሁት ነገር መልሳችሁ ትናገራላችሁ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

ሀ/ የጥቅም ሰው ማለት ምን ማለት ነው?

ለ/ አንድን ሰው እኔ በደንብ አድረጌ አውቀዋለሁ፣ ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሐ/ “ ወሬ አትስማ ” ማለት ምን ማለት ነው?

**ተግባር 1 ቀጥሎ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ጭውውት ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ/ ጭውውቱ የቀረበው  በስንት ሰዎች ነበር?

ለ/ በድንገት ተነስታ" ስማ  ! ስማ ! እባክህ "ብላ ንግግር የጀመረችው ማነች?

ሐ/ ጭውውቱ ምንን መሰረት ያደረገ ነበር?

መ/ ከጭውውቱ መረዳት የሚቻለው ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

**አንደኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት ሁለት**

**ስለአካባቢ ተፈጥሮ መናገር**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ስላነበባችሁት ነገር መልሳችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ስለአካባቢ ጥበቃ ጥሩ ግንዛቤ ታገኛላችሁ፡፡

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ሀ.የአካባቢ ጥበቃ ስንል ምን ማለታችን ነው?

**የአካባቢ ጥበቃ**

ስለአካባቢ ጥበቃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከናወኑ ተግባራት ጥሩ ውጤት እያሳዩ መጥተዋል፡፡ ይህንኑ የአካባቢ ጥበቃ በማበረታታት ብዙ **ንቅናቄዎች** ተደርገዋል፡፡ የንቅናቄዎቹም አላማ የተፈጥሮ አካባቢዎችን ከጥፋት ለመጠበቅ ሲባል **ገንዛቤ** መፍጠር ነው፡፡ አካባቢያችን ጥበቃ ካልተደረገለት በተለያዩ ምክንያቶች ሊበከል ይችላል፡፡ ከነዚህም ብክለቶች ዋና ዋናዎቹ የአፈር ብክለት ፣የውሃ **ብክለት**፣የአየር ብክለት ናቸው፡፡ እነዚህም ብክለቶች የሚከሰቱት

ከኢንዱስትሪዎች በሚወጡ ፍሳሾች፣ ከሞተር ተሽከርካሪዎች በሚወጡ ጋዞች፣ወዘተ ነው፡፡

አካባቢያችንና የተፈጥሮ ሃብታችን በነዚህ ምክንያቶች ከተበከለ በኋላ የሰው ልጅም ሆነ ሌላውም **ህይወት** ያለው ፍጡር በህይወት መቀጠሉ ላይ አደጋ ይፈጥርበታል፡፡ ተክሎች ይጠፋሉ፤እንሰሳት ይሞታሉ፤አካባቢያችን በከፍተኛ ሙቀት ይሸፈናል፡፡ ይህ ደግሞ ህይወትን ለማስቀጠል ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ አካባቢያችንን ከብክለት ለመከላከል ከሰፈራችን ጀምረን ጥንቃቄና ጥበቃ ልናደርግ ይገባናል፡፡ ቀለል ባለ ሁኔታ ብክለትን ብንመለከተው በየእለቱ እየገዛን የምንጠቀምባቸው **የላስቲክ** እቃዎች (ኘላስቲክ) እነሱም አካባቢን በመበከል ደረጃ **አስተዋፃ** አላቸው፡፡ ከተጠቀምንበት በኋላ እንጥለዋለን ፣ስለማይበሰብስ መሬት ውስጥ ገብቶ ይቀመጣል፡፡ መሬቱም ለእርሻና ለልማት እንዳይሆን ይበክለዋል፡፡ ባጠቃላይ ያአገራችን ተፈጥሮ ሃብት የሚጠብቀው አካባቢያችንን ስንጠብቅ ነው፡፡ ከሰፈር ጀምረን አካባቢያችንን ከጠበቅን ሀገራችን ትጠበቃለች ፣ሀገራችንን ከጠበቅን አለማችን ትጠበቃለች፡፡

**ተግባር 1. ከላይ የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ምላሻችሁን ለክፍል ተናገሩ፡፡**

ሀ/ አካባቢ የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?

ለ/ የአካባቢ ጥበቃ ስንልስ ምን ምን ነገሮችን ያካትታል?

ሐ/ የአካባቢ ብክለት የሚከሰትባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው ?

መ/ አካባቢያችንን ክብክለት ለመታደግ ምን መደረግ አለበት ?

ሠ/ ሰፈራችንን ስንጠብቅ ሀገራችን ይጠበቃል፡፡ የሚለውን ሀሳብ ሰፋ አድርጋችሁ ግለፁት ፡፡

**ተግባር 2. ከላይ የቀረበውን ምሳሌ በሰራችሁት መሰረት እናንተ ደግሞ በአካባቢያችሁ ስላለው የደን መመናመንና የደን ጭፍጨፋ በቡድን በመሆን መረጃ አስባስባችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

## አንደኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ሶስት

### ምንባብ

ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች ፡-

- ❖ ምንባቡን በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- ❖ ምንባቡን በአንብባችሁት መሰረት አካባቢያችሁን ትጠብቃላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በፍጥነት በማንበብ በውስጡ ያለውን መረጃ ለቅማችሁ ለማውጣት ሞክሩ፡፡**

## የአካባቢ ንጽህና

በንጹህ አካባቢ መኖር አስደሳች ነው፡፡ ሆኖም በከተማዎች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው ቆሻሻ ምክንያት አካባቢያችንን ንጹህ ማድረግና ማሳመር ይበልጥ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ ማዘጋጃ ቤቶች ቆሻሻ የሚሰበስቡበት ዘዴ በማዘጋጀት መንገዶችን በንጽህና ለመያዝ ቢጥሩም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ መጠራቀሙ አልቀረም ፡፡ይህ ደግሞ ለዓይን የሚያስቀይም ከመሆኑም በላይ ለህብረተሰቡ ጤና ጠንቅ ነው፡፡ በየቦታው የተጠራቀሙ ቆሻሻዎች ለአይጦች ፣ለበረሮዎችና በሽታ አስተላላፊ ለሆኑ ነፍሳት ምቹ የመራቢያ ስፍራ ይሆናሉ፡፡ ይህን ሁኔታ ለማስወገድ እናንተ በበኩላችሁ ልታደርጉት የምትችሉት ነገር ይኖራል ? አዎን፣ መኖሪያ ቤታችሁንና ጊቢያችሁን ንጹህ፣ እንዲሁም ያልተዝረከረከ እንዲሆን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ንጹህ ቤት የሚኖራቸው በቂ ሀብት ያላቸው ሰዎች ናቸው ብለው ያስባሉ፡፡ ሆኖም የቤታችንም ሆነ የአካባቢያችን ንፁህ መሆን ያመለካከታችን ጉዳይ ነው፣ በዚህ ረገድ ተገቢውን አመለካከት ማዳበር ቤታችንን በንጽህና ለመያዝ ያነሳሳናል፡፡ በእርግጥም፣ቤትን በንጽህና መያዝ በእጅጉ የሚቻለው በቤተሰብ አባላት ንቁ አመለካከት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ቤታችንንና አካባቢያችንን በንጽህና በመያዝ እያንዳንዳችን ምን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደምንችል መመርመሩ ጥሩ ይሆናል፡፡ ብዙ ጊዜ ልጆች በመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ትተዋቸው የሄዱትን የቆሸሹ ልብሶች ወይም አንዳንድ የተዝረከረኩ እቃዎቻቸውን የሚያነሱት ወላጆች መሆናቸውን አስተውላችሁ

ታውቃላችሁ? እንደ በረት፣ ጎሮኖ፣ ጎተራ፣ መኝታ ቤት፣ ወዘተ ያሉ አንዳንድ ቦታዎች መጽዳታቸው ለጤንነት ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህ የቤት ውስጥ ጤንነትን የተሟላ ለማድረግ ቤተሰቡን በጠቅላላ የሚያሳትፍ ግልጽ የሆነ የጽዳት መርሀ-ግብር ማውጣት የእናትና የአባትን ሸክም ለማቃለል ይረዳል፡፡

**ተግባር2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. በየቦታው የተጠራቀመ ቆሻሻ የምን መራቢያ ሊሆን ይችላል?
2. ብዙ ጊዜ ልጆች መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ትተዋቸው የሄዱትን ልብሶች የሚያነሱላቸው እነማን ናቸው?
3. በንጹህ አካባቢ መኖር ያለው ጠቀሜታ ምንድነው ?
4. ቤትን በንጽህና መያዝ የሚቻለው እንዴት ነው ?
5. አከባቢያችንን በንጽህና ያለ መያዝ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድነው?

**ተግባር3 ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

**ማስታወሻ**

የገረፍታ ንባብ ወይም የፍጥነት ንባብ የምንለው ከአንድ ንባብ ወይም ጽሁፍ ውስጥ ስም ዝርዝር፣ነጠላ ሃሳብ ፣ወዘተ የምንፈልገውን ብቻ በፍጥነት ለይተን ለማውጣት የምንጠቀምበት የንባብ አይነት ነው፡፡ ነገር ግን ትኩረት ሰጥተን ወይም በጥልቀት የምናነበው አይደለም፡፡

ሀ/ከላይ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚዘረዘሩ ነገሮችን በፍጥነት ፈልጋችሁ አውጡ፡፡

ለ/ ቤትን በንጽህና ለመያዝ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከምንባቡ ውስጥ ለይታችሁ አውጡ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አራት**

**መፃፍ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ❖ መጠይቃዊ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ ትጠቀማላቸሁ፡፡

❖ መጠይቃዊ ቃላትን ትዘረዝራላችሁ ፡፡

## መጠይቃዊ ቃላት

**ማስታወሻ**

- መጠይቃዊ ቃላት የምንላቸው አንድን ጥያቄ ለመጠየቅ ስንፈልግ ስለ ነገሩ ምንነት፣ምክንያት፣እንዴትነት ፣ወዘተ የምንጠይቅባቸው ቃላት ሲሆኑ፣ ብቻቸውንም ሆነው ይሁን ከሌሎች ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮች ጋር በመሆን ጥያቄ ለመጠየቅ ያገለግሉናል፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን መጠይቃዊ ቃላት ተመልክታችሁ አገልግሎታቸውን በጽሑፍ ግለፁ፡፡**

| | |
|---|---|
| ምንድን | ማን |
| የት | ወዴት |
| የትኛው | ምን |
| ለምን | እንዴት |

**ተግባር 2. ከላይ የተዘረዘሩትን መጠይቃዊ ቃላት ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡**

ሀ/ ምን ሆነህ ነው ትናንት የቀረኸው?

ለ/ ----------------------ቶሎ አትመጣም ?

ሐ/----------------------- እንደሚሰራ ንገረኝ ?

መ/ ---------------------- ነው ዛሬ የመጣኸው?

ሠ/------------------------ ሄደህ ነበር ትላንትና ?

ረ/ ----------------------- ላንተ እንደሚሻልህ አይተህትመርጣለህ?

ሰ/----------------------ትፈልጋለህ ሻይ ወይስ ቡና ?

**ተግባር 3.ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ጭውውት ተመልክታችሁ በዚያ መሰረት መጠይቃዊ ቃላትን ተጠቅማችሁ በቡድን በመሆን ጭውውት አዘጋጁ።**

**ጭውውት**

ገጃቦ - ሰሞኑን የት ሄደህ ነበር ?

ዶሪ- ኧረ ! የትም አልሄድኩም ።

ገጃቦ - ታዲያ ! ለምን አላየሁህም ?

ዶሪ - በጣም ስራ በዝቶብኝ ነው።

ገጃቦ - ምንድነው የምትሰራው ?

ዶሪ - ከአባቴ ጋር እርሻ ላይ ነው የምሰራው።

ገጃቦ - እንዴት ? ከትምህርቱ ጋር አይከብድህም?

ዶሪ - በእርግጥ ሊከብደኝ ይችላል።

ገጃቦ - እንዴት ማድረግ ይሻልሃል?

ዶሪ- ሰአቱን ለማመቻቸት እሞክራለሁ።

## ሁለተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት አምስት

## ቃላት

**የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን ለይታችሁ ታወጣላችሁ።

**ተግባር1. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍች ለይታችሁ ፃፉ።**

**ምሳሌ፡- ጠላት** ሲጠብቅ መጥላት ፣ አለመውደድን ያሳይል።
ሲላላ ባላጋራን ያመለክታል ።

**አካፋ** ሲጠብቅ- በትንሹ ዝናብ መዝነብን
ሲላላ - የአሸዋ፣የአፈር፣ወዘተ መዛቂያ

| **ቃል** | **ሲጠብቅ** | **ሲላላ** |
|---|---|---|
| 1. ድል | **ሞቅ ያለ** | **ማሸነፍ** |

2. አዛባ -------------------- -----------
3. አያት -------------------- ------------
4. ሽፍታ --------------------- ----------
5. ከፍታ ---------------------- ----------

**ተግባር 2. ጠብቀውና ላልተው የተለያየ ፍች የሚሰጡ አስር ቃላትን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

## ሁለተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ስዋስው

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ❖ ስለ ጾታ ምንነት ታብራራላችሁ፡፡
- ❖ አንስታይና ተባዕታይ ጾታን በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ጾታን ከተፈጥሯችን በመነሳት ሴቴና ወንዴ ወይም አንስታይና ተባዕታይ ብለን ብንጠራቸውም ምንም ጾታ የሌላቸውንም በለመድነው ልማድ መሰረት ወንድና ሴት ብለን እንጠራቸዋለን፡፡ በጥቅሉ ጾታ ሴትነትን ወይም ወንድነትን የሚያመለክት ነው፡፡

**ተግባር1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት የትኛውን ጾታ እንደሚያመለክቱ በቡድን በመሆን ለዩ፡፡**

| ቃል | ጾታ |
|---|---|
| 1. ልጅ | ወንድ/ተበዕታይ |
| 2. አለሚቱ | ሴት/አንስታይ |
| 3. ልጅቷ | ------------------------- |
| 4. አለሙ | ------------------------ |
| 5. ድንጋይ | ------------------------- |

**ተግባር2. ከላይ የተማራችሁት ጾታ ጥቅል ነው፡፡ ነገር ግን ያለምንም ቅጥያ ወንድና ሴትን የሚገልጹና ተጨማሪ ቅጥያ ወስደው ጾታን የሚያመለክቱ አሉ፡፡በቡድን በመሆን እነዚህን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

**ያለምንም ቅጥያ ጾታን የሚገልጹ**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ አባት | ሐ/ ወንድም | ሠ/ ባል |
| ለ/ እናት | መ/ ላም | ረ/ ሚስት |

**ቅጥያ በመውስድ ጾታን የሚገልጹ**

| | |
|---|---|
| ሀ/ ልጁ | ሠ/ሰውየው |
| ለ/ ልጅቷ | ረ/ ሴትዮዋ |
| ሐ/ አህያው | ሰ/ ብረድስቱ |
| መ/ አህያዋ | ሸ/ ብረድስቷ |

**ተግባር 3 ከላይ በተሰጣችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተሉትን ፆታ አመልካች ቃላት ያለቅጥያ ጾታን የሚያመለክቱና ቅጥያ ወስደው ጾታን የሚያመለክቱ ብላችሁ ለዩ፡፡**

| ቃል | ቅጥያ የሌለው | ቅጥያ ያለው |
|---|---|---|
| 1. ደከመች | ------------------------- | --------------- |
| 2. ደከመው | ------------------------ | --------------- |
| 3. አንበሳ | ------------------------ | --------------- |
| 4. ወይፈን | ------------------------ | --------------- |
| 5. ጊደር | ------------------------ | ---------------- |
| 6. ጎረምሳ | ------------------------- | ---------------- |
| 7. ልጃገረድ | ------------------------ | --------------- |

**ሶስተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት ሰባት**

**ሥነ-ጽሁፍ**

**ምሳሌያዊ ንግግሮች**

## ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

-ምሳሌያዊ ንግግሮችን ተጠቅማችሁ ሃሳባችሁን ትገልጻላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ምሳሌያዊ ንግግሮች አንድን ነገር በሚገባና በቀላሉ ለማስረዳት ሲፈለግ ተናጋሪው በንግግሩ ውስጥ እንደ ቅመም ጣል በማድረግ ንግግሩን የሚያጣፍጥበትና በቀላሉ ለማስረዳት የሚጠቀምበት ነው፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያገለግሉት የተናጋሪውን ሀሳብ ለማጠናከርና ግልጽ ለማድረግ ነው፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌያዊ ንግግር በምሳሌው መሰረት አብራሩ፡፡**

ምሳሌ፡-1 ያለ ሴት ቤት ያለ በሬ መሬት፡፡

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያስተላልፈው ቤት ያለ ሴት እንዳማይሞቅና መሬት ካለ ደግሞ ያለ በሬ እንደማይታረስ ነው፡፡ በተጨማሪም ለቤትና ለመሬት ሴትና በሬ ወሳኝ ነገሮች ናቸው ይላል፡፡

2. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል ፡፡

ሌብነትን የሚቃወም አባባል ነው፡፡ሌብነትን የለመደ ሰው ዳቦ አደራ ብታስጠብቀው ሌብነት ሱስ ስለሆነበት ባይበላውም ይልሰዋል ማለት ነው፡፡

**ችኮላን የሚነቅፉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ፡-**

- ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል፡፡
- የነ- ቶሎቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ፡፡
- የቸኮለች አፍሳ ለቀመች፡፡
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ፡፡

**ስግብግብነትንና ንፉግነትን የሚነቅፉ**

- ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ፡፡
- ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል፡፡
- ስስታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው፡፡
- ሆዳም ቢፈተፍት የበላ ይመስለዋል፡፡

**ስንፍናን የሚኮንኑ**

- ሰነፍ ቢመክሩት ውሃ ቢወቅጡት፡፡
- አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ፡፡
- ሰነፍ- ገበሬ በሰኔ ይሞታል፡፡

## ሶስተኛ ሳምንት ፡ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ቅጥያዎችን ማጣመርና መነጠል

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ቅጥያዎችን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን ታጣምራላችሁ፡

**ተግባር1. በ "ሀ" ምድብ የቀረቡትን ቃላት በ “ለ” ምድብ ከተቀመጡት ቅጥያዎች ጋር በማጣመር ቃል መስርቱ ፡፡**

| ሀ | ለ | ቃል |
|---|---|---|
| 1. ተማሪ | - ዎች | ተማሪዎች |
| 2. ግንብ | - ኧኛ | --------- |
| 3. ልጅ | - ኦች | ---------- |
| 4. ሰው | - ነት | ---------- |
| 5. ኢትዮጲያ | - አዊ | ---------- |

**ተግባር 2. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቃላትውስጥ ዋናውን ቃልና ቅጥያውን ለይታችሁ በማውጣት አሳዩ፡፡**

| ቃል | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|
| 1. መጣችሁ | መጣ | -ኣችሁ |
| 2. ተራራማ | ---------------- | ---------------- |
| 3. ደጋማ | --------------- | ------------ |
| 4. ብልጠት | ----------------- | ----------- |
| 5. ማህበራት | ------------------- | ------------ |

**ተግባር 3. ከላይ በተማራችሁት መሰረት አስር ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ፈልጋችሁ በመፃፍ ዋናውን ቃልና ቅጥያውን ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

## ሶስተኛ ሳምንት ፦ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ስርዓተ ነጥቦች

### ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ድርብ ሰረዝን በዐረፍተነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- የሦስት ነጥብ አገልግሎትን ታብራራላችሁ፡፡

| ማስታወሻ |
|---|
| ድርብ ሰረዝ - ተያያዥነት ያላቸው ሀረጋትንና ዐረፍተ ነገሮችን ለማያያዝ የምንጠቀምበት ሲሆን፣ ሦስት ነጥብ ግን የቀረ ሀሳብ መኖሩን ለመግለጽ ያገለግላል፡፡ |

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ በመመልከት በምሳሌው መሰረት ቀጣዮቹን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

ምሳሌ ፡-1. አበበ በእረፍት ቀኑ ልብሱን ያጥባል፤ሰውነቱን ይታጠባል፤ ተጨማሪ ሥራዎችን ይሰራል፡፡

2. ንፋሱ ነፈሰ ፤ ዝናቡ ዘንበ፤ ሰማዩ ጨላለመ፡፡

3. ልጁ ከጨዋታ መልስ ወደ ቤቱ ሄደ፤ የቤት ስራውን ሰርቶ.. ተኛ፡፡

ሀ/ አንበሳ ሲያድን ይመለከታል---------ይዘጋጃል----------በመጨረሻም አባሮ ይይዛል፡፡

ለ/ እባክህን ቶሎ  ብለህ ወደ ቤት ውሰደኝ አለችና -------------በመኪና ይዟት እየፈጠነ ወደቤቷ ወሰዳት፡፡

ሐ/ በልቷል ---------ዘርፏል.... ገኗል---------ብላችሁ ስሜን  ለምን ታጠፋላችሁ፡፡

መ/ ምንድነው የተፈጠረው ?ብሎ ግርግሩ ውስጥ ገባ ----------ነገሩን ለማርገብ የሞከረው ሙከራ ገን አልተሳካለትም፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ ጭውውቶችን ሰምታችሁ ሀሳባችሁን ተናግራችኋል፡፡ በመቀጠልም ስለ አካባቢ ጥበቃ የተፃፉ ምንባቦችን በማንበብ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርታችኋል፡፡ እንዲሁም የገረፍታ ስለ ተባለ የምንባብ ስልት የተማራችሁ ሲሆን፣ መጠይቃዊ ቃላት የሚባሉትን በጽሁፍ ውስጥ በማስገባት ልምምድ አድርጋችኋል፡፡ በተጨማሪ ስለሚጠብቁና ስለሚላሉ ቃላት ፣ስለ አንስታይ እና ተባዕታይ ፆታ፣ ስለ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ቅጥያዎችን መነጠልና ማጣመር ፣የስረዓተ- ነጥቦችን አጠቃቀም በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸው ናቸው፡፡

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በግል በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ/ መጠይቃዊ ቃላት የሚባሉትን ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

ለ/ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት አምስት ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

ሐ/ ጾታን የሚያመለክቱ ቃላትን ሰብስባችሁ አቅርቡና ውይይት አደርጉባቸው ፡፡

መ/ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስባችሁ በማምጣት ስለምን እንደሚናገሩ ለክፍሉ አብራሩ ፡

ምዕራፍ አምስት

የግለሰብ የህይወት ታሪክ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሌሎች ተማሪዎችን ልምድ በማዳመጥ የራሳችሁን ልምድ ትናገራላችሁ፡፡
- ስዕሎች ፣ካርታዎች ሰንጠረዦች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትናገራላችሁ፡፡
- ጥልቅ የንባብ ስልትን በመጠቀም የንባቡን መልዕክት ታወጣላችሁ፡፡
- ዋናና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ተጠቅማችሁ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ትጠቀማላችሁ ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| ስሜት | የሀገር ፍቅር | ሁለንተናዊ |
| መቆርቆር | ሀገርን መውደድ | ዳርቻ |
| መገለጫ | ሰንጠረዥ | ግራፍ |

## አንደኛ ሳምንት ክፍለትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የሚነገራችሁን ልምድ አዳምጣችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ፡፡
- የራሳችሁን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታካፍላላችሁ ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ

ሀ/ ልምድ ማለት ምን ማለት ነው ?

ለ/ ልምድ ማካፈል ምን ጠቀሜታ አለው ?

ሐ/ የታዋቂ ሰዎችን ልምድ በማዳመጥ ምን ትምህርት ልንወስድ እንችላለን?

**ተግባር 1. ቀጥሎ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን የአንድ ተማሪ ልምድ በደንብ በማዳመጥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ ።**

ሀ/ ልምዱን የተናገረው ተማሪ የስንተኛ ክፍል ተማሪ ነው?

ለ/ በአዳመጣችሁት ምንባብ ላይ ያካፈለው ልምድ ምንድነው?

ሐ/ የሱ ልምድ ጥሩ መሆኑን ከተረዳን እኛም በህይወታችን አስገብተን ልንጠቀምበት እንችላለን ?

**ተግባር 2. ከዚህ በመቀጠል እናንተ የራሳችሁን ልምድ ተራ በተራ በመነሳት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።**

## አንደኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ሁለት

## መናገር


ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ስለተመለከታችሁት ስዕልና ካርታ ትናገራላችሁ።
- ሰንጠረዦች የያዙትን መልዕክት ታስረዳላችሁ።

| ተ/ቁ | የክፍል ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 5ኛ | 423 | 454 | 857 |
| 2 | 6ኛ | 441 | 326 | 767 |
| 3 | 7ኛ | 496 | 423 | 919 |
| 4 | 8ኛ | 445 | 453 | 898 |
| | ድምር | 1805 | 1636 | 3441 |

**ተግባር1..ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የዱመርሶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2011 ዓ/ም ከአምስተኛ እስከ 8ኛ የሚማሩ ተማሪዎች በአመቱ መጀመሪያ የተመዘገቡበት ሰንጠረዥ ነው፡፡ ሰንጠረዡን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በምዝገባ ወቅት ብዙ ተማሪዎች የተመዘገቡበት ክፍል የትኛው ነው፡?
2. ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴት ተማሪዎች የተመዘገቡበት ክፍል የትኛው ነው ?
3. በየክፍሉ የተመዘገቡትን ተማሪዎች ከትልቁ ቁጥር ጀምራችሁ እስከ ትንሹ ቁጥር በቀደም ተከተል ዘርዝሩ?
4. ወንዶች በዝቅተኛ ቁጥር የተመዘገቡበት ክፍል የትኛው ነው?




**ተግባር2. ከዚህ በላይ የቀረበው ግራፍ የሚያመለክተው ከ2004---2008 ዓ.ም በደቡብ ክልል በሚገኝ በአንድ ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች መሀከል ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ያለፉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህንን ግራፍ በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በግራፉ ላይ ከተጠቀሰው ዓመት ምህረት ብዙ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ያመጡበት ዓመተ ምህረት የትኛው ነው?

2. ብዙ ተማሪዎች መካከለኛ ውጤት ያስመዘገቡበት በየትኛው ዓመተ ምህረትነው ?
3. በ2006 ና በ2007 ዓመተ ምህረት ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አምጥተዋል?
4. በአምስት ዓመት ውስጥ በጠቅላላ ስንት ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አምጥተዋል?

**ተግባር 3. ከላይ በሰራችሁት መሰረት የክፍላችሁን ተማሪዎች በፆታ ፤በእድሜ ከፋፍላቸሁ ሰንጠረዥ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

**አንደኛ ሰምንት ክፍለ ትምህርት ሶስት**

**ስዕላዊ ገለፃ ማድረግ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሚቀርብላችሁን ስዕል ተመልክታችሁ ማብራሪያ ትሰጣላችሁ፡፡
- ስዕሎች የሚያስተላልፉትን መልዕከት ታብራራላችሁ፡፡

**ተግባር 1 ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕሎች በመመልክት ከስዕሉ ግርጌ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**



ሀ/ በስዕሉ ላይ የምትመለከቱት ስለምንድነው?

ለ/ እየተሰራ ያለው ስራ መልካም ስራ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሐ/ እንደዚህ አይነት ሥራ የሚሰሩ ሰዎች የሚበረታቱበት ነገር መፈጠር ይኖርበታል ትላላችሁ ?

መ/ መልካም ስራ ለመስራት የናንተስ ፍላጎት ምን ያህል ነው?

## ሁለተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት አራት

### ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የቀረበላችሁን ንባብ አንብባችሁ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ስለ ግለሰቡ የሰማችሁትን ታሪክ አሳጥራችሁ ትናገራላችሁ፡፡

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

የግለሰቦች የህይወት ታሪክ ምንን ያመለክታል ?

የግለሰቦች የህይወት ታሪክ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለው?

ከዚህ በፊት የግለሰቦችን የህይወት ታሪክ አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ?

### ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ

ዶክተር ቦጋለች ገብሬ የተወለደችው ከአዲስ አበባ 355 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደቡብ ክልል ውስጥ በምትገኘው የከንባታ ጠንባሮ ዞን ባቾ በተባለች ትንሽ መንደር ነው፡፡ ዶ/ር ቦጋለች በተወለደችበት ዘመን በባቾ አካባቢ የትኛዋም ሴት ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ አይፈቀድላትም ነበር፡፡ ሴት ልጅ ከማጀት ጉዳዮች አልፋ ለትልቅ ቁም ነገር ትደርሳለች ተብሎ በማህበረሰቡ አይታሰብም፡፡ ይልቁንም ሴቶችን የሚጫኑ ልዩ ልዩ ጎጂ ልማዶች የሚከናወኑበትና የሴት ልጅ ግርዛት የተስፋፋበት ጊዜ ነበር፡፡

ዶክተር ቦጋለች ወደ አጎቷ ቤት በመሄድ ከተማሩ አጎቷና የአጎቷ ቤተሰቦች ፊደልን ተምራለች፡፡ ከዚያም በመቀጠል ማንበብና መፃፍም ቻለች፡፡ በመጠንከር ወላጆቿ የሚያዟትን ስራ በትጋት በመስራት ስራዋን ከአጠናቀቀች በኋላ በሚነደው እሳት ብርሃን ቁጭ ብላ ታጠና ነበር፡፡

ትጋቷንና ጥንካሬዋን ያዩ አባቷ ትምህርት ቤት እንድትገባ ፈቀዱላት። በቀን እስከ 6 ኪሎ ሜትር በመጓዝ ትምህርቷን ቀጠለች። በዘጠኝ አመቷ የአራተኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቀቀችና ወደ አምስተኛ ክፍል ገባች። ይህም በዚያ አካባቢ ካሉት ሴት ተማሪዎች በላይ የተማረች አደረጋት። እሷም ለመንደሩ ሰዎች ማመልከቻ በመፃፍ ትረዳቸው ነበር። በአካባቢው ባህል መሰረት አባት በወንድ ልጁ ስም የእከሌ አባት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን እናት ደግሞ በሴት ልጇ ስም የእከሊት እናት ተብላ ነው የምትጠራው። የቦጋለች ጉብዝና ግን ይህን ታሪክ ቀየረውና አባትየው የቦጋለች አባት እየተባሉ መጠራት ጀመሩ።

ቦጋለች የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በዚያው በመጨረስ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በመነን ትምህርት ቤት ተምራለች። ከዚያም ነፃ የትምህርት እድል በማግኘት ወደ እስራኤል ሄዳ ተምራለች ።ከዚያም በተለያዩ ሀገራት በመሄድ ተምራ በ "ኢፒዴሚሎጂ" የዶክተሬት ዲግሪ ይዛለች። ደ/ር ቦጋለች በአፀፋው "ሴት ልጅ መደባ ማጀት ነው" የሚለውን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከንባታ ወጣት ነች።

**(ምንጭ ኩሜ ቢሮ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ 2003 ዓ/ም)**

**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ምንባብ በአነብባችሁት መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ዶክተር ቦጋለች ገብሬ የተወለደችው በየትኛው አካባቢ ነው?
2. የዶክተር ቦጋለች አባት፣የቦጋለች አባት እየተባሉ መጠራት የጀመሩት ከመቼ ወዲህ ነው?
3. በመጀመሪያ ትምህርቷን የጀመረችው ቤተሰቦቿ ፈቅደውላት ነው?

**ተግባር 2. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡-**

1. የቦጋለች ቤተሰቦች አቅም ስለሌላቸው ትምህርቷን ያቋረጠችው አራተኛ ክፍል ነው።

2. ቦጋለች ምንም ትምህርት ብትከለከልም በራሷ ብርታትና ፍላጎት ነው ፊደል ፣ማንበብና መፃፍ የለመደችው፡፡
3. ከሀገሯ ወጥታ ወደ አዲስ አበባ የሄደችው እዚያ ያሉ ቤተሰቦቿጋ ለመኖር ነበር ፡፡
4. ደብዳቤና ማመልከቻዎችን የምትጽፍላቸው በአካባቢው ላሉ ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ሰዎች ነበር፡፡
5. እስከ ውጪ ሀገር ለትምህርት መሄዷ የመማር ፍላጎቷን ትልቅነት ያሳያል፡፡

**ተግባር3. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ፡**

1. የቦጋለች አባት፣ ቦጋለች ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ የፈቀዱላት መቼ ነበር

   ሀ/ ማንበብና መፃፍ ከጀመረች በኃላ ለ/ እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ

   ሐ/ የቤት ስራ ስለማትሰራ መ/ ለና ሐ መልሰ ናቸው

2. ቦጋለች ወደ አምስተኛ ክፍል ስትገባ የመጀመሪያዋ ሴት ተማሪ ሆነች ሲባል

   ሀ/ ሌሎች የተማሩት ከዚያ በታች ነበር፡፡ ለ/ ሌሎች አልተማሩም ነበር ፡፡

   ሐ/ ሌሎች የተማሩት ከዚያ በላይ ነበር ፡፡ መ/ መልስ የለም

3. "አንድ ሰው ጠንክሮ ከታገለ ምንም ነገር አያሸንፈውም፡፡" የሚለው ቃል ከቦጋለች ህይወት አንፃር

   ሀ/ እውነት ነው ለ/ ትክክል አይደለም

**ሁለተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት አምስት**

**አንቀጽ መፃፍ**

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች**

❖ ዋና ሀሳብ የያዘውን ዐረፍተ ነገር ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
❖ ዝርዝር ዐረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
❖ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ዋና ዓረፍተ ነገር - በአንቀጽ ውስጥ ሊገለጽ የታሰበውን ዋናውን ሀሳብ ጠቅሎ የያዘ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ዋና አረፍተ ነገር ሃይለ ቃል እየተባለም ይጠራል፡፡

ዝርዝር ዓረፍተ ነገር - በዋናው ዓረፍተ ነገር የተገለፀው ሀሳብ የተብራራበትና የተተነተነበት ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

አንቀጽ - በዋና ዓረፍተ ነገርና በዝርዝር ዓረፍተ ነገር የተዋቀረ አንድነትና ግጥምጥምነት ያለው የጽሁፍ ክፍል ነው፡፡

**ተግባር 1. ከሚቀጥሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የያዘውንና ዝርዝር ሀሳብ የያዙትን ዐረፍተ ነገሮች ለይታችሁ አውጡ፡፡**

1. ሀ/ አጠር አጠር ያሉና ፈጣንነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡
   ለ/ እንቅስቃሴያቸው በህብረት ነው፡፡
   ሐ/ ልጆች በጨዋታ ጊዜ የሚያዜሙዋቸው ዜማዎች ይለያሉ፡፡
   መ/ ከነዚህም መሀከል አንዱ መሀረቤን ያያችሁ ነው፡፡
2. ሀ/ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው አዲስ አበባ ነው የሚኖሩት ፡፡
   ለ/ ለምለምና ዘላለም በጣም የሚዋደዱ እህትና ወንድም ናቸው፡፡
   ሐ/ በዚሁ ቦታ ብዙ ፈተና ገጥሟቸዋል፡፡
   መ/ ሆኖም ሁሉንም በህብረት በመሆን አሸንፈዋል፡፡
3. ሀ/ ከነዚህ መካከል አባያና ጫሞ ተጠቃሾች ናቸው
   ለ/ ለዚህም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል
   ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሀይቆች ይገኛሉ፡፡
   መ/ በሁለቱ ሀይቆች መካከል ተመሳሳይነትና ልዩነት አለ፡፡

**ተግባር 2 ከላይ ዋናውን ዐረፍተ ነገርና ዝርዝር ዐረፍተነገሩን በለያችሁት መሰረት ዋናውን ዐረፍተ ነገር በማስቀደም ዝርዝር ዐረፍተ ነገሮችን በማስከተል አንቀጽ መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-1** ልጆች በጫወታ ጊዜ የሚያዜሙአቸው ዜማዎች ይለያያሉ፡፡ አጠር አጠር ያሉና ፍጥነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ እንቅስቃሴያቸውም በህብረት ነው፡፡ ከነዚህም መካከል መሀረቤን ያያችሁ አንዱ ነው፡፡

**ከላይ የቀረበው አንቀጽ ላይ እንደሚታየው የተሰመረበት ዋናው ዐረፍተ ነገር ሲሆን ከሱ ስር ያሉት ደግሞ ዝርዝር ዐረፍተነገሮች ናቸው፡፡በዚሁ መሠረት ሌሎቹንም በማደራጀት አንቀጽ መስርቱ፡፡**

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት

## አንብቦ መረዳት

ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- በጥልቅ ንባብ ስልት ምንባቦችን ታነባላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ መልእክቱን ታወጣላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ጥልቅ ንባብ የምንለው ከአንድ ንባብ ውስጥ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ፈልፍለን ለማውጣት በእርጋታና በትኩረት የምናደርገው ንባብ ነው፡፡ጥልቅ ንባብ የምንማራቸውን ትምህርቶች በጥልቀት አንብበን ለመረዳት ይረዳናል፡፡

**ተገባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥልቀትና በትኩረት በማንበብ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

## የመንገድ አጠቃቀም

ስለመንገድ አጠቃቀም ለአሽከርካሪም፣ ለመንገደኛም መሰረታዊ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መጻህፍት በግለሰቦች ፣በአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋማት፣ እንዲሁም በመንገድ ትራንስፖርት ባለ ስልጣን በየጊዜው ይታተማሉ፡፡ ተጠቃሚው ማነው ሲባል ግን መልሱ መንጃ ፍቃድ ለማውጣት የፈለገ

ወይም የፈለገች ናት፡፡ ነገር ግን እግረኞች ሊያውቁትና ሊማሩበት ይገባል፡፡ እስቲ ለአብነት ያህል በሀገራችን የመንገድ ስርዓት መሰረት በሁሉም መጻህፍት ውስጥ የሚገኝ አንድ መመሪያ እንመልከት ፡፡ለተሸከርካሪ ክፍት በሆኑ መንገዶች እግረኞች የግራ መስመራቸውን ይዘው መጓዝ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ታዲያ ይህንን መመሪያ እግረኞች መጻህፍቱን አንብበውና አውቀው ካልተገበሩት አሽከርካሪዎች ብቻ ስለ አውቁት ምን ያህል ውጤታማ ሊሆን ይችላል ፡፡

ህግና ስርአቱን ሾፌሩ ያውቀዋል፡፡ተሳፍሪው ግን በአጋጣሚ በሰማው አሊያም በደመነብስ ይጓዛል ለምሳሌ- እኛ ደስ ባለን ወይም በፈለግነው ቦታ ላይ እንጓዛለን፤ በፈለግነው ቦታ ላይ ከመኪና አውርዱን እንላለን፤ እምቢ ካሉም እስከ መጣለት ድረስ እንደርሳለን፡፡ አንዳንድ ሾፌሮችም ቢሆኑ በልምድ እንጂ በመጻህፍቱ ላይ ያሉትን መመሪያዎችና የመንገድ ዳር ምልክቶች ትርጉም ገብቷቸው አደለም የሚያሽከረክሩት፡፡ ምክንያቱም መጽሀፉን ያነበቡት ለፈተና ብቻ ስለሆነ ነው፡፡

ሀ/ ያነበባችሁት ምንባብ ምን አይነት መልዕክት ነው የሚያስተላልፈው?

ለ/ ስለመንገድ አጠቃቀምና ስለ አሽከርካሪ የሚናገረው ምንባብ ምን ምን ችግሮችን ነው የሚያንፀባርቀው?

ሐ / ችግሩን ለመፍታት ምን አይነት እርምጃ ነው መወሰድ ያለበት ?

መ/ ከዚህ ምንባብ የተረዳችሁትን ነገር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

**ተገባር2. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ቀጥተኛ ፍቺያቸውን ስጡ፡፡**

1. አጠቃቀም
2. ለፈተና ብቻ
3. ህግ
4. ስርአት
5. ተጠቃሚ
6. ግንዛቤ

## ሶስተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ሰባት

### ስዋስው

የዐረፍተ ነገር ክፍሎች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን አውቃችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

**ከላይ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ስለ ባለቤት ፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ፡፡ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ትምህርት ክፍል የስም ገላጭን በመጨመር ትማራላችሁ፡፡**

ማስታወሻ

የስም ገላጭ ፡- የምንለው ከስሞች በፊት ወይም ቀድሞ እየመጣ ስሞችን ከመጠን ፣ከዓይነት ፣ወዘተ አንፃር የሚገልጽ ነው

**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በስም ገላጭ ቦታ ገብተው ስምን የሚገልጹ ቃላትን ተመልከቱ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| አጭር | ብዙ | ቀጭን | ጎበዝ |
| ቀይ | ረጅም | አዲስ | አሮጌ |
| ወፍራም | ጥቁር | ሰነፍ | ትልቅ |

ምሳሌ ፡-1. አጭር ቀሚስ ትንሽ ልጅ

ቀይ በሬ ጎበዝ ተማሪ

አሮጌ ልብስ ትልቅ ዛፍ

2. ሀ/ አበበ <u>**ነጭ ልብስ**</u> መልበስ ይወዳል፡፡

ለ/ እኔ <u>ቀይ</u> በሬ ገዛሁ፡፡

ሐ/ <u>ወፍራሙ ሰውዬ</u> መጣ፡፡

መ/ <u>ትልልቅ ዛፎች</u> ይታዩኛል፡፡

ሠ/ አንጀሎ <u>ትንሽ በግ</u> ገዛ ፡፡

**ተግባር2. ከላይ በምሳሌው በተመለከታችሁት መሰረት የሚከተሉትን ስሞችና የስም ገላጮች አጣምሩ፡፡**

| **የስም ገላጭ** | **ስም** |
|---|---|
| ቀጭን | አበባ |
| ቀይ | ገበሬ |
| ጎበዝ | መኪና |
| አሮጌ | ጀበና |
| ጥቁር | ማስመሪያ |

**ተግባር 3 .በመቀጠል እነዚህን ያጣመራችኋቸውን የስም ገላጮች፣ስምና ተሳቢ በማድረግ ዐረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ ቀይ አበባ**

ጡሜቦ ቀይ አበባ ይዟል፡፡ቀይ አበባ ተሳቢ ሆኖ ገብቷል፡፡

## ሶስተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ሥነ ጽሁፍ

### ፈሊጣዊ ንግግር

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ፈሊጣዊ ቃላትን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- ፈሊጣዊ ንግግርን በንግግራችሁና በጽሁፋችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፧

ማስታወሻ

ፈሊጣዊ ንግግር የምንላቸው ከመደበኛ ፍቺያቸው ውጪ ሌላ ፍች በመያዝ ሀሳባችንን የሚያጎሉልንና የበለጠ ሀሳባችንን ግልጽ የሚያደርጉልን የቃላት አጠቃቀሞች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ በጥምር ቃል የተመሰረቱ ናቸው፡፡

**ምሳሌ፤-** አመድአፋሽ ፣እግረቀላል ፣ጥቁርእንግዳ ፣ገደቢስ ፣ እግረደረቅ፣ ጥላቢስ

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ፈሊጣዊ ንግግሮች በመመልከት ያላቸውን ፍቺ ተረዱ ፡፡**

1. አመድአፋሽ - ሰጥቶ ውለታው የማይታሰብለት

2. ገደቢስ - ምንም እድል የሌለው
3. እግረቀላል - ፈጣን
4. ልበሙሉ - ደፋር
5. ጥቁርምላስ - ከፉ ተናጋሪ
6. ሆድአምላኩ- - መብል ብቻ የሚወድ

**ተግባር 2 ከላይ ባያችሁት ምሳሌ መሰረት በቡድን በመሆን አምስትፈሊጣዊ ንግግሮችን ጻፉ።**

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ቃላት

**የቃላት ቀጥተኛ ፍች**

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች**

- ❖ የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ትናገራላችሁ።
- ❖ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ።

**ተግባር1 ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት በቡድን በመሆን ቀጥተኛ ፍችያቸውን ስጡ፡፧**

1. ወላጅ አልባ
2. መመሪያ
3. ፍቅር
4. በጎነት
5. እርምጃ

**ተግባር2 ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት ቃላት እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

| ሀ/ | ለ/ |
|---|---|
| 1. ሰጠ | ሀ/ ለብቻ |
| 2. በጋራ | ለ/ ጥላቻ |
| 3. አስበ | ሐ/ ወሰደ |
| 4. ነገረ | መ/ ተወ |

5. ፍላጎት ሠ/ ወቀሳ
6. አደረገ ረ/ የተበከለ
7. ምስጋና ሰ/ በግምት
8. ንፁሕ ሸ/ ዝምአለ

## የምእራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የሌሎች ተማሪዎችን ልምድ አዳምጣችሁ የራሳችሁን ልምድ እንዴት እንደምታካፍሉ ተምራችኋል፡፡ ከዚያም የቀረቡላችሁን ሰንጠረዦችና ግራፎች በመመልከት ጥያቄዎችን በቃል መልሳችኋል፡፡ ከንባብ ስልቶች አንዱ የሆነውን ጥልቅ የንባብ ስልት ተምራችኋል፡፡ ምንባቡን በዚያው መሰረት አንብባችኋል፡፡ ዋናና ዝርዝር ዐረፍተ ነገሮች ምን እንደሆኑና ዋና ዐረፍተ ነገር ዋናውን ሀሳብ ጠቅልሎ የያዘ እንደሆነ፣ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች እሱን ለማብራራት የሚገቡ እንደሆኑ ተምራችሁ አንቀጽ መስርታችኋል፡፡ በመቀጠልም ስለስም ገላጭና ስም ተምራችሁ ዐፍተነገርን መስርታችኋል፡፡ በመጨረሻም ስለ ፈሊጣዊ ንግግር ተምራችሁ ለፈሊጣዊ ንግግሮች ፍች በመስጠት ሰርታችሁ ምዕራፉን አጠናቃችኋል፡፡

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተማራችሁት መሰረት መልሱ፡፡**

1 ልምድን ማካፈል የሚቻለው ምን አይነት ልምድ ሲኖር ነው?
2. በስዕሎችና ሰንጠረዦች መልእክትን ማስተላለፍ ይቻላል?
3. ጥልቅ የንባብ ስልትን የምንጠቀመው እንዴት ላለ ንባብ ነው?
4. ዋናና ዝርዝር ዐረፍተ ነገር የምንላቸው ምንድናቸው?
5. አንቀጽ በውስጡ የሚይዛቸውን የዐረፍተ ነገር ዓይነቶች ግለጹ፡፡
6. ከአምስት ያላነሱ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡

**ምዕራፍ ስድስት**

**ሀገር ወዳድነት**

## ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- *የሚቀርቡትን ምንባቦች አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡*
- *ሀገር በቀል እውቀቶችን አምጥታችሁ ለክፍል ትናገራላችሁ፡፡*
- *ምንባቡን አንብባችሁ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ታወጣላችሁ፡፡*
- *የተማራችሁትን መመሪያ ተከትላችሁ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡*
- *ቃላትን አዳምጣችሁ ቀጥተኛ ፍችያቸውን በቃል ትናገራላችሁ፡፡*
- *የዐረፍተ ነገር ስልቶችን አውቃችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡*
- *የቀረበላችሁን ግጥም ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ ታነባላችሁ፡፡*

## ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሚስጥራዊነት | የሀገር ፍቅር |
| መቀላቀል | እንቅልፍ ይነሳል |
| ይረክሳል | ቋሚ |

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ

## አዳምጦ መረዳት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሚቀርብላችሁን ንባብ አዳምጣችሁ ታብራራላችሁ፡፡
- አዳምጦ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ

ሀ/ ባህላዊ መድሐኒቶች ጉዳት አላቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ/ መደሃኒቶች መጠናቸው ካልታወቀ የሚያስከትሉት ጉዳት ምንድነው ?

ሐ/ ባህላዊ መድሐኒቶችን ወደ ዘመናዊ መድሐኒትነት ለመቀየር ምን መደረግ አለበት ?

**ተግባር1. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ ።**

1. ከምንባቡ እንደሰማችሁት በባህላዊ መንገድ መድሐኒት( የሚያዘጋጁት) የሚዘጋጀው ከምን ከምንድነው?
2. የባሕል መድሐኒቶችን ለሰዎች ሲሰጡ መለኪያቸው ወይም መጠኑን ማወቂያቸው ምንድነው ?
3. የባህል መድሐኒትን በጥቅሉ ጎጂ ነው ብለን መደምደም እንችላለን ?
4. የባህል መድሐኒት ከሀገራችን ሀገር በቀል እውቀት አንፃር ብዙ ተሰርቶበታል ትላላችሁ?

**ተግባር2. ከላይ ካዳመጣችሁት አገር በቀል እውቀትን ከሚናገረው ምንባብ ተነስታችሁ በአካባቢያችሁ ከሚገኙት ሀገር በቀል በህላዊ እውቀቶች መካከል በቡድን በመሆን አሰባስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅርብ አዳምጠው አስተያየት እንዲሰጡበት አድርጉ።**

አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሁለት

መናገር

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ የንባቡን ሀሳብ ተናገሩ።**

## የባህል መድሐኒት

በሀገራችን በኢትዮጵያ በተለይም በደቡቡ ክልል በስፋት የሚታወቁ የባህል መድሐኒቶች አሉ። እነዚህ የባህል መድሐኒቶች የተለያዩ በሽታዎችን ለመፈወስ የሚጠቅሙ ሲሆኑ ሚስጥርነታቸው ግን መድሐኒቱን በሚያውቁ ሰዎች የተጠበቀ ነው። ምክንያቱም ስለመድሐኒቱም ምንነት ለማንኛውም ሰው ከተነገረ መድሐኒቱ ይረክሳል የሚል እውነታ አለ። መደሐኒቶቹ ከተክሎች ቅጠል ፣ ከግንዱ ቅርፊት፣ ከተክሎች ስር፣ ከተክሎች ፍሬ ፣ወዘተ የሚሰበሰቡ ሲሆን አንዳንዱ ብቻውን ተቀምሞ ሲሰጥ አንዳንዱ ግን ከሌሎች

ጋር በመቀላቀል ተቀምሞ መድሐኒት እንዲሆን ይደረጋል። ያንንም ለታመሙ ሰዎች በመስጠት ይፈወሱበታል። ይህ የባህል መድሐኒት አባቶች ከሚታወቁበት ሀገር በቀል እውቀት አንዱ ሲሆን ይህንን ዕውቀት በዘመናዊ ሳይንስ በመቀየር አገራችን እንድትጠቀምበት አልተደረገም። ይህ ደግሞ የሀገራችንን ትተን የሩቅ ናፋቂ እንድንሆን አድርጎናል።

**ተግባር 2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።**

1. ሀገር በቀል የባህል መድሐኒት ማለት ምንድነው?
2. ብዙውን ጊዜ የባህል መድሐኒት የሚፈለገው ለምንድነው?
3. ሃገር በቀል እውቀትን እንዴት ወደ ዘመናዊና ሳይንሳዊ መንገድ መቀየር ይቻላል?
4. የባህል መድሐኒትና ዘመናዊ መድሐኒት በሚል ርዕስ በቡድን በመሆን ክርክር አቅርቡ።

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሶስት

## ምንባብ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- ❖ ምንባቡን በጥልቀት ታነባላችሁ።
- ❖ የምንባቡን መልዕክት ታወጣላችሁ።

**ቅድመ ንባብ ጥያቄ**

1. የሀገር ፍቅር ምንድነው ?
2. የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ሰዎች መገለጫቸው ምንድነው?
3. የሀገር ፍቅር ስሜት ሲቀንስ ለሀገር መቆርቆር አብሮ ይቀንሳል?

### ያገር ፍቅር ስሜት

የሀገር ፍቅር ስሜት አለም አቀፋዊና ሁለንተናዊ ነው። አንዱጋ በርቶ ሌላው ጋ የሚጠፋ ሻማ አይደለም። ሰውና ሀገር እስካሉ ድረስ አብሮ የሚኖር ነው። አብሮነቱ ህያው ሲሆን ስሜቱም እውነት ነው። በየትኛውም የአለም ዳርቻ ወይም እንብርት ላይ የሚኖር፣ በየትኛውም ሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀስ፣ በማንኛውም ልብ ውስጥ የሚነግስ ነው። የሀገር ፍቅር

ስሜት እርግጥ ነው፤ ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህ ስሜት ከመሆኑ አንፃር ሊቀያየር የሚችል ነው፡፡

የሀገር ፍቅር በልብ ውስጥ እንደሚታተም ታትሞ የሚኖር ህያው ስሜት ነው፡፡ ሀገርን ሲያነሷት የሚሸንጥ፣ ክብሯ ሲነገር፣ የሚያስደስት፣ ሲነካኳት የሚያስቃስት የሀገር ፍቅር (Patriotism) በየዜጋው ልብ ውስጥ ስሩን ሰዶ፣ የሚያብብ አበባ ነው፡፡

የአበባውም አይነት ፅጌረዳ ሲሆን በሾህም የታጠረ ነው፡፡ አባቶቻችን እሾህ ሆነው ወራሪውን በመዋጋት ሲመክቱ የኖሩት ስለዚህ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለቅኝ ገዥዎች እሳት ሆነው ኖረዋል፡፡ ወደፊትም ይቀጥላሉ፡፡ ጠላትን በየጊዜው መክተው መልሰዋል፡፡ ወደ ፊትም ይመከታሉ፡፡ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ፍቅር እስከ ሞት ይታገላሉ፡፡

የሀገር ፍቅር ስሜት እንቅልፍ ይነሳል፡፡ አንድ ባለሀብት ከኔ ቢጤ ደሃው የበለጠ ንብረቴ ሃብቴ ይሰረቃል ብሎ እንደሚጨነቅና ዘወትር እንደሚጠነቀቅ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ጠላቶቻቸውን ነቅተው ይጠብቃሉ፡፡ ጠብቀውም ይመክታሉ፤ መክተው ይመልሳሉ፡፡ ይህ የትላንት እውነት ነበር፡፡ ዛሬም ቋሚ እውነት ነው፡፡ ነገም እውነት ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በእኛም በተተካውም ትውልድ የሀገር ፍቅር ስሜት እንደ ሀውልት በልባችን ውስጥ ትልቅ ህንፃ ሆኖ ሊቀመጥ ይገባዋል፡፡ የማይፈርስ ጽኑ ግንብ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከኔ በላይ ሀገሬ ልንል ይገባናል፡፡

**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ምንባብ ደጋግማችሁ በጥልቀት በማንበብ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የሀገር ፍቅር ስሜት እንቅልፍ ይነሳል ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ለሀገርና ለወገን ፍቅር እስከሞት ድረስ መቆም የሀገር ፍቅር ስሜትን በትክክል ያንጸባርቃል?
3. ተተኪው ትውልድ የሚለው የትኛውን የማህበረሰብ ክፍል ነው ?

**ተግባር2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. በማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ፣በማንኛውም የሰው ልብ ውስጥ የሚነግስ የተባለው፡፡

ሀ/ የሰው ልጅ ፍቅር  ለ/ የሀገር ፍቅር  ሐ/እራስ ወዳድነት መ/ሁሉም

2. «ባለሀብት ከደሃው የበለጠ ንብረቱ ይሰረቃል ብሎ እንደሚጨነቀው ":- የሚለው ሃሳብ የተነፃፀረው ከምን ጋር ነው፡፡

ሀ/ ከሀገር ፍቅር  ለ/ ጥላትን ተጠንቅቆ ከመጠበቅ ሐ/ ገንዘብን ከመጠበቅ

3. “ከእኔ ይልቅ ለሀገሬ ልንል ይገባናል” የሚለው ሃሳብ የሚገልፀው

ሀ/ እራስን ማስቀደምን ለ/ጥቅምን ማስቀደምን ሐ/ ሀገርን ማስቀደምን

4. የሀገር ፍቅር ስሜት በልባችን ውስጥ ምን መሆን አለበት?

ሀ/ እንደሀውልት መቆም ለ/ እንደግንብ መጽናት

ሐ/ እንደአለት መጠንከር መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

5. የሀገር ፍቅር ስሜት ያለው ዜጋ

ሀ/ ስለሀገሩ ይቆረቆራል ለ/ ሀገሩ በጠላት እንድትጠቃ አይፈልግም

ሐ/ ሀገሩ ስትደሰት ይደሰታል መ/ ሁሉም መልስ ነው

**ተግባር3. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ ከገቡበት አውድ አንፃር ፍች ስጧቸው፡፡**

1. የሀገር ፍቅር ስሜት
2. ተተኪው ትውልድ
3. ቅኝ ገዢ
4. የሚነሽጥ
5. ህያው

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አራት

### መፃፍ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ❖ የግል ደብዳቤ አፃፃፍን ታውቃላችሁ፡፡
- ❖ የግል ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

የግል ደብዳቤ የሚባለው አንድ ግለሰብ ለዘመዱ፣ ለወዳጁ ፣ወዘተ ሰላምታን ለማቅረብ የሚጽፈው ነው፡፡ የራስን ችግርም ይሁን ደስታ ለመግለጽ፣ ደህንነትን ለመጠየቅ በግል የሚፃፍ ደብዳቤ ነው ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን የግል / የወዳጅ ደብዳቤ ቅርጽና በውስጡ ያሉትን ክፍሎች ተመልከቱ፡**

ቀን --------------------

የተቀባይ አድራሻ

የለኪ አድራሻ-----------------

-------------------------------------------------------------------------------- መግቢያ

------------------------------------------------------------------------------ ------------- ዋና መልዕክት

------------------------------------------------------------------------------------------ መደምደሚያ

ስምና ፊርማ ----------------------

**ተግባር2. ቀጥሎ የቀረበውን ደብዳቤ ከላይ በቀርበው መሰረት ክፍሎቹን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

ጥቅምት 16-ቀን2014

ተማሪ ዳውሎ ማራናታ

ካራት 1ኛ ደረጀ ትምህርት ቤት

ፓስታ ሳጥን ቁጥር 423

ኮንሶ

ለዳዋይቶ ሾይጫ

ማሾሌ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ፖስታ ሳጥን ቁጥር 93

ማሾሌ

ውድ ወንድሜ እንደምን አለህልኝ ? እኔ ካንተ ሀሳብና ናፍቆት በስተቀር ደህና ነኝ፡፡ አንተ እንደምን አለህልኝ ፣ ቤተሰቦችህስ ደህና ናችው?

ባለፈው አመት አንተ ሰባተኛ ክፍል መማርህ የሚታወቅ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ዘንድሮ ነው ከ6ተኛ ወደ 7ኛ ያለፍኩት፡፡ ስለዚህ ለ7ኛ ክፍል የሚሆኑ ማጣቀሻ መፃሕፍትና አጋዥ መፃህፍት ስለ ቸገረኝ አንተ የተማርክባቸውን መጻሕፍቶች ካሉ እባክህን ላክልኝ፡፡ ትምህርቱን እንደጨረስኩ ወዲያው እመልስልሃለሁ፡፡ እባክህን አዘጋጅልኝ፡፡

በተረፈ በሚቀጥለው ጊዜ በደብዳቤም ይሁን በአካል እስከምንገናኝ ድረስ በሰላም ቆይልኝ ደህና ሁን፡፡

ያንተው ወንድም

ዳውሎ ማራናታ

**ተግባር3. ከላይ የቀረበውን ሞዴል የደብዳቤ አፃፃፍ መሠረት በማድረግ እናንተም በዚሁ መሰረት ለአንድ ጓደኛችሁ ደብዳቤ ፃፉ፡፡**

## ሁለተኛ ሳምንት ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ትናገራላችሁ ።
- ለቀረቡላችሁ ቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ ።

**ተግባር1 ቀጥለው የቀረቡትንቃላት በመመልከት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ።**

1. ሀሩር
2. አሽከር
3. ክርክር
4. ሚርት
5. ሲሳይ

**ተግባር2. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ" ለ "ሥር ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ ቀጥተኛ ፍቻቸውን አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ርስት | ሀ/ ስጦታ |
| 2. ሽረሽረ | ለ/ በቀላሉ የማይድን በሽታ |
| 3. ቀደሰ | ሐ/ ልዩ ችሎታ |
| 4. ባላገር | መ/ በገጠር የሚኖር |
| 5. ተሰጥኦ | ሠ/ መመኪያ |
| 6. ነቀርሳ | ረ/ ቦረቦረ |
| 7. አለኝታ | ሰ/ የግል ይዞታ |
| 8. ችሮታ | ሸ/ አመሰገነ |

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ስዋስው

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የዐረፍተ ነገር ስልቶችን አውቃችሁ ትጽፋላችሁ።

**ማስታወሻ**

**ዐረፍተ ነገሮችን ከስልት አንፃር በአራት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ እነሱም ሐተታዊ ፣ጥያቄያዊ ፣ትዕዛዛዊና አጋናኝ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ሐተታዊና ጥያቄያዊ ዐረፍተነገሮችን ለይተን እንማራለን፡፡**

1. **ሀተታዊ ዐረፍተ ነገር** አዎንታዊና አሉታዊ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

   አዎንታዊ = አበበ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡

   አሉታዊ = አበበ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ አይደለም፡፡

2. **ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገር** ጥያቄን የሚያቀርብ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

   መቼ ነው ፈተና የምንፈትነው?

   አባቴ አልመጣም እንዴ ?

**ተግባር1 ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች በሐተታዊና በጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገር ለዩአቸው፡፡**

1. ጀማል ትምህርት አይወድም፡፡
2. ሶለኔ ስንተኛ ክፍል ነች?
3. እኔ ንባብ እወዳለሁ፡፡
4. ትላንት ለምን ከትምህርት ቤት ቀረህ?

**ተግባር2 ከላይ በተማራችሁት መሰረት አምስት ሐተታዊና አምስት ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሰባት

*ሥነ- ጽሁፍ*

ከዚህ ትምህርተ በኋላ ተማሪዎች

- ቀለል ያሉ ግጥሞችን ታነባለችሁ፡፡
- ስንኝና ሀረግን ታውጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. ግጥሙን ደጋግማችሁ አንብቡትና ስለምን እንደሚያወራ ተረዱ፡፡**

**መሬትና ጥንቸል**

መሬትና ጥንቸል ፣ማህበር ገቡና ፣ጽዋ ተጣጡና ፣
መሬት የፋንታዋን ስትከፍል በጽሞና ፣
እብስ አለች ጥንቸል መክፈል ጠላችና ፣
ብትሮጠው ብትሮጠው፣
ጋራውን ተሻግራ ፣ሜዳውን አቋርጣ ፣
አልቻለችም ከቶ ከእዳዋ ልትድን ከመሬት አምልጣ::
መሬትና ጥንቸል ማህበር ገቡና ጽዋ ተጣጡና፤
እብስ አለች ጥንቸል መክፈል ጠላችና፡፡

(ደበበ ሰይፉ፣1992፣83-84)

**ተግባር2. ቀጥሎ የቀርቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ማንና ማን ናቸው ማህበር የገቡት ?
2. ማነው ሳይከፍል ለማምለጥ የሞከረው?
3. ዕዳውን ሳይከፍል ማምለጥ ችሏል ትላላችሁ?

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስምንት

ነፃ ምዕላድ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

**ማስታወሻ**

**ነፃ ምዕላድ የሚባለው ምንም አይነት ቅጥያ ምዕላድ የሌለው ወይም ከሱ ወዳነሰ ክፍል ሊከፈል የማይችል ነው፡፡**

**ተግባር ፦ ቀጥለው የቀረቡትን ምሳሌዎች አይታችሁ በምሳሌው መሰረት ስሩ፡፡**

**ለምሳሌ፡-** 1 **ሰው** - ምንም ቅጥያ ከፊትም ከኋላም የለውም ቃሉ ነፃ ምዕላድ ነው፡፡

2 **አልመጣም** - ይህ ቃል ከፊትም ከኋላም ቅጥያ አለው ከፊት - አል- ከኋላ -ም አለው፡፡ ዋናው ቃል **መጣ ነው፤** ስለዚህ ነፃ ምዕላድ አይደለም ፡፡

1. ወንድም
2. ቤታችን
3. ሰነፍ
4. ግንበኛ
5. ቆንጆ
6. ሰፊ

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

### መጠይቃዊ ቃላት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

❖ መጠይቃዊ ቃላትን በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፧

**ተግባር፦1 ቀጥለው ከቀረቡት ርዕሶች መካከል በቡድን ሆናችሁ አንዱን ምረጡና እርስ በእርስ ለምን፣ምን፣ እንዴት የሚሉትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም ተጠያየቁ፡፡**

**ምሳሌ** የቤት ሥራ መስራት ምን ይጠቅማል?

የቤት ስራ **ለምን** አትሰራም?

የቤት ስራው **እንዴት** ነው የሚሰራው?

የቤት ስራ **ለምን** እሰራለሁ /ትሰራለህ?

ባልሰራ **ምን** እሆናለሁ?

**ርዕስ**

1. ኮሮና ቫይረስ
2. የባህል መድሐኒት
3. መከባበር
4. አገራችን ኢትዮጵያ
5. ስነ - ምግባር

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሀገር ወዳድነት በሚለው ርዐስ ስር ስለ ሀገር በቀል እውቀቶች ፣ስለ ባህል መድሐኒት ቅመማ ተምራችኋል።በመቀጠልም የሀገር ፍቅር ስሜት የሚለውን ምንባብ በጥልቀት አንብባችሁ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርታችኋል። ከዚያም የግል ደብዳቤ አፃፃፍን በደንብ ተምራችሁ በተመሣሣይም ደብዳቤ ጽፋችኋል። የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ተምራችኋል። እንዲሁም የዐረፍተ ነገር ስልቶችንና ቀለል ያሉ ግጥሞችን፣ ነፃ ምዕላድን በዚህ ክፍል የተማራችኋቸው ናቸው።

**ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።**

1. የግል ደብዳቤ የሚይዛቸውን ክፍሎች ዘርዝሩ ።
2. የዐረፍተ ነገር ስልቶች በሆኑት በሐተታዊና ጥያቄያዊ አምስት አምስት ዐረፍተ ነገር ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፧
3. ነፃ ምዕላድ የሆኑ ቃላትን አምስት ፃፉ።

ምዕራፍ ሰባት

ባህል

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- በሞባይል የተቀረፁ ታሪኮችን አዳምጣችሁ ታብራራላችሁ፡፡
- ባህላዊ መረጃን አደራጅታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ምንባብ አንብባችሁ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ታወጣላችሁ፡፡
- የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴን ተጠቅማችሁ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ለቃላት አገባባዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የዐረፍተ ነገር ስልቶችን ትለያላችሁ ፡፡
- የግጥም አላባውያንን ታወጣላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

| | |
|---|---|
| ጎደሬ | ማወዳደር |
| ተጨፈለቀ | ዝግጅት |
| ማነጻጸር | አሬራ |
| ተዘርግፎ | ማጣፈጫ |

**አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ**

**ማዳመጥ፡-**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

በሞባይል የተቀረፁ ታሪኮችን ታዳምጣላችሁ፡፡

አዳምጣችሁ የምትጠየቁትን ጥያቄ ትመልሳላችሁ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ባህላዊ አስተዳደር ምንድነው?
2. ባህላዊ አስተዳደር በሁሉም ብሔረሰቦች ውስጥ ይገኛል?
3. የባህላዊ አስተዳደር ጠቀሜታው ምንድነው?

**ተግባር1. በመቀጠል መምህራችሁ በሞባይል የተቀረፀ ንግግር ያስሟችኋል ያንን አዳምጣችሁ ቀጥሎ የቀረበውን ጥያቄ መልሱ።**

1. የኧሌ ብሔረሰብ ስንት ኅሳዎችና ስንት የኅሳ መረጃዎች አሉት?
2. የኅሳ መሪ በኧሌ ብሔረሰብ እንዴት ነው የሚመረጠው?
3. ከህዝቡ ወደ ኅሳ ፣ ከኅሳ ወደ ሕዝቡ መረጃ የሚያመጡ ሰዎች ምን ይባላሉ?
4. የኅሳ መሪው ሚስት ኅሳውን መምራት የምትችለው እንዴት ነው?
5. በሳርካው አማካኝነት ግጭቱ የሚደረገው እንዴት ነው?

**ተግባር 2 ከላይ በአዳመጣችሁት መሠረት እናንተም ስለአንድ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር መረጃ በማሰባሰብ በሞባይል ቀርፃችሁ አምጥታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሟቸው።**

**አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሁለት**

**መናገር**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ስለአንድ ባህል መረጃ ሰብስባችሁ ታቀርባላችሁ።

**ቅድመ መናገር ጥያቄዎች**

1. ባህላዊ መረጃ ማለት ምንድነው?
2. ባህላዊ መረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል?
3. የራሳችሁን ብሔረሰብ ባህል እናውቃለን ብላችሁ ታስባላችሁ?

**ተግባር1. በመጀመሪያ በቡድን በመሆን ተደራጁና ስለአንድ የምታውቁት ባህል መረጃ አሰባስባችሁ ወይም በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል አቅርቡ።**

**ተግባር2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል ስሩ፡፡**

**ድህረ መናገር ጥያቄዎች**

1.ስለአቀረባችሁት የባህል አይነት መረጃ እንዴት አገኛችሁ?

2. በመረጃው ላይ ጉድለት አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

3. መረጃው ምን ያህል አስተማማኝ ነው?

4. የመረጃውስ ምንጭ ማነው?

5 የዚህ ባህል መረጃ በስርዓት እንዲቆይ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሦስት**

**ማንበብ**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ምንባቡን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ስለባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት በደንብ ትረዳላችሁ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ሀ. ባህላዊ ምግብ ምንድነው?

ለ. ባህላዊ የምግብ አሰራር ከሌላው የምግብ አሰራር በምን የሚለይ ይመስላችኋል?

**የኮንታ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት**

" ሱልሶ" " ኡለታ" ጫዲያ፣ " ኩቦ"ዋ፣ " በሩዋ" እና " ባጭራ" የኮንታ ብሔረሰብ ዋነኛ ባህላዊ ምግቦች ናቸው፡፡ " ሱልሶ" ከጥሬ ሥጋ፣ ከቅቤ ፣ ከደም ፣ ከሐሞት እና ከተለያዩ የማጣፈጫ ቅመሞች ከተዘጋጀ በኋላ በተለበለበና ክብ በተቆረጠ የእንሰት ቅጠል ላይ ለቤተሰቡ አባላት ይቀርብና በቡላ ወይም በቆጮ ይበላል፡፡ "ሲሊሶ" ከቅቤና ከአይብ የሚዘጋጅ ሲሆን ለቤተሰቡ አባላት በቡድን ይቀርባል፡፡ " ኡለታ" ከስጋ ከእንሰት ተዋጽኦዎች ከተለያዩ የእህል አይነቶች ከጎመን፣ ከቆጮ ከበቆሎ ዱቄትና እሸት አተር ይዘጋጃል፡፡ " ጫዲያ " የሚዘጋጀው ከተቀቀለ ጎደሬ ሲሆን በእንጨት ገበታ ተዘርግፎ እንዲቀዘቅዝ ከተደረገ በኋላ በመጨፍለቂያ ወይም በጫዴ ሚታ

ተቀጥቅጦ ከተጨፈለቀ በኋላ በአይብና በወተት እየተጠቀሰ ይበላል፡፡ " ኩቡዋ " ከዶሮ ስጋ በተለየ ሁኔታ የሚሰራ የብሔረሰቡ ታዋቂ ምግብ ነው፡፡ " ቦሩዋ " ከበቆሎ ፣ ከጤፍ ፣ ከስንዴና ከአጃ ዱቄት የሚዘጋጅ ነው፡፡ " ባጭራ" ከተነከረ ቡላ ከአይብ ወይም ከአሬራ ወተት የሚሠራ ሲሆን ቅቤ ተጨምሮበት የሚበላ የምግብ አይነት ነው፡፡

**/ ምንጭ፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ፕሮፋይል/**

**ተግባር 1. ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡**

ሀ. የኮንታ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ፣ የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

ለ. ከቅቤና ከአይብ የሚዘጋጅ ምግብ የትኛው ነው?

ሐ. " የጫዲያ " ምግብ አዘገጃጀት የሚሰራው ከምንድነው?

መ. በወተትና በአይብ እየተጠቀሰ የሚበላው የምግብ አይነት የቱ ነው?

**ተግባር2 . ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. " የሱልሶ" ምግብ የሚዘጋጀው ከጥሬ ሥጋና ከቅቤ ብቻ ነው፡፡

ለ. ከተቀቀለ ጐደሬ የሚዘጋጀው ምግብ " ኩቡዋ " በመባል ይታወቃል፡፡

ሐ. "ቦሩዋ" የምግብ አዘገጃጀት ከበቆሎ ፣ ከጤፍ፣ ከስንዴና ከአጃ ዱቄት የሚዘጋጅ ነው፡፡

መ. "ኩቡዋ" ከዶሮ ሥጋ በተለየ ሁኔታ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡

**ተግባር3. ከ "ሀ" ሥር ያሉትን በ "ለ " ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ " |
|---|---|
| 1. "ሲሊሶ" ፣ ጫዲያና ኡኮታ፡፡ | ሀ. "ሲሊሶ" |
| 2. ከበቆሎ ዱቄትና እሸት አተር ይዘጋጃል ፡፡ | ለ. " ባጭራ" |
| 3. ከተነከረ ቡላና ከአታብ የሚዘጋጅ ፡፡ | ሐ. " ሱልሶ" |
| 4. ከሐሞት እና ከተለያዩ ማጣፈጫ ይዘጋጃል፡፡ | |
| | መ.ባህላዊ የምግብ አይነቶች |
| 5. ለቤተሰብ አባላት በቡድን ይቀርባል፡፡ | ሠ. "ኡካታ" |

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አራት

### መጻፍ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ**

- አንቀጽን ታስፋፋላችሁ፡፡
- በምሳሌ፣ በማነጻጸርና በማወዳደር እንቀጽን ታስፋፋላችሁ፡፡

**ተግባር 1. የሚከተሉት አንቀጾች በምሳሌና በማነጻጸር የተስፋፉ ናቸው፡፡ እነዚህን በማንበብ ግንዛቤ ጨብጡ፡፡**

**1. በምሳሌ የተስፋፋ**

የኮሬ ብሔረሰብ በደቡብ ክልል የሚገኝ ሲሆን የብዙ ባህል ባለቤት ነው፡፡ ለምሳሌ ባህላዊ አስተዳደራቸው ፣ የጋብቻ ስነስርዓታቸው፣ የበዓላት አከባበራቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኮሬ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ ለየት ያለ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ቂቿላ ፣ ገንፎ፣ ባራቂጣ፣ አንጨሳ የበሬ ስጋ ተከትፎ ተጠራቅሞ ከቆየ ወተት ጋር የሚሠራ፣ ኮይቻ፣ ሥጋ ተከትፎ በቆጮ መካከል ተደርጎ የሚበላው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**2. በማነጻጸር የተስፋፋ**

የኤሌክትሪክ ምጣድና የእንጨት ምጣድ ያላቸው ልዩነት በጣም ብዙ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ምጣድ ጭስ የለውም፣ ሙቀቱም እንደ እሳት አይገርፍም፣ እንጨት መጨመር መቀነስ የሚባል የለበትም፡፡ የእንጨት ምጣድ ግን፣ ጭሱ፣ የእሳቱ ወላፈን፣ የምንጠቀመው እንጨት (እርጥብ፣ ደረቅ) ሰፊ ችግር ያለበት ነው፡፡

**ተግባር2. በምሳሌው መሰረት በምሳሌና በማነጻጸር/ በማወዳደር አንቀጽ ጻፉ፡፡**

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡፡
- ለቃላት ከአገባባቸው አንጻር ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥለው በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ።**

1. እጅግ አስከፊ ኑሮና ፈተና ገጥሟቸዋል።      -- መሰናክል
2. ይበልጥ ያሳሰባት የወንድሟ እንግልት ነበር።
3. የስነ ልቦና ባለሙያ ምክር ተቀብለዋል።

4 .ከነበረበት የጎዳና ህይወት ተላቀቀ።

5 ከእኩዮቻቸው ጋር መቦረቅ አልቻሉም።

6. ለምለምና ዘላለም ተስፋቢስ ሆነው አልቀሩም።
7. ከባድ የስራ ሸክም ተጫነባቸው።

8 የስራ ድርሻ ወይም አስተዋጽኦ ነበራት።

9 አርአያ መሆን ያስፈልጋል።

10 ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንግታ።

**ተግባር 2. ከላይ በሠራችሁት መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ።**

ሀ. ትውልድ

ለ. ሱስ

ሐ. ሀብት

መ. ለጋስ

ሠ. ደላላ

**ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**ስሞች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የተወላጠ ስሞችን አጠቃቀም አውቃችሁ ትጠቀማላችሁ።

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡትን ተወላጠ ስሞች በደንብ ተመልክታችሁ አገልግሎታቸውን ተረዱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| እኔ | አንተ | እናንተ | እሷ |
| እኛ | አንቺ | እነሱ | እሱ |

**ተግባር2. ከላይ ከቀረቡት ተወላጠ ስሞች በመምረጥ የተሰመረባቸውን ስሞች ተኩ፡፡**

1. ደጊቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡ እሷ ወደ ተምህርት ቤት ሄደች፡፡
2. አለሚቱና አበበ ተማሪዎች ናቸው፡፡
3. እኔና ወንድሜ ስለአገራችን እናስባለን፡፡
4. ተሾመ ለልጆቹ ምክር ይመክራቸዋል፡፡
5. አንቺና አለሙ ነገ ትመጣላችሁ፡፡
6. አማረ የቤት ስራውን ቶሎ ቶሎ ይሰራል፡፡

**ተግባር 3. ከላይ በተማራችሁት መሠረት ቀጥሎ በቀረቡት ተወላጠ ስሞች አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. እኔ | 5. እሱ |
| 2. አንተ | 6. እናንተ |
| 3. እሷ | 7. እኛ |
| 4. እነሱ | 8. አንቺ |

**ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሰባት**

**ስዋስው**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የዐረፍተ ነገር ስልቶችን መርጣችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡

**ተግባር 1– ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመመልከት ቀጥለው የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ትዕዛዛዊ ወይም አጋናኝ በማለት መልሱ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንዳትነካ፡፡ - ትዕዛዛዊ

ለ. ፈረስ የሚያስጋልብ ቤት፡፡ - አጋናኝ

1. አለምን ያስደመመ ንግግር፡፡
2. ሰዓት ሳይደርስ ከክፍል አትውጡ፡፡
3. በጣም የምትገርም ጎል!
4. ወጧ እጅ ያስቆረጥማል፡፡

5. ማስክ ሳታደርግ ከቤት አትውጣ፡፡
6. የቤት ስራውን ሰርታችሁ አምጡ፡፡
7. ጩኸቱ ምድር ያናውጣል፡፡
8. ምግብ ከመብላትህ በፊት እጅህን ታጠብ

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስምንት

### የግጥም አላባውያን

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የስንኝ ምንነት ታብራራላችሁ፡፡

የሀረግ ምንነት ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀርበውን ምሳሌ በቡድን በመሆን አንብቡና ተረዱት፡፡**

**ስንኝ የግጥም አንድ መስመር ነው**

**ምሳሌ፡-**

አይዞህ የኔ ጌታ ነገርህን አርትሳ (ስንኝ)1

አለስልሰህ ዝራ የስንዴውን ማሳ፡፡ (ስንኝ)2

በዚህ ግጥም ውስጥ ሁለት ስንኞች አሉ ማለት ነው፡፡

**ሀረግ፡- የስንኝ እኩሌታ ሆኖ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ነው፡፡**

**ምሳሌ፡-**

ቅሰሙ ወጣቶች ፣ጥበብን ተግታችሁ፣

ስንፍና በፍፁም ፣አይግባ ልባችሁ፣

በዚህ ግጥም ውስጥ አራት ስንኞች አሉ፡፡

**ተግባር2. ከላይ በተመለከትነው ግጥም ውስጥ ሁለት ስንኞችና አራት ሐረጎች አሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ ከቀረበው ግጥም ስንኞችንና ሃረጎችን አውጡ፡፡**

አርሶ መሸመት ፣ተኩሶ መሳት፣

ይለበልባል፣ እንደ እግር እሳት፡፡

አረንዛ ውጦኝ፣ እስከ ጉልበቴ፣

ሽልም አወጣኝ ፣የነፍስ አባቴ፡፡

ያላረሰ ጎበዝ ፣እርፍ ያልነቀነቀ፣

ስልቻውን ይዞ፣ ለቃርሚያ ዘለቀ፡፡

1. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

ሀ. 10 ለ. 8 ሐ. 6 መ. 4

2. ግጥሙ ስንት ሀረጎች አሉት?

ሀ. 12 ለ. 14 ሐ. 16 መ. 18

3. ግጥሙ ስንት መነሻ ሀረጎች አሉት?

ሀ. 4 ለ. 6 ሐ. 8 መ. 10

4. የግጥሙ አንድ ስንኝ ስንት ሀረግ አለው?

5. ሀ. 12 ለ. 2 ሐ. 6 መ.4

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ትርጉም/ፍች ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማንበብ በምን በምን ጉዳይ ላይ እንደተነገሩ ወይም ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ - ጥንቃቄን
2. ስጋ በልቶ ከብስና ጎመን በልቶ በጤና፡፡
3. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ፡፡
4. አለባበሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ፡፡
5. እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች፡፡
6. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ፡፡
7. ለሰው ብሎ ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ፡፡
8. ሀሜትና ጅራት ከበስተ ኂላ ነው፡፡

**ተግባር2. ቀጥለው በቀረቡት ሁኔታዎች ዙሪያ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አዘጋጅታችሁ / ጽፉችሁ በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. መቸኮል መጥፎ እንደሆነ

2. ሴቶችን የሚያሞግሱ
3. መስራትን የሚያበረታቱ
4. ኃላፊነትን የሚነግሩ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ መምህራችሁ ያቀረቡላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች ሰርታችኋል፡፡ በመቀጠልም የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ስለ ሀገር ባህል መድሀኒት ምንነት ተረድታችኋል ፤የቀረቡትንም ጥያቄዎች ሰርታችኋል፡፡ በተመሳሳይ የሀገር ፍቅር ስሜት የሚለውን ምንባብ አንብባችሁ ከምንባቡ የወጡ ጥያዌዎችን ሰርታችኋል፡፡ ስለ ግል ደብዳቤ አፃፃፍ ተምራችሁ የሙከራ ደብዳቤ ጽፋችኋል፡፡ በክፍለትምህርት ስድስት ከዐረፍተ ነገር ስልቶች ፣ ሐተታዊና፣ ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገርን ተምራችሁ ዐረፈተ ነገር መስርታችኋል፡፡ በመቀጠልም የቀረበውን ግጥም አንብባችሁ ስንኝና ሀረግን ለይታችሁ አውጥታችኋል፡፡ ከዚያም የነፃና የጥገኛ ምዕላዶችን ልዩነት አውቃችሁ ሰርታችኋል፡፡ በመጨረሻም መጠይቃዊ ቃላትን ተጠቅማችሁ የተለያዩ ንግግሮችን አድርጋችሁ ምዕራፉን አጠናቃችኋል፡፡

**ቀጥለው ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን በመነጠል አሳዩ፡፡**

1. አስመጣው
2. ደራሲው
3. ሰራተኞች

**ቀጥለው የቀረቡትን ቃላትና ሀረጎች በጽሁፍ አብራሩ፤፡**

1. ስንኝ
2. ሐረግ

**አራት ሐተታዊና ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ አሳዩ፡**

**ምዕራፍ ስምንት**

**መቻቻል**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦**

- *በሞባይል ተቀርፀው የመጡ ታሪኮችን አዳምጣችሁ ስለአዳመጣችሁት ባሕል ጠንካራና ደካማ ጎን ትናገራላችሁ፡፡*
- *ቀለል ስላሉ የመስክ ጉዞዎች ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡*
- *ገላጭ ምንባቦችን አንብባችሁ ችሎታችሁን ታዳብራላችሁ፡፡*
- *የድርሰት አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡*
- *ለአማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡*
- *አምስቱን የቃል ክፍሎች ትዘረዝራላችሁ፡፡*
- *መቼትንና ዋና ገጸ ባህሪያትን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡*

**ቁልፍ ቃላት**

| | | |
|---|---|---|
| *መቻቻል* | ውበት | *መገላት* |
| የኑሮዘዴ | *መንስኤ* | ችግር ፈቺ |
| ልዩነት | *መፍትሔ* | ዘላቂ |

አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ

*ማዳመጥ*

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

-በሞባይል ተቀርጾ የሚቀርብላችሁን ንግግር አዳምጣችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡

*ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች*

ሀ. እርቅ ሲባል ምንድነው?

ለ. በባህል ሁለት ወገኖችን እንዴት ነው ማስማማት የምንችለው?

ሐ. በእርቅ ላይ የሚገኙ አካላት ስንት ናቸው?

**ተግባር ፦በመቀጠል መምህራችሁ የሚያሰሚችሁን በሞባይል የተቀዳ ንግግር አዳምጣችሁ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የባልና የሚስት እርቅ ፣ ከሌሎች እርቆች ያለው ልዩነት ምንድነው?
2. ባህላዊ እርቅ አገር በቀል እውቀት ነው ትላላችሁ?
3. በእርቅ ጊዜ መቻቻል በሁለቱ ታራቂዎች ዘንድ እንዲኖር የባህሉ ሽማግሌዎች ምን ያደርጋሉ ?
4. ባሕሉን ጥሶ እርቁን እምቢ ያለ ሰው በባህሉ የሚወሰድበት እርምጃ ምንድነው?
5. አንድ ጊዜ እርቅ ከተፈፀመ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ ማኩረፍ እንደሌለ ባህሉ እንዴት ያስታውቃል?

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሁለት

### መናገር

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

-በመስክ ጉዞ ላይ የተመለከታችኋቸውንና የሰበሰባችኋቸውን መረጃዎች በቃል ለክፍል ትናገራላችሁ።

## ቅድመ ንግግር ጥያቄዎች

ሀ. የመስክ ጉዞ ምንድነው?

ለ. በመስክ ጉዞ ላይ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ ይቻላል?

ሐ. የመስክ ጉዞን በመረጃ አደራጅቶ በንግግር ማቅረብ ይቻላል?

**ተግባር፦ ተማሪዎች ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ቀለል ያሉ የመስክ ጉዞዎችን አመቻችታችሁ በመሄድ ከመስክ ጉዞው ያገኛችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። በመቀጠልም ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የመስክ ጉዟችሁ እንዴት ነበረ?
2. በጉዟችሁ ምን ምን ተመልክታችኋል?
3. የመስክ ጉዞ ያደረጋችሁበት ቦታ እንዴት ነበር?

4. መረጃዎችን እንዴት ነው ያሰባሰባችኋቸው?

5. መረጃውን በቃል ስታቀርቡ የተፈጠረ ችግር ነበር ?

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ተቻችሎ መኖር እንዴት እንደሆነ ታስረዳላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. መቻቻል ወይም ተቻችሎ መኖር ማለት ምንድነው?

ለ. ልዩነቶቻችን ለኛ ውበታችን እንጂ ግጭት ሊሆኑ አይገባም ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. በመሀከላችን የሚከሰተውን ግጭት እንዴት ነው መፍታት የሚቻለው?

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ በኋላ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

## ተቻችሎ መኖር

በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች የተገናኙት በስራ ምክንያት ከተለያየ ቦታ መጥተው ነበር፡፡ ሁለቱም ተከራይተው በአንድ ቤት ነው የሚኖሩት፡፡ ካላቸው መተሳሰብ አንጻር አንዱ ከስራ ቀድሞ ቢመጣ ለሁለቱም ምግብ አዘጋጅቶ ነው የሚጠብቀው፡፡ በተመሳሳይ ሌላውም ቢመጣ እንደዚያው ነው የሚያደርገው፡፡ ልብስ ለማጠብ እንኳ አንዱ ቢያስብ የራሱን ብቻ መርጦ አያጥብም፡፡ የሁለቱንም ወስዶ ነው የሚያጥበው፡፡ ይህ መተሳሰባቸው በብዙ ሰዎች ዘንድ ይደነቅላቸው ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ የሚያስደንቀው በሁለቱ መካከል ግጭት ቢፈጠር ቁጭ ብለው በውይይት ይፈቱታል እንጂ ወደ ጥል አይገቡም፡፡ ከነሱ በላይ ቢሆን እንኳ ችግራችንን ሊፈታልን ይችላል የሚሉት ሰው ጋ ሄደው ለችግሩ መፍትሄ ይፈልጋሉ፡፡ ከዚያም ችግራቸውን ፈትተው ይመለሳሉ፡፡ ያ እንኳ ባይሆን ልዩነታቸውን በመቻቻል ሸፍነው እንደድሮአቸው ይኖራሉ፡፡

የነዚህ የሁለቱ የመንግስት ሰራተኞች የኑሮ ዘይቤ ለኛ የሚያስተምረን ነገር ብዙ አለ። በየጊዜው የሚያጋጥሙንን ችግሮች በመቻቻል መንገድ መፍትሄ መስጠት እንደሚገባ ያስተምረናል። የኛን ልዩነት እያጎሉ ልዩነታችን እንዲሰፋ የሚያደርጉ ሰዎችን እየተቋቋምን ልዩነታችንን እንደውበት አድርገን በማየት በመቻቻል መኖር ይኖርብናል።

በአገራችንም ደረጃ ቢሆን አገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን ብዙ ልዩነቶችና ፍላጎቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህን ልዩነቶችና ፍላጎቶች እንደውበት በመቁጠር በመቻቻል መኖርና ፍላጎታችንን ደግሞ በትዕግስትና በስርዓት ለሟሟላት መታገል ይኖርብናል።

(ለማስተማሪያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ)

**ተግባር2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።**

1. ልዩነታችን ሁልጊዜ የግጭት መንስኤ ሊሆን አይገባም።
2. የሁለቱ መንግስት ሰራተኞች የኑሮ ዘይቤ ተቻችሎ መኖር በውስጡ የለበትም።
3. አገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰብ አገር ነች ሲል መብዛታችን ውበታችን መሆኑን ያሳያል።
4. ልዩነታችንን የሚያሳዩ ሰዎች ግጭታችንን የሚፈልጉ ናቸው።
5. ፍላጎት በአንድ ጊዜ የሚሟላ ሳይሆን ዘላቂነት ያለው ነው የሚለው አባባል ትክክል ነው።

**ተግባር3. ቀጥለው ከምንባቡ ለወጡት ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍችያቸውን ስጡ።**

1. ውበት
2. የኑሮ ዘይቤ
3. ችግር ፈቺ
4. ልዩነት
5. መፍታት

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አራት

### መጻፍ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

የድርሰት አጻጸፍ ሂደትን ተከትላችሁ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡

ማስታወሻ


ድርሰት በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በአዕምሮ ወይም በወረቀት ላይ የሰፈረን ንድፍ ተከትሎ የሚፃፍ ጽሁፍ ነው፡፡ የፈጠራ ጽሁፎችም ድርሰት ናቸው፡፡ በአንድ አንቀጽም የተጻፈ ቢሆን እንኳ ድርሰት ነው፡፡

ድርሰት ከመጻፋችን በፊት የድርሰት ክፍሎችንና የድርሰት ዓይነቶችን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ አሁን በዚህ ክፍል የድርሰት ክፍሎችን ታያላችሁ፡፡ የድርሰት ክፍሎች ሦስት ናቸው፡፡ እነዚህም **መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ** ናቸው፡፡

የድርሰት መግቢያ፡- ፀሐፊው የድርሰቱን ርዕስ ጉዳይ አጠቃላይ አቅጣጫ ለአንባቢው የሚጠቁምበትና ስለድርሰቱ ጭብጥ ፍንጭ የሚሰጥበት ነው፡፡

የድርሰቱ ማዕከላዊ አካል/ ሀተታ፡- በመግቢያውና በመደምደሚያው መካከል የሚገኝና የድርሰቱ ዋነኛ ሀሳብ የሚተነተንበት ነው፡፡

መደምደሚያ፡- የድርሰቱ ጽህፈት የሚጠናቀቅበት ወይም የሚቋጭበት የመጨረሻው ክፍል ነው፡፡




**ተግባር1. መምህራችሁ በወረቀት አዘጋጅተው የሚሰጧችሁን ድርሰት በመመልከት በቡድን ሆናችሁ የመግቢያ አንቀጽ፣ ሀተታውንና መደምደሚያውን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

**ተግባር2. የሚከተለውን የመግቢያ አንቀጽ ተመልክታችሁ በሱ መሰረት ስለ አንድ ርዕስ የመግቢያ አንቀጽ ለመጻፍ ሞክሩ፡፡**

**የቡና ቤት ስዕሎች**

ሰአሊ አይደለሁም፣ ትንሽ ልሞክር ብል ድሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለ አራት እግር ጠረጴዛ ነው እምስለው፡፡ ሆኖም አንድን ስዕል ማየት ብቻ ሳይሆን ማስተዋል፣ ውበቱን፣ መልዕክቱን መገንዘብ- በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሰረት መተቸት - ደስ ይለኛል፡፡ ሙያው ባይኖረኝም አንዳች እርካታ አገኝበታለሁ፡፡ ከዚህ በመነሳት ስለ ቡና ቤት ስዕሎች አንዳንድ የመሰሉኝን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ፡፡

(መስፍን ሀብተማርያም / 1976፣ ገጽ 12/ የቡና ቤት ስዕሎችና ሌሎች ወጎች)

**ተግባር3. ቀጥሎ የቀረበውን መደምደሚያ ተመልክታችሁ በሱ መሠረት ለመጻፍ ሞክሩ፡፡**

የሚወዱትን ዕቃ ጥሩነት፣ ወይም ምትክ የማይገኝለት መሆኑን ለመግለጽ፣ የጥንት ነው እስኪ ገምት አያቴ የጠጡበት ሲኒ፣ ቅድመ አያቴ የገዙት ቁም ሳጥን "እያሉ የአሮጌ እቃ እድሜ ሲያራዝሙ የራስን ማሳነስ ምን ይባላል? እድሜ መስታወት ነው" የከርሞ ሰው ይበልህም" ጥሩ ምርቃት ነው፡፡

(መስፍን ሀብተማርያም ፣ 1976 ፣ 130/ እድሜ)

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

እማሬያውና ፍካሬያዊ ፍች

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ለቃላት እማሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የቃላትን ፍካሬያው ፍች ትናገራላችሁ፡፤

**ተግባር1. የሚከተሉትን ቃላት በቡድን በመሆን አጥኗቸው ፡፡**

| ቃል | እማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| ሀ. መሰላል | መወጣጫ | ረጅም |

| | | |
|---|---|---|
| ለ. ቀፎ | የንብ ማርቢያ | ባዶ |
| ሐ. ቆቅ | የአዕዋፍ ዘር | ብልጥ |
| መ. አንበሳ | የዱር አራዊት | ደፋር |
| ሠ. ድንጋይ | አለት | የማይገባው |

**ተግባር2. ከላይ በተመለከታችሁት ምሳሌ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተሰጧችሁን ቃላት እማሬያዊ ፍች ጻፉ፡፡**

ሀ. እባብ

ለ. አህያ

ሐ. አሳማ

መ. ነቀዝ

ሠ. ቀዳዳ

**ተግባር3. ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃላት ፍካሬያው ፍች ጻፉ፡፡**

ሀ. እንጀራ

ለ. እሳት

ሐ. ወንፊት

መ. ውሻ

ሠ. ዱባ

**ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**ስዋስው**

**የቃል ክፍሎች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የስም ምንነት ታብራራላችሁ፡፡
- ቅጽልን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. መጠሪያ የሆኑ ስሞችን ተመልከቱ**

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ህልም | ደብተር |
| ፈረስ | ጠረጴዛ |
| ዳውሮ | ሕዝብ |

ሀዲያ ሰው

መሀመድ አስተማሪ

**ተግባር2. ቅጽሎችን ከዚህ በታች ተመልከቱ**

የዋሀ አስተዋይ

ደግ ትንሽ

ወፍራም መጥፎ

ታታሪ ትሁት

ሰነፍ ጀግና

**ተግባር3. በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. ሰነፍ ሰው ስራን አይወድም፡፡

ለ. ተሾመ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

ሐ. ዳንችሌ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡

መ.ሙስጠፋ መጽሐፍ ገዛ፡፡

ሠ. ረዥሙ ልጅ መጣ፡፡

ረ. በሩ ስላረጀ በሰበሰ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሰባት

ሥነ ጽሁፍ

**የልቦለድ አላባውያን**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ከልቦለድ ውስጥ ዋና ገጸባህሪያትን ታወጣላችሁ፡፡
- የልቦለዱን መቼት ትናገራላችሁ

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ከልበወለድ ውስጥ ተቀንጭቦ የወጣ ነው፡፡በዚህ ምንባብ ውስጥ ታሪኩን የሚያከናውነውንና ታሪኩ የሚከናወንበትን ቦታ በቡድን በመሆን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

‹‹ --- ምኞቴ ከሰፈሩ በሚገኝ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ ትምህርቱን ይቀጥላል፣የመጀመሪያው እለት ትምህርት ቤት ውሎ ሲገባ እናቱን ከእግር

ጥፍራቸው እስከ ራስ ጠጉራቸው እየተጥመለመለ በመሳም የእናት ፍቅሩን ለመግለጽ ሞክሮ›› እማዬ በህይወቴ ዘመን ከአንቺ ለምጠይቃቸው ጥያቄዎችና ሐሳቦች ሁሉ እገዛለሁ፡፡» አላቸው፡፡

ወይዘሮ በለጥሻቸው የምኞቴን ክቡርና ግዙፍ መልዕክቶች ሰምተው፣ያኔውኑ የሚፈልጉትን ደረጃ የደረሰ መሰላቸው፣ወደር በሌለው ዓይን አሻቅበው አዩና‹ ምኞቴ ልሳምህ ›ብለው ጉንጮቹን አገላብጠው በመሳም፣ዛሬውኑ የት እንደምትደርስ መገመት ችያለሁ፡፡ ለሁሉም መልካም መሳካት የተጨመረበት ሆኖ የሚኙ አባትህን ፍላጎትና ምኞት ተሟልቶ ለማየት ያብቃን› አሉት፡፡....«

1. በዚህ የልብወለድ ታሪክ ውስጥ ገጸ ባህሪያቱ እነማን ናቸው?
2. በዚህ ታሪክ ውስጥ መቼት አለ? ካለስ የት ነው?
3. ታሪኩ ስለማን ነው እየተነገረ ያለው?
4. ወይዘሮ በለጥሻቸው ስለማን ነው የሚያወሩት?

**ተግባር2. ከላይ በሰራችሁት መሰረት የተለያዩ ልብወለዶችን በመፈለግ አንዱን ምዕራፍ መርጣችሁ በማንበብ ገጸባህሪያቱንና መቼቱን ለይታችሁ በማውጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስምንት

## የቃል ክፍሎች

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የቃል ክፍሎችን አምስቱንም በምሳሌ ታሳያላችሁ፡፡
- ስለመስተዋድድ፣ተውሳከግስና ግስ አውቃችሁ በጽሑፍ ታሳያላችሁ፡፤

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡትን ምሳሌዎች በቡድን በመሆን ተመልከቷቸው፡፡**

**መስተዋድዶች፡-** እንደ፣ስለ፣ከ፣ለ፣ ወ.ዘ.ተ.

**ምሳሌ**-አስቴር እንደ አልማዝ ቆንጆ ነች፡፡

ካሳ ከጎጃም መጣ፡፡

ስለሰው ማውራት አልወድም፡፡

**ተወሳከ ግሶች፡-** ገና፣ክፉኛ፣ቶሎ ወ.ዘ.ተ

**ምሳሌ፡-** አለሙ <u>ገና</u> አልመጣም፡፡

ልጁ <u>ክፉኛ</u> ታሟል፡፡

**ግሶች፡-** በላች፣ይመጣል፣መጣ ወ.ዘ.ተ.

**ምሳሌ፡-** አለሚቱ ምሳዋን <u>በላች</u>፡፡

ወንድሜ ዛሬ <u>ይመጣል</u>፡፡

ልጁ ትምህርት <u>ይማራል</u>፡፡

**ተግባር2. ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች እንደተረዳችሁት ቀጥለው ከቀረቡት ቃላት ውስጥ መስተዋድዶችን ለብቻ፣ተውሳከግሶችን ለብቻ፣ግሶችን ለብቻ በቡድን በመሆን ለዩ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. ነበር | 6. አገኘሁ |
| 2. ወደ | 7.ነገ |
| 3. ሸጠው | 8.ከ |
| 4. ምንኛ | 9.መጡ |
| 5. በ | 10.ለመደ |

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## የቃላት ቀጥተኛ ፍች

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የቃላትን ቀጥተኛ ፍች በትክክል ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር 1. ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

1. ጥገኛ
2. በአካል
3. ገንቢ
4. አቃለለ
5. ግልጽ
6. ተስማሚ

**ተግባር2. ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፧**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አስተካከለ | ሀ .ጠባብ |
| 2. ታየ | ለ. ከለከለ |
| 3. ሰፊ | ሐ. ቀጨጨ |
| 4. ሰጠ | መ. አበላሸ |
| 5. ቀረበ | ሠ. ጠፋ |
| 6. አደገ | ረ. ራቀ |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕረፍ በሞባይል የተቀረጸ አገር በቀል እውቀትን አዳምጣችሁ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች በቃል መልሳችኋል‹፡፡ የመስክ ጉዞ በማድረግ መረጃ አሰባስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችኋል፡፡‹ በመቀጠልም ገላጭ ምንባብ ቀርቦላችሁ በማንበብ መልእክቱን ተረድታችኋል‹፡፡የድርሰትን ምንነትና የድርሰት ክፍሎችን ተምራችኋል፡፡ በተጨማሪም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን ከነልዩነታቸው አውቃችኋል፡፡‹ የቃል ክፍሎችንም የተማራችሁ ሲሆን በመጨረሻም ከልብወለድ አለባውያን ሁለቱን ገጸ ባህሪያትንና መቼትን ተምራችሁ ምዕራፉን አጠናቃችኋል፡፡

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተመልክታችሁ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን አውጡ፡፡**

1. ሰረቀ
2. ልብ
3. ለም
4. ዋርካ
5. ፍሬ

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጸሁፍ መልሱ፡፡**

1. የድርሰት ክፍሎችን በጽሁፍ አሳዩ፡፡
2. አምስቱን የቃል ክፍሎች ጽፋችሁ ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጡ፡፡
3. ሁለቱን የልብ ወለድ አለባውያን ግለጹ፡፡

ምዕራፍ
ዘጠኝ

ተላላፊ
በሽታዎች

**ከዚህ ምዕራፍ ፡- ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የሚቀርብላችሁን ጥያቄ አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ ፡፡
- ኮሮና ቫይረስ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ታብራራላችሁ፡፡
- ተራኪ ምንባቦችን አንብባችሁ ችሎታችሁን ታዳብራላችሁ ፡፡
- ተራኪ የሆኑ ድርሰቶችን ትጽፋላችሁ ፡፡
- ለቃላት እማሪያዊና፣ፍካሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የስርወ ቃልን ምንነት ትረዳላችሁ፡፡
- የልቦለድ አላባውያንን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- ስማዊ ሀረግን ትመሰርታላችሁ ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

| | |
|---|---|
| ማስክ | የመተንፈሻ አካል |
| ንክኪ | የሳንባ ምች |
| መጠርጠር | መተላለፊያ መንገድ |

**አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ**

**ማዳመጥ**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

በሽታዎች ተላላፊ ናቸው የሚባሉት እንዴት ነው ?

በሽታዎች የሚተላለፉባቸው መንገዶች ምንድናቸው ?

ከተላለፊ በሽታዎች እንዴት መጠንቀቅ ይቻላል፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከአዳመጣችሁ በኂላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ተላላፊ በሽታዎች ፣በመነካካት፣በትንፋሽ ፣ወዘተ ይተላለፋሉ ማለት ምንን ይገልፃል?
2. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዴት ያሉ ናቸው?
3. በተላላፊ በሽታ የተያዙ ሰዎችን እንዴት ነው የምናስታምመው?
4. ከተላላፊ በሽታዎች እንዴት መካላከል ይቻላል?
5. ያዳመጣችሁት ምንባብ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሁለት

### መናገር

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች**

- የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን አውቃችሁ ትጠነቀቃላችሁ ፡፡
- ኮሮና ቫይረስ ከሚያስከትላቸው ችግሮች እራሳችሁን ትከላከላላችሁ ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ግለጹ፡፡**

| | |
|---|---|
| ኮሮና ቫይረስ | ሳኒታይዘር |
| ኮቪድ 19 | አልኮል |
| ማስክ | እጅን በሳሙና መታጠብ |

**ተግባር2. ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች በመምረጥ በቡድን በመሆን ተወያይታችሁበት የተወያያችሁበትን ለክፍል በንግግር አቅርቡ፡፡**

1. የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶች፣
2. ኮሮናን የመከላከያ መንገዶች ፣
3. ኮሮና ቢይዘን ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ፣

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሦስት

### ማንበብ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡

የኮሮና ቨይረስ መተላለፊያ መንገዶችን አውቃችሁ ትናገራላችሁ፡፡

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ/ የኮሮና ቫይረስ ምልክቶች ምን ምን ናችው?

ለ/ አንድ ሰው በኮሮና ቫይረስ መያዙን እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

ሐ/ በኮሮና መያዙን ካወቀ ማድረግ ያለበት ጥንቃቄ ምንድነው?

**ተግባር1. ምንባቡን ጥንድ በመሆን አንብቡ፡፡**

### ኮሮና ቫይረስ (COVID 19)

ኮሮና ቫይረስ በቻይናዋ ውሃን ግዛት ተነስቶ ከቻይና ውጪ ወደ በርካታ አገራት ተዛምቷል፡፡ ኮሮና ቫይረስ ከቀላል እስከ ከባድ የመተንፈሻ አካል ህመም የሚያስከትል የቫይረስ ዝርያ ሲሆን ሞትን ሊያስከትል የሚችል ህመም ነው፡፡ የኮሮና ቫይረስ በሽታ የመተላለፊያ መንገዶች ብዙ ቢሆኑም ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም በሽታው ያለበት ሰው ሲያስነጥስ ፣ባልበሰሉ ምግቦች፣ ከታማሚው ሰው ጋር በሚደረግ የቅርብ ንኪኪ ይተላለፋል፡፡ ይህንን በሽታ ለመከላከል አፍና አፍንጫን በማስክ መሸፈን እጅንና ፊትን ወይም ሌሎች መገልገያዎችን በደንብ በሳሙና ማጠብ ፣ሰው በበዛባቸው ቦታዎች ላይ አለመገኘት፣ ከማንኛውም ሰው በሁለት እርምጃ መራቅ፣ በበሽታው ከተያዙ ሰዎች ጋር ንኪኪ አለማድረግ፣ ናቸው፡፡ የበሽታው ምልክቶችም በበሽታው የተያዙ ሰዎች ላይ ይታያሉ፣ እነሱም ትኩሳት፣ ሳል፣ የትንፋሽ መቆራረጥ፣ እና የመተንፈስ ችግር ምልክቶች ይታዩባቸዋል፡፡ በሽታው በጠናባቸው ሰዎች ላይ ደግሞ እንደሳንባ ምችና ከባድ የመተንፈሻ አካላት ህመም ይስተዋላል፡፡ በበሽታው ስለመያዛቸው የጠረጠሩ ሰዎች ማድረግ ያለባቸው ነገር ከላይ የተጠቀሱትን ምልክቶች እንዳየን ወዲያውኑ በአቅራቢያ ወደሚገኝ የጤና ተቋም መሄድ፣ በምናስልበትና በምንናስነጥስበት ጊዜ በሽታው

ወደ ጤነኛ ሰው እንዳይተላለፍ አፍና አፍንጫን በክርንና በመሀረብ ወይም በሶፍት መሸፈን፡፡ማስክ ማድረግ ፣የተጠቀምንበትን ነገር በአግባቡ በቆሻሻ መጣያ በመጣል ማስወገድ፡፡

(ከቢቢሲ አማርኛ ድረ ገጽ ተሻሽሎ የተወሰደ)

**ተግባር 2. ከላይ የቀረበውን ምንባብ ደጋግማችሁ በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ ፡፡**

1. ከሮና ቫይረስ ((COVID 19) በመጀመሪያ የተነሳው ከየት ነው?
2. የመተላለፊያ መንገዶቹ ምን ምን ናቸው?
3. በሽታው የጠናበት ሰው ምን አይነት ችግር ያጋጥመዋል?
4. ላለመያዝ ምን አይነት ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል?

**ተግባር3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ኮሮና ቫይረስ የለም የሚሉ ሰዎች ተሳስተዋል፡፡
2. ይህ በሽታ እስከሞት የሚያደርስ ነው፡፡
3. ማስክ በማድረጋችን ብቻ በሽታውን መከላከል እንችላለን፡፡
4. የበሽታው ምልክቶች ትኩሳት፣ሳል፣የትንፋሽ መቆራረጥ ሊሆን ይችላል፡፡
5. በሽታ የተስፋፋው በተወሰኑ አገራት ብቻ ነው፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አራት

### መፃፍ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

ስለተራኪ ድርሰት ምንነት  ታስረዳላችሁ፡፡

አንድ ርዕስ መርጣችሁ ተራኪ ድረሰት ትጽፋላችሁ፡፡

### ማስታወሻ

**ተራኪ ድርሰት አንድ ነገር ወይም ሁኔታ ወይም ታሪክ ፣ወይም ድርጊት መቼ እንደተፈፀመ ፣የት ተጀምሮ የት እንደተፈፀመ ፣ ከጊዜ አንፃር በተከታታይ የሚያቀርብ ነው፡፡ይህም ማለት ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይም የሚያትት ጽሁፍ ነው፡**

**ተግባር1. በምዕራፍ ስምንት ላይ ስለድርስት አካላትና ስለ ድርስት አጻጻፍ የተማራችሁትን መምህራችሁ በክለሳ መልክ ያቀርቡላቸኋል፡፡ ከዚያ በመነሳት ቀጥሎ የቀረበውን የተራኪ ድርሰት ምሳሌ አንብቡ፡፡**

**ምሳሌ፡-** - የተወለድኩት በ1935 ህዳር 6 ቀን ነው፡፡ ለወላጆቼ ሦስተኛ ልጅ ነኝ፡፡ ምናልባት የአምስት ወይም የስድስት ዓመት ልጅ ሆኜ መጀመሪያ የቄስ ትምህርት ቤት ገብቼ በደንብ ተምሬአለሁ፡፡በኮከበ ጽባሕ ትምህርት ቤት (የፈረንጆች ትምህርት ቤት) ገብቼ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን እዛው አጠናቅቄ አንድ አመት ካስተማርኩ በኋላ በ1955 የኒቨርሲቲ ገብቼ በ1959 ከአርትስ **ፋካሊቲ** ከዛሬው የኢትዮጲያ ስነ ጽሁፍ ክፍል ተመርቄያለሁ፡፡ አንድ ዓመት በተመረቅኩበት ክፍል በረዳትነት አስተምሬ ወደ አሜሪካ ሄጄ እንግሊዘኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በማስተማር በተለይም **በሶሲዩ ሊንጎስቲክስ** በሚባል ዘርፍ **የኤም ኤ** ድግሪዮን አግኝቼ ተመልሼ የ66 አብዮት እስከፈነዳበትና በዕድገት በህብረት ዘመቻ እስክሰማራ በዩኒቨርሲቲ አስተምሬለሁ፡፡ በ1968 **ግድም** ከደርግ መንግስት ጋር በነበረኝ ቅራኔ ወይም ጠብ ተሰድጄ በስነ ጽሁፍ **ፒኤችዲ** ዲግሪ ይዤ ተመልሻለሁ ከመጣሁ አምስት ዓመት ሊሆነኝ ነው፡፡

(ሪፖርት መጽሔት 1993 ገጽ 16 የተወሰደ)

**ተግባር2. ከላይ የቀረበውን ተራኪ ድረሰት በደንብ ተመልክታችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ታሪኩ ስለ አለፈ ታሪክ ነው የሚናገረው?
2. የታሪኩ ቅደም ተከተል ምን አይነት ነበር?
3. የሚተርከው ስለምንድነው?
4. ከድርሰቱ ስለተራኪ ድርሰት ምን መረዳት ትችላላችሁ?

**ከላይ የቀረበው ተራኪ ድርሰት የሚናገረው ስለ አለፈ ታሪክ ነው፡፡ ይህም ታሪክ ስለአንድ ሰው የህይወት ታሪክ ሆኖ ከተወለደበት ቀን አንስቶ አሁን እስከአለበት ደረጃ ድረስ ያለውን ተከታታይ ታሪክ ነው አንድ ባንድ የነገርን ፡፤**

**ተግባር3 . ከላይ በቀረበው ተራኪ ድርስት መሰረት በአንድ አንቀጽ አንድ ተራኪ ድርሰት ጽፋችሁ በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ፍንጭ ፡- የምትጽፉት ስለ አለፈ ታሪክ መሆን አለበት ፡፡

የጊዜ ቅደም ተከትሉ መጠበቅ አለበት ፡፡

የትና መቼ እንደተፈጸመ መገለጽ አለበት፡፡

ቢቻል መግቢያ ሀተታና መደምደሚያ ቢኖረው ጥሩ ነው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አምስት

ቃላት

እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች -**

ለቃላት እማሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ ፡፡

ለቃላት ፍካሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ሀ/ ጅሎ ከባለቤቱ ጋር ስለ አልተስማማ ቤቱ ፈረሰ ፡፡

ለ/ በራሶ እሳት የሆነች ልጅ አለችው፡፡

ሐ/ ሚስማሩ የደያሶን ሽሚዝ ሸረከተው፡፡

መ/ የልጁ አካሄድ ልክ እንደ ኤሊ ነው፡፡

ሠ/ ሰውዬው ሰው የሚለውን የማይሰማ ድንጋይ ነው፡፡

**ተግባር2. የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ በዐረፍተ ነገር ውስጥ አስገብታችሁ አሳዩ ፡፡**

| | |
|---|---|
| ሀ/ ንብ | መ/ እርግብ |
| ለ/ እስስት | ሠ/ ቋንጣ |
| ሐ/ ድንጋይ | ረ/ ምስጥ |

**ተግባር3. የሚከተሉትን ቃላት አማሬያዊና ፍካካሬያዊ ፍች ፈልጋችሁ ጻፉ።**

| | ቃሉ | የቃሉ አማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| ሀ | ቆቅ | | |
| ለ | መብረቅ | | |
| ሐ | ጨርቅ | | |
| መ | በርሜል | | |
| ሠ | ቀፎ | | |

**ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**ስዋስው**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

ስለ ስርወ ቃል ምንነት ታውቃላችሁ።

ከቃል ውስጥ ስርወ ቃልን ታወጣላችሁ።

**ማስታወሻ**

ሥርወ ቃልከአንድ ቃል ውስጥ አናባቢዎች ወጥተውለት የሚቀረው የተናባቢ ክፍል ነው።

**ተግባር1. ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ ተመልክታችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ስርወ ቃል አውጡ።**

**ለምሳሌ** ፡- በቀለ / ብ - ቅ - ል /

በቀለ ከሚለው ቃል አናባቢዎቹ ሲወጡለት የሚቀረው ሳድስ ፊደል ብ- ቅ- ል ነው። /ብ - ቅ- ል/ ስርወ ቃል ነው፡፧

| | ቃል | ስርወ ቃል |
|---|---|---|
| 1 | ገደለ | /ግ - ድ - ል/ |
| 2. | ለቀመ | |
| 3. | ሰቀለ | |

4. ደከመ
5. ብልህ

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለትምህርት ሰባት

ሥነ ጽሁፍ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ**

የልብ ወለድን ምንነት ታውቃላችሁ፡፡

የልብ ወለድን ዓይነቶች ትናገራላችሁ፡፡

ማስታወሻ

ልቦለድ በእውኑ ዓለም የሚንቀሳቀሱትን የግለሰብና የማህበረሰብ ህይወት በቃላት አማካይነት የሚያንጸባርቅ ምናባዊ ስዕል ሆኖ የሚታይ የሥነጽሑፍ ስራ ነው፡፡

አጭር ልቦለድ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን ፍጥነት ያለውና ውሱን ገጸባህርያትና፣ውሱን መቼት ያለው የፈጠራ ስራ ነው፡፡

ረጅም ልቦለድ ሰፊ ሃሳብ የሚይዝ፣ከልደት እስከሞት የሚተርክ፣ብዙ ገጸ ባህርያትን የሚይዝ የፈጠራ ስራ ነው፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ስሩ ፡፡**

1. በአጭር ልብወለድና በረጅም ልብወለድ ውስጥ የጋራ ሊሆኑ የሚችሉ ባህርያት ምንድን ናቸው?
2. ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ አንድነታቸው ምንድነው?
3. የሁለቱ ልዩነት ምን እንደሆነ ግለጹ

ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስምንት

ስማዊ ሀረግ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርተ በኋላ**

ስማዊ ሀረግን ትመሰርታላችሁ፡፡

ከዐረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረግን ታወጣላችሁ፡፡

ማስታወሻ

ስማዊ ሀረግ ማለት መሪው ስም የሆነና በመሪው ብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመጣመር ስማዊ ሀረግን የሚመሰርት ነው

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡትን የስማዊ ሀረግ ምሳሌዎች ተመልከቱ**

| | |
|---|---|
| ረጅም <u>መንገድ</u> | አዲስ <u>ሹራብ</u> |
| ትልቅ <u>ልጅ</u> | ቀይ <u>ብዕር</u> |
| ጎበዝ <u>ተማሪ</u> | ሰባራ <u>ምጣድ</u> |

**ከላይ ከተዘረዘሩት ሀረጎች ከስር የተሰመረባቸው ቃላት በሙሉ ስሞች ናቸው፡፡ በግራ በኩል ካሉት ቃላት ጋር በመቀናጀት ደግሞ ስማዊ ሀረግን መስርተዋል ማለት ነው፡፡**

**ተግባር2. ከዚህ በታች የተለያዩ ቃላት ቀርበዋል፡፡ እነዚህንቃላት በማቀናጀት ስማዊ ሀረግመስርቱ፡፡**

አዲስ ሽክላ ቤት ስው

ትልቅ የእንጀራ ድስት

እናት

ተማሪ የልጅ ሰነፍ

እምቅ

**ተግባር3. ከዚህ በታች ከቀረቡት ሀረጎች ውስጥ ስም የሆነውን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

| | |
|---|---|
| ምሳሌ - ሀ/ የአማርኛ <u>አስተማሪ</u> | መ/ ነገረኛ ሰው |
| ለ/ ፈጣን ልጅ | ሠ/ አሮጌ ጫማ |
| ሐ/ ትምህርት ቤት | ረ/ የዶሮ ስጋ |

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለትምህርት ዘጠኝ

### ግጥም

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

**ግጥሙን ታነባላችሁ፡፡**

ከግጥሙ ውስጥ ስንኝና ሀረጎችን ቆጥራችሁ ታወጣላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብቡት፡፡**

**ግጥም**

እወድሻለው ማለት ፣አይጠቅም አይበቃ ፣
ፍቅሬ ነሽ ማለትም ፣አይጠቅም አይበቃ፣
ነፍሴ  ነሽ ማለትም ፣ልቤን አያርሰው ፣
የፍቅራችን ነገር ፣ዝም ነው ዝም ነው፡፡
ምን ሳርገው መውደዴን ፤ ለመግለጽ በሙሉ?
ልሳምሽ ? ልቀፍሽ ?ላልቅስ  ወይ ላመሉ?
እግርሽን ልሳም ወይ፣ ልስገድልሽ ወይ ፣
አዋጅ ልናገር ወይ በየአደባባይ ፣
ወረቀት ልፃፍ ወይ፣ ልላክ ወይ ደብዳቤ፣
እያንዳንዱን ቃላት ወስጄ ከልቤ፡፡

(መንግስቱ ለማ ፣1955፣23)

**ተግባር2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ግጥሙን መሰረት በማድረግ መልሱ፡፡**

1. የግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ ምን ይላል ?
2. የመጀመሪያው ስንኝ ስንት ሀረግ አለው ?
3. ግጥሙ በአጠቃላይ ስንት ስንኝ ነው ያለው?
4. በግጥሙ ውስጥ ስንት ሀረጎች አሉ ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለተላላፊ በሽታዎች ከመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች ሰርታችኋል፡፡ እንዲሁም ስለ ኮሮና ቫይረስ የቀረበላችሁን ምንባብ አንብባችሁ የመረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል፤ስለተራኪ ድርሰት ፣ምንነት አውቃችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት በምሳሌው መሰረት ጽፋችኋል፡፡ ስለ ስርወ ቃል ምንንት አውቃችኋል፡፡ ስለ ልብወለድ ምንነትና አይነቶች አውቃችኋል፡፡ በመጨረሻም ስማዊ ሀረግን አውጥታችኋል፡፡ ስንኙና ሀረግን ከግጥም ውስጥ አውጥታችኋል፡፡

**ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጻፍ መልሱ፡፡**

1 ስለ ኮሮና ቫይረስ በቡድን በመሆን መተላለፊያ መንገዶችንና መከላከያ መንገዶችን አዘጋጅታችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡

2. አንድ ልብ ወለድ ከአንድ ምዕራፍ አንብባችሁ ከውስጡ ገጸ ባህሪያትንና መቼቶችን ለቅማችሁ አውጡና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምዕራፍ አስር

የፈጠራ ስራ

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ

- የፈጠራ ስራዎችን አዳምጣችሁ ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ፡፡
- በማህበራዊ አውዶች ሀሳብን በአክብሮት ትገልጻላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ታወጣላችሁ፡፡
- ገላጭ ድርሰትን መጻፍ ትችላላችሁ፡፡
- ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- ግሳዊ ሐረግን ትመሰርታላችሁ፡፡
- የአነጻጻሪ ዘይቤን ምንነት ትረዳላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

| | |
|---|---|
| አቅርቦት | ቬንትሌተር |
| ቁሳቁስ | ወረርሽኝ |
| አየር ንብረት | አገርአቀፍ |

**አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አንድ**

**ማዳመጥ፡-**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

ስለፈጠራ ስራ የቀረበላችሁን ምንባብ ታዳምጣላችሁ፡፡

የሚቀርብላችሁን ጥያቄ ትመልሳላችሁ::

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

1. የፈጠራ ስራ ማለት ምንድነው?
2. ተማሪዎች ትርፍ ጊዜያቸውን በምን አይነት ነገር ላይ ቢያሳልፉ ጥሩ ነው?
3. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች ምን መስራት ትችላላችሁ?

**ተግባር1. ከዚህ በመቀጠል መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በማዳመጥ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. የፈጠራ ስራ የሚጀምረው ካለንበት ደረጃ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. የፈጠራ ስራን ለመስራት የመጀመሪያው ነገር ፍላጎት ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሐ. የሰው ልጅ ለአሁኑ ደረጃ የደረሰው ምን በማድረጉ ነው?

መ. ከዚህ ምንባብ ምንድነው የተማራችሁት?

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሁለት

### መናገር

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የአክብሮት ንግግርን አውቃችሁ ተግባራዊ ታደርጋላችሁ፡፡

አውዱን አይታችሁ ንግግራችሁን ታስተካክላላችሁ፡፡

**ተግባር1 ቀጥለው የቀረቡትን ምሳሌዎች ተመልክታችሁ ቀጥለው ለቀረቡት አውዶች ተገቢውን ንግግር አድርጉ፡፡**

1.**በእድሜ ለገፉ ሰዎች የሚቀርብ**

እንደምን አሉ?

ምን ልታዘዝዎት?

2. **በእድሜ እኩያ ለሆኑ**

ወንድሜ እንዴት ነህ?

እህቴ ምን ልርዳሽ?

3.**ለማንኛውም ሰው አክብሮት የተሞላበት ንግግር ማድረግ**

እህቴ - ወደ አርባ ምንጭ የሚሄደው መኪና ወጣ?

ወንድም - ወደ ኮንሶ የሚሄደውን መንገድ ልትነግረኝ ትችላለህ?

1. ለትላልቅ ሰዎች ሰላምታ ሲቀርብ
2. የስራ ሀላፊዎችን ስናነጋግር
3. የሐይማኖት አባቶችን ስናነጋግር

## አንደኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሦስት

### አቀላጥፎ ማንበብ

**ተማሪዎች ከዚህ ትምርት በኋላ**

ምንባቡን አንብባችሁ ትረዳላችሁ፡፡

ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፡፡

የምንባቡን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታካፍላላችሁ፡፡

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የፈጠራ ስራ ምንድነው?
2. ለፈጠራ ስራ ምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋላ?

### የኢዘዲን ከሚል የፈጠራ ስራዎች

ኢዘዲን ብዙ የፈጠራ ስራዎችን የሰራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ደግሞ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት እያጋጠመ ያለውን እጥረት ለመፍታት የመተንፈሻ መሳሪያ ወይም ቬንትሌተርን ጨምሮ ሦስት የፈጠራ ስራዎችን ሰርቷል፡፡ ለበሽታ ሊያጋልጡ የሚችሉ ነገሮች ለፈጠራ ስራዎቹ መነሻ ሆነውታል፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ በአለም ላይ ከተከሰተ ወዲህ የህክምና መሳሪያዎችና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ከምንጊዜውም በላይ አንገብጋቢ ጉዳዮች ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ወረርሽኙ በድንገት የተከሰተ በመሆኑ ጥሩ የህክምና አቅርቦት ላላቸው ሀገራት ጭምር አቅምን የሚፈትን ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ አንዳንድ የፈጠራ ባለሙያዎች ችግር ፈቺ ስራዎችን ይዘው መምጣት ጀምረዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ወጣት ኢዘዲን ከሚል አንዱ ነው፡፡ ኢዘዲን በወልቂጤ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ሲሆን በርካታ የፈጠራ ስራዎች አሉት፡፡ ከፈጠራ ስራዎቹ ለመጥቀስ ያክል በፀሐይ ብርሃንና በኤሌክትሪክ የሚሰራ ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ ሰርቶ ነበር፡፡ ምንም አይነት ነዳጅ አይጠቀምም ለአየር ንብረት ተስማሚ ነው፣ በሰዓት 60 ኪሎሜትር ይሄዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኤሌክትሪክና በፀሐይ ብርሃን የሚሰራ ብስክሌት ሰርቷል፡፡ " በሩራል ኢነርጂ ቴክኖሎጂ" የፈጠራ

ውድድር በአገር አቀፍ ደረጃ አሸናፊ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት እያጋጠመ ያለውን እጥረት ለመፍታት የመተንፈሻ መሳሪያ ወይም ቬንትሌተርን ጨምሮ ሦስት የፈጠራ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

(ምንጭ ሳይንስና ሕብረተሰብ Dal. Com)

ተግባር1. **ከዚህ ከጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ኢዘዲን የስንተኛ ክፍል ተማሪ ነው?

ለ. ኢዘዲን ምን አይነት ተማሪ ነው?

ሐ. በሀገራችን የፈጠራ ስራ ባለሙያዎች መኖራቸው ምን ጠቀሜታ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

መ. ከምንባቡ የተረዳችሁትን መልዕክት ባጭሩ አብራሩ፡፡

**ተግባር2. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ትክክል ከሆነ "እውነት" ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ዓለምን ስጋት ላይ የጣለው ወረርሽኝ የኮረና ቫይረስ ነው፡፡

ለ. የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ልጆች በሀገሪቱ ላይ ለሚከሰተው ችግር የመፍትሔ አካል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሐ. ልጆች ያላቸውን ተሰጥዎ እንዲያጎለብቱ ወላጆች የማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

መ. ለኮሮና ቫይረስ በጣም አንገብጋቢ የሆነ ነገር የንፅህና መጠበቂያ መሣሪያ ብቻ ነው፡፡

ሠ. ከኢዘዲን የፈጠራ ስራዎች ውስጥ አንዱ በነዳጅ የሚሰራ ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ ተጠቃሽ ነው፡፡

ረ. ኢዘዲን የሰራቸው የፈጠራ ስራዎች ቬንትሌተርን ጨምሮ ሦስት የፈጠራ ስራዎች ናቸው፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አራት

### መጻፍ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

ስለ ገላጭ ድርሰት ታውቃላችሁ፡፡

በገላጭ ድርሰት አንድ ጽሁፍ ትጽፋላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

ገላጭ ድርሰት በአንድ ነገር ወይም ሀሳብ ወይም ጉዳይ ላይ የሚጻፍ ድርሰትሲሆን አንድን ታሪካዊ ሁኔታ ለመተርጎም፣የአካልን አወቃቀር ፣የአንድን ነገር አሰራር፣የቃልን ትርጓሜ፣ወዘተ.ለማቅረብ ይውላል፡፡

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረበውን ገላጭ አንቀጽአንብባችሁ፤ እናንተ ደግሞ ስለ ቡና አፈላል አንድ ገላጭ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

**ንብ**

የንብ አካላት አሰራር የሚገርም ነው፡፡ አካላቷ በሦስት ክፍል የተከፈለ ሲሆን በአንደኛው ክፍል የምታሸትበትና የምትዳስስበት፣ የምትልስበትን በግንባሯ በስተቀኝና በስተግራ ሁለት ቀጫጭን ነገሮች እንደ ቀንድ የሆነ አሏት፡፡ ደግሞ በዚህ በራቷ ላይ ሁለት ትልልቅ ጠፍጣፋ አይኖች በግራና በቀኝ ሆነው ለማየት የሚያስችሏት በሌሎች ትንንሽ አይኖች የተሞሉ አሏት፡፡....

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

**የቃላት ተዛማጅ ትርጉም**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡፡

የቃላትን ተዛማጅ ትርጉም አውቃችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡

**ተግባር1. ከዚህ ከጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመመልከት ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ተዛማጅ ትርጉማቸውን ተናገሩ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ሀገር በእናት ትመሰላለች፡፡

ለ. ፍሬ በልጅ ይመሰላል፡፡

1. እወቀት
2. ድንቁርና
3. ችግኝ
4. አድባር
5. አረንጓዴ
6. እርግብ

**ተግባር2. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ዐረፍተነገር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሰላም የነገሮች ሁሉ መሰረት ነው፡፡

1. ብርሃን
2. ጨለማ
3. ህፃን
4. ባለግርማ
5. ልምላሜ
6. ልጅ
7. እናት

**ተግባር 3. ሌሎች ተዛማጅ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በማምጣት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡**

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

ስዕል ተመልክታችሁ ታብራራላችሁ፡፡

ስእሎችን ታነጻጽራላችሁ፡፡





ስእል 1 ስዕል 2

**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ስእሎቹ ስለምንድነው የሚገልፁት?
2. በስዕሎቹ ላይ ያሉትን ነገሮች ተናገሩ?
3. በሁለቱ ስእሎች ላይ ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?
4. መጥፎ ባህሪይ ነው ብላችሁ የምትገልፁት የትኛውን ስዕል ነው?
5. የምትደግፉት የትኛውን ስዕል ነው?

**ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ሰባት**

ስዋስው

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

የግሳዊ ሀረግን ምንነት ትረዳላችሁ፡፡

ግሳዊ ሀረግን ትመሰርታላችሁ፡፡

ማስታወሻ

ግሳዊ ሀረግ -የሀረጉ መሪቃል ግስ የሆነ የሀረግ አይነት ነው፡፡

**ተግባር 1. ከዚህ በታች የቀረቡ ምሳሌዎችን በመመልከት ቀጥለው ከቀረቡት ሀረጎች ውስጥ ግሳዊ ሀረግን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. አስተማሪ ሆነ፡፡

ለ. መኪና ገዛ፡፡

ሐ. ምሳ በላ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ወጣት ልጅ | 6. የሰነፍ ቆሎ | 11. እንጀራ ጋገረች፡፡ |
| 2. ኮፍያ አደረገ፡፡ | 7. ወድቆ ተነሳ ፡፡ | 12. ልብሱን አጠበ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 3. እንጨት ሰበረ፡፡ | 8. ታሞ ሞተ፡፡ | 13. ትምህርት ቤት ሄደ፡፡ |
| 4 እሸት በቆሎ | 9. የስንዴ ዳቦ | 14. ትኩስ ወተት |
| 5. ፈረስ ጋለበ፡፡ | 10 ወተት ጠጣ፡፡ | 15 ትልቁ መጽሐፍ |

**ተግባር2. ከዚህ በታች የቀረቡ ቃላትን አቀናጅታችሁ ግሳዊ ሀረግን መስርቱ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኳስ | በላ | እንጨት | ጠጣ |
| አየሮጠ | ጋገረች | ተማረ | ተጫወተ |
| ትምህርት | ደፋች | ውሃ | እንጀራ |
| ምሳ | ፈለጠ | መጣ | ዳቦ |

## ሁለተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ስምንት

### ቅጽል፡-

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የቅጽሎችን ብዙ ቁጥር አውቃችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡትን ቅጽሎች ወደ ብዙ ቁጥር እንዴት እንደሚቀየሩ ከምሳሌው ተመልክታችሁ ተረዱ፡፡**

**ምሳሌ 1፡-** ጥቁር - ኦች ጥቁሮች

ቢጫ - ዎች ቢጫዎች

ከቀረበው ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው ቅጽሎች እንደ ስሞች ሁሉ የብዙ ቁጥር አብዥዎች "ኦች ና - ዎች "ን እንደሚወስዱ አይታችኋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም በዚሁ መሰረት ይሄዳሉ ማለት አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ከዚህ የተለየ የብዙ ቁጥር አመሰራረት አላቸው፡፡

**ተግባር2. ቀጥለው የቀረቡትን ቅጽሎች ወደ ብዙ ቁጥር ቀይራችሁ ጻፉ፡፡**

1. ሰነፍ
2. ጎበዝ
3. ቀይ
4. ደረቅ
5. ቀጭን

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

### ዘይቤ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

የአነጻጻሪ ዘይቤን ምንነት ታውቃላችሁ፡፡

አነጻጻሪ ዘይቤን ተጠቅማችሁ ትናገራላችሁ፡፡

**ተግባር1. ለአነጻጻሪ ዘይቤ ምሳሌ የሚሆኑትን ከዚህ በታች ተመልከቱ፡፡**

ሀ. ጃንቦ እንደአንበሳ ያስፈራል፡፡ ጃንቦን ከአንበሳ ጋር ነው ያነጻጸረው፡፡

ለ. ልጁ ቁርጥ አባቱን ይመስላል፡፡ ልጁን ከአባቱ ጋር ነው ያመሳሰለው፡፡

ሐ. ጨለማ የገሀነም ያህል ያስፈራል፡፡ ጨለማን ከገሀነም ጋር ነው ያነጻጸረው፡፡

**ተግባር2. ከላይ በቀረበላችሁ ምሳሌ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡት አነጻጻሪ ዘይቤዎች ከማን ጋር እንደተነጻጸሩ አሳዩ፡፡**

ሀ. ልጁ እንደ መብረቅ ጮኸብኝ፡፡

ለ. ብሩክ እንደ እርግብ የዋህ ነው፡፡

ሐ. የልጅቷ ፊት ብርቱኳን ይመስላል፡፡

መ. ሰውየው እንደጅብ በልቶ አይጠግብም፡፡

ሠ. ሳሊ ኤሊ ይመስል ቶሎ አይራመድም፡፡

ረ. ዳንቦቢ እንደ እባብ ተንኮለኛ ነው፡፡

**ተግባር3. ከዚህ ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ በመሆን አነጻጻሪ ዘይቤዎችን ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ.

ለ.

ሐ.

መ.

ሠ.

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለፈጠራ ስራ የቀረበላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ የቀረበላችሁን ጥያቄ መልሳችኋል፡፡ የአክብሮት ወይም የትህትና ንግግር እንዴት እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ ስለ ገላጭ ድርሰት ምንነትና አጻጻፍ ተምራችኋል፡፡ ገላጭ ድርሰትም በአንድ አንቀጽ ፅፋችኋል፡፡ በመቀጠልም የቃላትን ተዛማጅ ትርጉም አውቃችኋል፡፡ ስለ ግሳዊ ሀረግ ተምራችሁ፤ ግሳዊ ሀረግን መስርታችኋል፡፡ በመጨረሻም ስለ ዘይቤ ምንነትና ስለ አነጻጻሪ ዘይቤ ምንነት ተምራችሁ ምዕራፉን አጠናቃችኋል፡፡

**ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ግሳዊ ሀረግ መስርታችሁ አሳዩ

ሀ. ------------------------------------------------------------------

ለ. ------------------------------------------------------------------

ሐ. ------------------------------------------------------------------

2. **ማን ከማን ጋር እንደተነጻጸረ አሳዩ**

ሀ. አለም እንደ እርግብ የዋህ ነው፡፡

ለ. ሉዘንቦ አንበሳ ይመስል ያስፈራል፡፡

ሐ. ታሪኩ እንደ እባብ ተንኮለኛ ነው፡፡

3. **ተዛማጅ ትርጉማቸውን ጻፉ**

ሀ. ፍሬ ------------------------------------------

ለ. ዋርካ ----------------------------------------

ሐ. እርግብ ---------------------------------------

# ዋቢ ጽሁፎች

መስፍን ሀብተማርያም፡፡(1996-1999)፡፡ *የቡናቤት ሰዕሎች ና ሌሎች ወጎች፡፡* አዲስ አበባ፣ ኤማይ ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

መንግስቱ ለማ፡፡(1955*)፡፡ የግጥም ጉባኤ*፡፡አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሣህሉ አክሊሉና ሌሎች፡፡ (1993)፡፡ *የሥነጽሑፍ ዓይነቶች*፡፡ አዲስ አበባ፣ትምህርት ሚኒስትር፡፡

ባይ ይማም (2002)፡፡አጭርና ቀላል የአማርኛ ስዋስው፡፡አዲሰ አበባ፣አልፋ አሳታሚዎች፡፡

አገኘሁ አለማየሁና ሌሎች (1993)፡፡የድርሰት አጻጻፍ፣ አዲስ አበባ፣ትምህርት ሚኒስትር፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(2007)፡፡*የሥነጽሁፍ መሠረታውያን*፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993) ፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1989)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ስዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

ደበበ ሰይፉ፡፡ (1980)፡፡ *የብርሃን ፍቅር፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

ሙዳዬ ቃላት

ሙስና - ህጋዊ ያልሆነ ጥቅም ማግኘት

ወላጅ አጥ - እናት አባት በተለያዩ ምክንያቶች የተለዩአቸው

መደብ - የአመለካከት ጎራ/ፖለቲካ

ሳልስ - ሦስተኛ

ሳድስ - ስድስተኛ

ሚና - ድርሻ

የምልክት ቋንቋ - የአካላዊ እንቅስቃሴ ቋንቋ

መስማት የተሳናቸው - የማዳመጥ ችግር ያለባቸው

ክራንች - የእግር ችግር ያለባቸው መደገፊያ

ብሬል - የአይነ ስውራን መፃፊያ ገበታ

ዊልቸር - አካል ጉዳተኞች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ጋሪ

ጥገኛ - እራሱን ችሎ የማይቆም

ቅድመ - በመጀመሪያ

ድህረ - በስተ መጨረሻ

ስዋስው - አገባብ

ኃይለቃል - በአንቀጽ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የሚይዘው ዓረፍተ ነገር

ግጭት - አለመግባባት

ማዋቀር - ማደራጀት

እሬቻ - የኦሮሞ ባህላዊ በአል

ደራሮ - የጌዴኦ ዘመን መለወጫ

ጊፋታ - የወላይታ ዘመን መለወጫ

ፍቼ - የሲዳማ ዘመን መለወጫ

ጋዜ ማስቃላ - የጎፋ ዘመን መለወጫ

ዮዮ ማስቃላ - የጋሞ ዘመን መለወጫ

ያሆዴ ማስቃላ - የሀድያ ዘመን መለወጫ

ያኦ ማስቃላ - የአይዳ ዘመን መለወጫ

እርጥብ ሳር - የሰላም ምልክት / የእርቅ ምልክት

ጥንድ - ሁለት

ስልት - ዘዴ

ማስክ- በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታን ለመከላከል
የሚጠቅም የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ

ማጣመር - ማያያዝ /ማገናኘት

ኮሮና ቫይረስ - ወደ ሰው የሚተላለፍ ገዳይ በሽታ

ኤምኤ - ሁለተኛ ድግሪ

ፒኤችዲ - ሦስተኛ ድግሪ ወይም ዶክትሬት

ጠባብ - አስፍቶ የማይመለከት ፣ራስወዳድ

ጫፍ የወጣ - በአመለካከት መንገዱን የሳተ

የሀገር ፍቅር - አገርን መውደድ

መቻቻል - በትዕግስት መኖር / ተከባብሮ መኖር

የኑሮ ዘይቤ - የአኗኗር ሁኔታ

ችግር ፍቺ - መፍትሔ ሰጪ

ሳኒታይዘር - ንጽህና መጠበቂያ

ፊጠራ - ግኝት

መንስኤ - መነሻ ምክንያት

የባህል መድሐኒት - በባህላዊ መንገድ የተዘጋጀ መድሐኒት